«መሄድሽ ነው እንዴ?» ሲል ጠየቃት::

«አምን መሄዴ ነው፣ ያደረጋችሁልኝን አልረሳም፣ ባለውለታችሁ ነኝ:: ትናንት እርስዎ ከወደቅሁበት ባያነሱኝ ኖሮ ይሽኔ ምናልባትም ሞቼ ነበር:: እርስዎንም ሆነ ባለቤትዎን ምን ጊዜም ቢሆን አልረሳችሁም» ባለችው ጊዜ ገበሬው ሳቅ አለ:: ዳያን በችኮላ «እንግዲህ ደህና ሁኑ፣ ጤና ይስጥልኝ:: ወደ ለንደን መሄዴ ነው:: እዚያ ከደረስኩ ምንም አልሆንም» ስትለው «ከእዚያ የምታውቂው ሰው አለ?» ብሎ ጠይቃት:: «ለንደን ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ኖሬአለሁ» ብላ መለሰችለት::

«ለንደን ከተማ ውስጥ መኖርሽና ከተማውን ማወቅሽ ጥሩ ነው:: መንገዱን ጨርት ያድርግልሽ:: ወደፊት አስታውሽን፤ የእኛ ከእዚህ መኖር አትርሺ:: በዚህ ባለፍሽ ቁጥር ቤትሽ ነው» ሲላት «በአካባቢው የባቡር ጣቢያ ይገኛል?» ስትል ዳያን ጠየቀችው::

«ጣቢያው ከዚህ ብዙም አይርቅም። እንዲያውም በአሥር ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ባቡሩ ይመጣል:: ወደፊት ግን እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ» ብሏት ይለያያሉ:: ዳያን ወደ ባቡር ጣቢያ ጉዞዋን ቀጠለች:: ገበሬው ኩትሂቶውን ትቶ እርስዋ ስትጓዝ ቆሞ በሩት ተመለከታት::

«አንድ ነገር መኖር አለበት:: ይህች ልጅ እስከ ዛሬ ካየኋቸው ሴቶች በሙሉ የተሻለ መልክ ያላት ቆንጆ ናት:: ሆኖም ይኸው ትንከራተታለች» ሲል ገበሬው ሲያሰላስል ባለቤቱ ብቅ ብላ «ጆን፣ ልጅትዋን አይተሃል?» ስትል ጠየቀችው::

«አምን፣ ሄዳለች:: ተሰናብታኝ ወደ ባቡር ጣቢያ ወርዳለች::»

«ሄደች!» ስትል ሴትዮዋ በመገረም ትናገራለች:: «ለዚህ ነዋ የላመችኝ! ወዴት ይሆን የምትሄደው?» ብላ ስትጠይቀው «ወደ ለንደን» ሲል መለሰላት::

«አይ ምስኪን! ጆን፣ ይህቺ ሕፃን አሁን ባል ያገባች ትመስላለች? በጣም ከፍቷታል:: ከቤትዋ ጠፍታ እኮ ነው የመጣችው:: ልጁን ሰው ገድሉብኛል፣ ሆኖም አውቀው አይደለም:: ብቻ ልጁ በለው ተገድሉአል» ብላ ነግራው የገበሬው ሚስት በጣም እየተከዘች «ይህ ዓለም ጨርሶ የማይገባ እንግዳ የሆነ ዓለም ነው:: በውስጡ ብዙ ሀዘኔተኞች እንዳሉበት አልጠራጠርም» አለች::

ምዕራፍ አሥራ አንድ

አሳበድዋት

ዳያን ቤትዋን ለቅቃ ከመውጣትዋ በፊት እምርራ ስትናገር፣ና ሄስተ-
ዳያን ከነበረችበት ክፍል ስትወጣ አኒ ክሌግን ይዛ ወጥታ ነበር።

«ልጅትዋ አብዳለች። ልጂ ነይ እንሂድ። አእምሮዋ እስኪመለ
ብቻዋን ብትሆን ይሻላል» ብላ አኒ ክሌግና ሄስተር ተያይዘው ስለወጡ
ማንኛቸውም ቢሆኑ ዳያን ወደ ማረፊያ ቤት መግባትዋን አላስተዋሉም
በሯን ስትከፍትም ሆነ ከቤት ስትወጣ ማንም አላያትም።

«እመቤቴ ደፍራ በመናገሬ ምናልባት ከመቆጣት አልፈው ሊደበድቡኝ
ይችላሉ። ግን ዳያንን በጣም ይበድሏታል» ስትል አሽከርዋ «ይገባታል
በማለት ሄስተር መለሰችላት።

«ለልጁ መድኃኒቱን አይሰጡት ስትል ሰጡት። አሁን ደግሞ ገብቺ
ልየው ስትልዎት መከልከል አልነበረብዎትም» ባለች ጊዜም «የሚያገባሽ
ነገር የለም። አለበለዚያ በአንቺ ላይ ይብሳል፣ አርፈሽ ተቀመጪ» አለች
- ሄስተር በቁጣ። ከዚያ በኋላ ስለዳያን ሳያነሱ ልጁ ተኝቶበት ከነበረው
ክፍል ደረሱ። ድምፅ እንዳያሰሙ ቡሩኖ በእጁ ምልክት ስለሰጣቸው በሩን
ቀስ ብለው ዘጉት።

«እርግጠኛ ነኝ እየተሻለው ሄዷል» ብሎ ቡሩኖ ሲነግራት ሄስተር
የልጁን ፊት መለስ ማለቱን ተገነዘበች። በእርግጥም የልጁ ሰውነት መለስ
ብሏል፣ ማቃሰቱንም አቁሞአል።

«አምን፣ ተሽሎታል» አለች ሄስተር። «አሁን ማድረግ ያለብን ወዲህና
ወዲያ እንዳይል መጠበቅ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጨርሶ ይድናል።»

ሄስተር ስለልጁ መዳን ስታረጋግለት ቡሩኖ ባለቤቱ ትዝ ብላው
«ዳያን የት ነው ያለችው?» ሲል ጠየቀ።

«ከክፍልዋ ወይም ከአንዱ ክፍል ውስጥ ትሆናለች» ብላ ሄስተር
ከመለሰች በኋላ «እባክህን ተዋት፣ እንድትመጣም ሰው ባትልክ ይሻላል።
በመጥፎ ሁኔታ ላይ ነው ያለችው። ስለተበሳጨች አእምሮዋ ልክ አይመ
ስለኝም» ስትለው «አሁን የመበሳጨት ስሜት የሚታይበት ጊዜ አይደለም፣
ለመሆኑ ምንድነው ያናደዳት?» ሲል ሌላ ጥያቄ ጠየቀ

«ልጅዋን እሹሩሩ ለማለት ትፈልጋለች። ልጁ ካለበት ገብታ
እያለቀሰችና እየጮኸች ልጁን ብትታቀፍ ደግሞ ትገድለዋለች።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እውነትሽን ነው፣ አምቃ ነው የምትገድለው። ግን ልጁን እንደ ታሸለው ሰው ሳኪና ንገርዋት። ይህንን የምሥራች ለመስማት ሳትጓጓ አትቀርም» ብሎ ሲያላስብ «እኔ እነግራታለሁ» አለች ሂስተር።

ሂስተር ያለፈው ድርጊትዋ ስለጸጸታት ልጁን በመንከባከብ ትጠብ ቀዋለች። ምናልባትም የልጁ ሕይወት የተመለሰው በእርስዋ ጥረት ሳይሆን አልቀረም። መዲሀና መዲያ በማለት ራሰዋን ለማዝናናት አልፈለገችም። የአንድ ወንድምዋ ልጅ በመሆኑ በልብዋ ትወድደዋለች። እመል ሆኖ ነው እንጂ ልጁ በደምብ ቢያዝ አትጠላም። ልጁን እንደመረዘችው በተገነዘበች ጊዜ እጅግ አዝናለች። ጳያን አገር ጥላ ከመሄድዋ በፊት የተናገረችውም ቃል እጅግ አስደንግጧት ነበር። የጳያን ፊት መለዋወጥ፣ የዓይንዋ መንከራተትና ርግማንዋ ከጎሊናዋ ውስጥ ተቀርጾአል። ሆኖም ጳያን ከቤት ጠፍታ ትሄዳለች፣ ከሄደችም አትመለስም የሚል ጥርጣሬ አልነበራትም።

ልጁን ስትንከባከብ እንኳን ታሰላስለው የነበረው «የልቤን ገልጪ አነጋግራታለሀ፣ ከዚያም ከጳያን ጋር እንታረቃለን» የሚል ነበር። ግን በዚያን ሰዓት በይበልጥ አስጨንቋት የነበረው የልጁ በእርስዋ ምክንያት መታመም ነበር። ስለዚህ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ልጁን እንጂ እድለ-ቢስዋን እናቱን ማንም አላስታወም። ዶክተሩ ስለተመለሰ ልጁ ከነበረበት ከፍል ወሰዱት። ገና ልጁን ሲያይ ፊቱ ፈገግ አለ።

«አዎን» አለ ሐኪሙ፤ ቡሩኖ ለጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ። «ተሽሎታል፣ አሁን እንኳን ተስፋ ያለው ይመስላል። ለክፉ የሚያደርሰው ቢሆን እስከዚህ አያቆየውም ነበር። ሚስስ ቡሩኖን ባገኝና እንኳን ደስ ያለሽ ብላት ደስ ይለኝ ነበር፤ ለማነኛውም የምሥራቹን ንገርዋት። እኔ ግን አሁን ልሂድና ጠዋት እመለሳለሁ። ነገ ደግሞ ከዚህ በበለጠ እንደሚሻለው ተስፋ አደርጋለሁ» ሲል ከቤት አሽከሮች አንድዋ ጳያንን ፍለጋ ወጣች። ግን ወዲያውኑ ተመልሳ ጳያን ከቤት አለመኖርዋን ተናገረች። ሐኪሙ «ከቤት የለችም!» ይላል። የልጁን ሁኔታ ለመስማት በቅርብ ሆና አለመጠ ባበትዋ እንግዳ ነገር ሆነበት።

«ምንም አይደለም፣ ነገ ጠዋት ስመለስ አነጋግራታለሁ» ብሎ ሐኪሙ ሄደ። ጳያን ቶሎ ባለመመለስዋ ቡሩኖ በጣም ስለገረመው «ለምን ይሆን ጳያን ያልመጣችው?» ብሎ እጎቱን ሲጠቃት «ተበሳጭታ ይሆናል» ስትል ሂስተር መለሰችለት።

«ምን አበሳጫት?» በማለት እንደገና ሲጠይቅ «ቡሩኖ የባለቤትህ ጠባይ ምን ዓይነት እንደሆነ እንድነግርህ አትጠይቀኝ፣ እኔም አላውቀው።

እኔ የማውቀው ነገር ቢኖር በጣም መበሳጨትዋን ብቻ ነው።››

ቡሩኖ ተቆጥቶ ከቤት ይወጣል። ጊዜው እያለፈና ልጁም እየተራበ ሲሄድ ቡሩኖ የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ ይሰማዋል።

«ከእንግዲህ ወዲህ ምንም አይሆንም። መድኃኒቱን ለልጁ በመስጠት ተሳስቼአለሁ፤ መስጠት አልነበረብኝም» አለች ሄስተር የጸጸት ሰሚት እየታየባት።

«ከልጁ አጠገብ ቁጭ ብዬ ሳለ ዳያንን 'በድለናታል' እያልኩ ሳሰላስል ነበር። ትንሽ ራሳችንን ማስተካከል ይኖርብናል። ገና የአሥራ ስምንት ዓመት ልጅ መሆንዋን ረስተናል መሰለኝ። በዚህ እድሜዋ ሁሉንም ነገር እንድታውቅ እንፈልጋለን። ግን ሊሆን አይችልም፣ ገና ልጅ ናት። ልጁ ሲሻለው የቤቱ መስኮት እንዲከፈት ከፈለገች ብንፈቅድላት። ጓደኞቻችንም መጥተው ቢያይዋትና እንዳንዴም ደስ እንዲላት ይዘናት ሽርሽር ብንወጣ እያልኩ ሳወጣና ሳወርድ ነበር» አለ ቡሩኖ።

«እንዳንድ ሰዎች ከገልቱ ልጅ ፍቅር ይይዛቸዋል» ስትለው ቡሩኖ «የፊትዋ ሁኔታ ትዝ ይለኛል። ከእዚህ ቁጭ ብዬ ሳስተውላት ፊትዋ እንዴት እንደተለዋወጠና እንደ ገረጣ አሁንም ጉልህ ሆኖ ይታየኛል» ሲል መለሰላት።

«ቡሩኖ ትሰማለህ? ዛሬማ ክፉ ቃል ከመወርወር አልፋ እኔን ስትራገም ነበር» ብላ ሄስተር አቢቱታዋን ስትጀምር ቡሩኖ በንቀት ዓይን አተኩሮ ተመለከታት።

«ይቅር እንድትያት ይገባል። ልጅዋን በጣም ትወድደዋለች። በእንቺ ምክንያት የሞተ መስሏት ይሆናል የተራገመችው።»

«ይቅር ብዬአለሁ» አለች ሄስተር እያፈዘች። «አየህ፣ ልጁ ይስቅ ጀመር፣ ተመስገን፣ ከምስጋና በስተቀር ለእንተ ምን ይገባል!»

ቡሩኖ ከልጁ አጠገብ ሳይነቃነቅ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሆነ። ለእንድ ደቂቃ እንኳን ከዚያ ለመነሳት አልፈለገም። ዳያን የልጅዋን ሁኔታ ሳታይ ያን ሁሉ ሰዓት በመቆየትዋ ምንኛ እንደ ተጨነቀችና እንደ ተሠቃየች ያሰላስላል። ስምንት ሰዓት ሲሞላ ግን «ሂጂ እፈልጋታለሁ። ልጁ ከተኛበት ክፍል አምጥቼ ልጁ ምን ያህል እንደተሻለው አሳያትና አብረው እንዲቆዩ አደርጋለሁ። እስከዚያን ሰዓት ድረስ ልጁ ከነበረበት ክፍል እንዳትጣባ የተደረገው በእርስዋ ለመጨከን ሳይሆን ስለልጁ ሕይወት በማሰብ እንደሆነ አስረዳታለሁ» እያለ በማሰብ ሁናቴዋ አሳዝኖት እጅግ ራራላት።

ወደ ክፍልዋ ሄደ። ጊዜው ጨለማ ስለነበር «ዳያን» ሲል ተጣራ። መልስ አላገኘም። መብራት አበራ፤ አሁንም ሊያገኛት አልቻለም። «ከክፍልዋ ውስጥ ትሆናለች» ሲል አሰበ። ሆኖም ሰጠራት አለመስማትዋ እንግዳ ነገር ነው በማለት እያሰላሰለ ወደ ክፍልዋ ቢሄድ ከዚያም ሰው የለም። «ምነው ተሞኘሁ፣ ከምድር ቤት ነዋ ቁጭ የምትለው» ብሎ በማሰብ ተስ እያለ ወደ ምድር ቤት ወርዶ ላለ፦ ወጥ ቤት፣ እንግዳ ቤት ገባ። ከእዚያም ዳያን የለችም። በዚህ ጊዜ ቡሩኖ የፍርሃት ስሜት አደረበት። ግን አገር ጥላ ትሄዳለች ብሎ አላሰበም። በመጨረሻ ምናልባት ከአሽከሮች ቤት ትሆናለች የማለት ግምት አደረበት። ሆኖም ከአሽከሮች ቤት ለመሄድ ስላልፈቀደ ልጁ ተኝቶበት ወደ ነበረው ክፍል ተመለሰ። እነ ክሌግ ከእኅቱ ጋር ቁጭ ብላ ያያል። እነ'ን ተስ ብሎ በጥቅሻ ጠራት።

«ሚስስ ቡሩኖ ምናልባት መንፈስዋ ስለተረበሸ ከሜሪ ጋር ለመጫወት ወደዚያ ሄዳ ይሆናል። ሂጂና ልጁ ተሽሎታል ብለሽ ንገሪያት። ይግሞም ላነጋግራት መፈለጌን ግለጭላት» ሲል ላካት። እነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመለሰች።

«ኧረ እሜቴ ከእዚያም የሉ። ሜሪ ደግሞ ከጠዋት ጀምሮ አላየኋ ቸውም ብላለች» ብላ ስትነግረው ቡሩኖ ታልዋን ስላልተቀበለ እውነት አልመሰለውም።

«ከጠዋት ጀምራ አላየቻትም! ታዲያ የት ሄደች?»

«ጌታዬ ለእህትዎ ለወይዘሪት ሄስተር ንገሪያት ብለው የማይጠይቁኝ ከሆነ አንድ ነገር ብነግሮት እወድዳለሁ» ብላ እየፈራች ስትናገር «አልጠ ይቅሽም፣ ንገሪኝ» አለ ልቡ በፍርሃት እየተዋጠ።

«እንግዲያውስ ሚስስ ቡሩኖ አገር ጥላ ሳትሄድ አልተረችም። ወይዘሪት ሄስተር በእርስዋ ላይ ያሳዩት ጭካኔ ማንኛውም ሰው ለመሸከም ከሚችለው በላይ ነው። ሁለቱ ዛሬ ጠዋት ብርቱና አስከፊ የሆነ ኃይለ-ቃል ነው የተለዋወጡት። ወይዘሪት ሄስተር ዳያንን 'ከዚህ ሰው ሁሉ ጠልቶሻል' ስላልዋት ምናልባት አገር ጥላ ሳትሄድ አልቀረችም።»

«ያንተ ያለህ!» ይላል ቡሩኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

«አዬ ጌታዬ፣ ልጁ የራስዋ ሆኖ ሳለ እባካችሁ አንድ ጊዜ ብቻ ገብቼ ልየው ብላ ስትለምን መከልከልዋ መከፋት ቀርቶ ፀሐይ እንደመታው በረዶ ልብን የሚያሟሟ ነው። እባካችሁ ልግባ እያለች ስትለምን ወይዘሪት ሄስተር መጥተው እንደ ውሻ እየጎተቱ ወሰድዋት። እንዳትገባ ከመከልከላቸውም በላይ 'አንቺ ገልቱና ራስወዳድ ሴት ነሽ' ሲሉ ሰደብዋት።»

«ከዚያስ?» አለ ቡሩኖ ገረድዋ እንባ ተናንቆአት ዝም ስትል ገዢ

«ከዚያ በኋላማ ሄስተር እስክ ተቆጥዋት ድረስ ከፉኛ አሰቀሰቻ ልኋ የሞተ መሰላት:: 'ወይኔ ልጄ ሞተ' እያለች ጮኸች:: እኔ እንኪን ላሙሞት ያጣጥራል እንጂ አልሞተም ብዬ ነግሬያት ነበር::»

«ልጁ ትንሽ እንደ ተሻለው እንኪን አላወቀችማ! የሞተ ነው የመሰላት?» ሲል ቡሩኖ ጠየቀ::

«ከእዚህ ወዲያ ባልናገር ይሻላል:: ጌታዬ እኔ እንደማሰበው ከሆነ ዳያን ቤቱን ጥላ ስትሄድ ልጅዋ የሞተ ነው የመሰላት::»

«ቤቱን ጥላ ልትሄድ!» ሲል ገረድዋ የተናገረችውን ከደገመ በኋላ «ግን የት ልትሄድ ትችላለች? በዓለም ላይ ያለ ሴላ ዘመድ ወይም ወዳጅ የላትም» አለ::

«ይመስለኛል የሄደችው ወደ መሞቻዋ ሥፍራ ሳይሆን አይቀርም- ትናንት ጠዋት ፊትዋ ሁሉ ያስፈራ ነበር:: ፊትዋ ከሞት አፋፍ ደርሰ የምታጣጥር ሴት ፊት መስሉ ነበር የታየኝ:: ዳያን ከመሄድዋ በፊት ወይዘሪት ሄስተርን ረግማ ነው የወጣችው:: ታዲያ ይህን ሁሉ ሰታደርግ ለሰለስ ብላ ነው:: ጤነኛ ሰው ብትሆን እንዲህ አታደርግም:: ደፍሬ በመናገሬ ይቅርታ ያድርጉልኝ እንጂ አብዳ እስክታርፈው ድረስ ጥፋት ሳይኖርባት ጥፋተኛ፤ በደል ሳይኖርባት በደለኛ በማድረግ ከሚገባት በላይ በደል ተፈጽሞባታል::»

«ታዲያ እስክ ዛሬ ድረስ ያልተነገረኝ ለምንድነው?» ሲል እየጮኸ ተናገረ ቡሩኖ::

« ያልተነገረኝ አሉ ጌታዬ፣ ምን ሊጠቅም:: እርስዎ እንደሆነ ሁል ጊዜም ወይዘሪት ሄስተርን ነበር የሚሰሙትና የሚደግፉት::»

«ይህን እንኪን አልተበለውም:: ሬማንኛውም ቤቱን አንድ በአንድ ካልፈተሽሁ ዳያን ሃኖስች ብዬ አላምንም፣ አልሄደችምም:: የት ትሄዳለች? ነይ፣ እስክናገኛት አብረን እንፈልጋት::»

አኒ ከሴግ የጌታዋን ፈቃድ ለመፈጸም ብቻ ስትል አብራው ሄደች:: ለብዙ ዓመታት ተዘግተው የኖሩት ክፍሎች እንኪን ሳይቀሩ ክፍሎቹን አንድ ገእንድ ፈተሹ:: ግን ዳያንን ሊያገኙዋት አልቻሉም:: ከቤት ውስጥ ገቡ፣ ሠሩ፣ ወደ ሜዳው ሮጡ:: ግን ከንቱ ልፋት ሆነባቸው:: ቡሩኖ ወደ እርሻው ማሳ ሄዶ አልፎ አልፎ «ዳያን» እያለ በዚያ ጪለማ ቢጣራም

መልስ ስላጣ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

«የፈጣሪ ያለህ! ሚሄድዋ እውነት ከሆነና ጉዱን አገር ሲሰማ ስሚ ምን ይላል፣ እኔ አብዳለሁ» አለ በሩጥ።

«ለጋዋ እመቤት በአግባቡ ተይዛ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስም ነበር» አለች ገረድዋ። በልብዋ ግን የሰውዬው ሁኔታ እጅግ አሳዘናት። ቡሩጥ ለመራመድ ቢሞክር እንደ ሰከረ ሰው ተንገዳገደ። ልጁ ተኝቶበት ወደ ነበረው ክፍል ሄደ። ሕሳቡ እንትልፍ መሰዶታል። መደዘራት ሂስተር ልጁን ለመጠበቅ ከአጠገቡ ቁጭ ብላለች። በእጁ ምልክት ሰለሰጣት ተያይዘው ወደ ሙሳ ወጡ።

«ባለቤቴ እኮ ጥሳኝ ሄደች» ብሎ ሲነግራት ሂስተር ደነገጠች። ስውነትዋም ተንተጠተጠ። በሕይወትዋ ሙሉ እንደዚያን ዕለት የደነገጠ ኾበትና የተብረከረከችበት ጊዜ ትዝ አያላትም።

«ጥላህ ሄደች! እርግጠኛ ነህ?» ብላ ስትጠይቀው «አዎን» አለ። «የሄደችውም በእንቺ ምክንያት ሳይሆን አልተረዳ፣ ማሰቱ ብራ ጠዋት በተናገርሻት» ሲላት ወይዘሪት ሂስተር በኩራት መንፈስ አንገትዋን ቀና አደረገች።

«ሚስስ ቡሩጥ እኔ በተናገርኩት ንግግር የተጎሳ ባልዋንና ልጅዋን ጥላ ትሄዳለች ብዬ አሳስብም።»

«ሄዳለች፣ የሕይወቱ ብርሃንም አብሮአት ሄዷል» ብሎ ሲናገር ወይዘሪት ሂስተር ሕሳቡን አያመለከተች «ወንድሜ፣ የሕይወትህ ብርሃን እሱ ነው» አለችው።

«የለም» ሲል መለሰ ጎዘን እየተሰማው፣ «እስከ ትናንትና ማታ ድረስ ማንም ሰው ቢጠይቀኝ በዓለም ላይ ካለው ነገር በሙሉ ልጄ ይበልጥብኛል ብዬ እመልስ ነበር። አሁን ግን ዳያንን ያህል የምወድደው ሰው እንደሌለ ተረዳሁ።»

«ታዲያ ርቃ አልሄደች» አለች ወይዘሪት ሂስተር፣ «አርግጥ ነው፣ ዛሬ ጠዋት በጣም ከፍድቷት ነበር። ግን እኔ እንተን ብሆን እስከዚህም በነገሩ አልጨነቅም። ደኅና የምትሆንበትንና የሚበጃትን በሚገባ ታውቃለች። አሁን የጠፋትው አንተን ለማስጨነቅና ለማስፈራራት ነው እንጂ ሲርባት ተመልሳ ትመጣ የለ! ስለዚህ ነገሩ ብዙም አያስጨንቅህ።»

«ከልብሽ ነው? የምትመለስ ይመስልሻል?» ሲል ሂስተርን ጠየቃት። መንፈሱ ትንሽ መለስ አለ።

«እርግጠኛ ነኝ። ሕሳን መሰልናት በዚህ የምንደነግጠው? ምክሬን ትቀበል እንደሆነ ሂድና ተኛ። ልጁን እኔ እጠብቀዋለሁ። ነገ ጣቶት ስትነሳ ደህና ሁኖ ታገኝዋለህ። ባለቤትህም ለቁርስዋ ስትል ትመጣለች ይኼኔ ከአንድ ሥርቻ ውስጥ ተወሽቃ ይሆናል።»

ሂስቱር የተናገረችው ሁሉ ከአንገት በላይ እንጂ ከልብዋ አልነበረም ወንድምዋ ተጨንቆ ስላየችው እርሱን ለማጽናናት ያለችው ነበር። እርሱም አሳብዋን ስለተቀበለ «ፈረሴን ጭኜ ፍለጋ ልሂድ ነበር» ይላል።

«ምን ማለትህ ነው? እብደሃል፣ ገና ሳይነጋ ፈረስህን ጭነህ ልትሄድ! ታሪክህ በመጥፎ ስም ከታሪክ መዝገብ እንዲሰፍር ከፈለግህ ጥሩ ነው» ስትለው ቡሩኖ፣ ሂስቱር ለተናገረችው መልስ ሳይሰጥ ወደ ክፍሉ ሄደ። በጣም ተጨንቆ ስለነበር የሚነጋ አልመሰለውም። ገና ከክፍሉ ሲገባ ሰውነቱ ሁሉ በይበልጥ ተረበሸ። ከመቃብር ቤት የሚገባ መሰለው። በዚህ ጊዜ «ዳያን» ሲል ጮኸ። ለዳያን የነበረው ፍቅር አገረሸበት። ዳያን ተመልሳ ከአጠገቡ እንድትሆን የነበረው ሰሜት እጅግ ጋለ። በትናት ተቃጠለ።

«የት ሄደች? ብትወድደኝ እኮ ጥላኝ አትሄድም ነበር» የሚል አሳብ ስለተቀረጸበት እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም። ጠዋት ጎህ ሲቀድ ለካስ አሸልቦት ኖሮ ስላታገሠው ይባንናል። «እንቅልፍ ወስዶኝ ነበር ማለት ነው?» ሲል ራሱን ጠየቀ። በሕለሙ ዳያን ከአበቦች መካከል በሚገኘው ቀጭን መንገድ ስትራመድ ተመለከተ። ከመንገዱ ዳርቻ ደግሞ አንድ ትልቅ ገደል መኖሩን አየ። የገደሉ አፋፍ በአበቦች ስለተሸፈነ ገደሉ በጉልህ አይታይም። ዳያን ገደል መኖሩን አለማወቅዋን ሲገነዘብ 'ተጠንቀቂ' ሲል ጮኸ። ዳያን ግን እርሱን ለማየትም ሆነ ለማዳመጥ አልፈቀደችም። «አንድ እርምጃ ብትራመድ መሄድዋ ነው» ሲል በድጋሚ በኃይል ጮኸ። ዳያን ጉዞዋን ቀጠለች። በፍርሃት ስትጮህና ወይኔ በማለት እጅዋን ለእርዳታ ስታውለበልብ አየ። ተስፋ የቆረጠውንና የገረጣውን ፊትዋን ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተ። ከዚያም ወርቃማው ጸጉርዋ ፊትዋን ሲሸፍንበትና ከገደሉ አዘቅዝቃ በመግባትዋ «ቡሩኖ» እያለች ስትጣራ በመስማቱ ደንግጦ ነው ብንን ያለው።

«ተመስገን በሕልሜ ነው» አለ። ሂስቱር ከአጠገቡ ቆማለች። «ቡሩኖ ምን ነካህ? ደኅና አይደለህም?» ብላ ስትጠይቀው «ስለዳያን መጥፎ ሕልም አየሁ። እንኳ ሂስቱር! እርግጠኛ ነኝ ዳያን አንድ አደጋ ደርሶባታል።»

«የማይረባ፣ አሁን ትመለሳለች። ዝም ብለህ አትጃጃል። እኔ አሁን የመጣሁት ሉረንስ በጣም እንደ ተሻለው ልንገርህ ብዬ ነው» አያለች

t.me/OLDBOOKSPDF

ሩሩጽናናውም ስለዳያን እየተከዘ ጥሉአት ከዘነጉሉ ወጣ.. ቀኑን ሙሉ ቢያይ ባለቤቱ አትመለስም። ወደ ምድር ቤት ወርዶ ቡና ሲጠጣ ኮሽታ በሰማ የሚሰቱ ኩቴ መስሉት ዞር ይላል። ሐኪሙ ልጁን ለማየት ነበር የመጣው።

«ልጁ ድኖአል» አለ ዶክተሩ። ሰው ከእንደዚያ ያለ ነጥብ ደርሶ ሲድን ሐኪሙ ያየበት ጊዜ በቁጥር ስለነበር የልጁን መዳን እንደ ተአምር ነው የቆጠረው። ይህ ተአምር ለሄስተር ትልቅ ትምህርት ሆኖ ከዚያን አለት ወዲህ ሐኪም ካላዘዘ በስተቀር ለበሽተኛ ያልታወቀ መድኃኒት እንደማትሰጥ አመነ።

«መደኃኒቱን ስለሰጠሽው የነቀፍኩሽን ያህል ላመስግንሽ። ለልጁ ሐኪም ያላዘዘውን መድኃኒት በመስጠትሽ ትልቅ ስሕተት ሠርተሻል ነበር። ግን ትእዛዜን ጠብቀሽ በሚገባ ስላስታመምሽው ሕይወቱን አዳንሽ። አሁን ሚስስ ቡሩኖን አስጠሩልኝና ላነጋግራት። ትናንት በልጅዋ መታመም የተነሳ ሕመምተኛ መስላ ነበር» ብሎ ሐኪሙ ሲናገር ወንድምና እህት እርስ በእርስ ተያዩ።

«ባለቤቴ ከዚህ የለችም» አለ ቡሩኖ፣ «ሆኖም ከአሁን አሁን ትመጣለች በማለት እየተጠባበቅናት ነው። 'ከልጁ አርቋት፣ አለበለዚያ ልቅሶዋና ዋይታዋ የልጁን ሕመም ሊያባብስ ይችላል' ባልከን መሠረት ልጁ ካለበት እንዳትደርስ አደረግን። ይህንንም ያደረግነው የሐኪም ትእዛዝ ለመጠበቅ ያህል ነበር። ዳያን ግን የክፋት መስሉአት እጅግ ተቆጣችን» ብሎ ታሪኩን ሲቀጥል «ከዚያስ?» ሲል ሐኪሙ ጠየቀ።

«ከዚያማ ከእኅቴ ጋር ትንሽ የማይሆን ቃል ተለዋወጡ መሰለኝ ቁጣዋ አልበርድ ብሎአት ቤትዋን ጥላ ሄደች።»

«ወይ ጉድ! መቼስ እንዴ ሆኖአል፣ የሆነውን እንዳልሆነ ለማድረግ አይቻልም። ትናንት ሳያት እጅግ እንደ ተጨነቀችና በጣምም እንደ ተከፋች ጠርጥሬ ነበር። ዜናው እንግዳ ነገር ሊሆንብኝ አይችልም። ተስፋ ስለቆረጠች ሁሉንም ነገር ጥላ መሄድዋ ነው» አለ ዶክተሩ። ዶክተሩ ይህን እየተናገረ ከነበረበት ክፍል ወጥቶ ሄደ። እኅትና ወንድም እፍረት ተሰምቷቸው አሁንም ይተያያሉ። ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ሆነ፣ ግን ዳያን አልተመለሰችም።

«አሁኑኑ ሂጂ ልፈልጋት» አለ ባልዋ።

ሄስተር አልተቃወመችም። ቡሩኖ ፈረሱን ጭኖ ጉዞውን ቀጠለ። ሚስቱን በመፈለግ ቀኑን እንዴት አንዳሳለፈ መዘርዘሩ እስከዚህም

የሚያስፈልግ አይደለም። ለሚቀጥሉት ቀናት ከዚያም ሰላምንት ግ
በመፈለግ ጊዜውን አሳለፈ። የሥራውና የእርሻው መታሳል የ
መነከን ስሜት አልሰጠውም። ዳያንን ብቻ ነበር የፈለገው። ለእርሱ ፈ
ሕይወቱ ቢያልፍ እንኳን ደንታ አልነበረውም።

ከሦስት ሳምንት ፍለጋ በኋላ ዳያን ከመንገድ ወድቃ ያነሳትን ት
ቶርቼን ያገኛል። ይህ ሰው ዳያን ታምማና ራስዋን ስታ እንዳገኘ
ገለጸለት። የሚስተር ቶርቼ ባለቤት ደግሞ እያለቀሰች ዳያን በጠፋ
ያለ ቁርስ መሄድዋንና «ልጄን ገድለውብኛል» በማለት እጅግ ማዘንዋ
ለቡሩኖ ነገረችው።

«ባለቤቴ ነበረች» አለ ቡሩኖ፣ «ጥፋቱ ግን የራስዋ ነው። ልጁ ሳይ
ሞት የሞተ መሰላት። ዓለም በሙሉ የእኔ ቢሆንና ዳያንን ባገኝ ዓለሙን
ሰጥቼ ዳያንን እመስድ ነበር» ብሎ ሲናገር «ወደ ለንደን ሄዳለች» ከማለት
በስተቀር ሌላ ፍንጭ ሊሰጡት አልቻሉም። ስለዚህ ቡሩኖ ዳያንን ፍለጋ
ወደ ለንደን ሄደ። ለንደን ውስጥ ከጸጥታ ክፍል ሄዶ አመለከተ። የጸጥታ
ክፍል ሠራተኞች ታሪኩን ካዳመጡ በኋላ ወደ አለቃቸው ወሰዱት
አለቅዮው የሚከተለውን ነገሩት።

«በእኛ በኩል ብዙም የምንረዳህ አልመሰለኝም። ሆኖም እንተ
የሚቻልህን አድርግ። ይህ ጉዳይ መቼም ብዙም ምስጢር ያዘለ ነገር
አይደለም። ጉዳይ ባጭሩ ስለእንዲት ቆንጆ ሴትና ሽማግሌ ባልዋ የተነገረ
ታሪክ ለመሆኑ ገብቶናል። ቢሆንም አንተ በበኩልህ የሚቻልህን ሁሉ
አድርግ፤ እኛም የቻልነውን ያህል እንሞክራለን።»

ለብዙ ሳምንታት ቡሩኖ በየመሥሪያ ቤቱ እየዞረ ባለቤቱን ይፈልጋል።
በመጨረሻ የሚያውቀው ሰው ሁሉ ፍለጋው ዋጋ የሌለው መሆኑን
ስለገለጸለት ውቃቢ ርቆትና ፍትሩን አምቆ፡ እንደ ተከዘና በአለፈው
ጊዜ የሠራው ስሕተት እንዳንገበገበው ወደ ቤቱ ተመለሰ። ከቤቱ እንደ
ተመለሰም «ዳያን እኮ ጥላኝ ጠፉች፡ ከእንግዲህ ደግሞ አትመለስም»
ብሎ ሲነግራት «አታላይ ሴት ናት» አለች እህቱ ሄስተር።

«በእኔና እኔን በሚዘመድ ሰው ሁሉ ላይ እፍረትንና ውርደትን አዝን
ባለች። በሕይወት ካለች ማግኘቴ ስለማይቀር እበቀላታለሁ። ያሰብኩት
ሁሉ እንደሚሳካልኝ ደግሞ ጽኑ እምነቴ ነው» ሲልም ቁጭቱን በቃላት
ተወጣ።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

የጋብቻ ቀለበት

ኔያን ከባቡር ጣቢያ እስክ ደረሰች «ገንዘብ ያስፈልገኛል» ብላ አላሰበችም። ወደ ከተማ ስትሄድና በሌላም ጊዜ ቡሩሞ ትንሽ ትንሽ ገንዘብ ይሰጣት ነበር። ሆኖም ገንዘብ የመቆጠብና የማጠራቀም ምኞት አልነበራትም። ነገር ግን ወደ ሳውትቤ ስትሄድ አንዳንድ ነገሮችን የመግዛት ፍላጎት ቢኖራትም ስትመለስ ሄስተር እንደምትቆጣት ስለምታውቅ ገንዘብ እያላት የምትፈልገውን ሁሉ ሳትገዛ ትመለስ ስለነበር የተረፋት ገንዘብ ቦርሳዋ ውስጥ ሳታውቀው ይጠራቀማል። ገንዘቡ ይጠራቀም እንጂ ምን ያህል ገንዘብ እንደነበራት ግን አታውቀውም።

ከባቡር ጣቢያ ደርሳ ቲኬት ለማስቆረጥ ቦርሳዋን ስትከፍት ብዙ ገንዘብ አገኘች። የገንዘቡ መጠን ከሙሉ ፓውንድ በላይ ስለነበር እጅግ ደስ አላት። በዚህም ለንደን ከተማ ውስጥ ምን እሆናለሁ የሚለው ጥርጣሬ ተወገደላት። ሰዓቱና ጊዜው እያለፈ ሲሄድ ባልዋና አጎቱ በእርስዋ ላይ ያደርሱት የነበረው ሥቃይና መከራ በጉልህ እየታየት ለእነርሱ የነበራትን ጥላቻ በይበልጥ አጎላው። ይህም እነርሱ ከነበሩበት ርቃ እንድትሄድ ገፋፋት። የመመለስ ስሜት ከሐሳብዋ ውስጥ ጨርሶ አልገባም። ይልቁንም ከእነርሱ በመራቅዋ የኩራትና የመንፈስ አረፍት ይሰማት ጀመር።

«አባቴን አመድደው ነበር፤ ግን ሞቷል። ልጄን አመድደው ነበር፤ እርሱም ሞቷል። ከእንግዲህ ወዲያ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ሌላ ሰው አልመድም» በማለት ለራስዋ ቃል ገባች።

ያቺ ምስኪን ይህንን እያሰላሰለችና ሰማይ ሰማዩን እያየች ጉዞዋን ቀጠለች። ካለፈው ትዝታ በስተቀር ሌላ ነገር አእምሮዋ ውስጥ ሳይገባ ለንደን ባቡር ጣቢያ ደረሰች። ከእዚያ ስትደርስ ግን ክፉኛ ባባች። ለመጠጊያ የሚሆን ቤት ወይም ዘመድ የላትም። ስለዚህ «የት ልሄድ? ማንን ልጠጋ፣ ምንስ ላድርግ?» በማለት ግራ ገብቶአት ተጨነቀች።

ወደ አውራው ጎዳና በወጣች ጊዜ ከአውራ ጎዳናው ላይ ሕዝብ ሲተራመስ ተመለከተች። ወንዶች አንገታቸው የተቆለመመ እስኪመስል ፊታቸውን እያዙሩ ያይዋታል። ሴቶች በአድናቆት ፈገጠው ይመለከትዋታል።

ከእንድ ሱቅ ገብታ ፊትዋን የምትሸፍንበትን ወፍራም ሻሽ ገዛች። ሻሽ ስታስር ጊዜ ያነጋገራት ሁሉ «መይዘሪት» እያለ ይጠራት ጀመር።

ማንም ሲመጣ ብዙ እግረ መንገዶች ብሎ ስልኩን እየከፈተ ጊዜ ወዳጋ ፈረንጆች እንደሚያደርጉት ሁሉ በቪዲዮ ሰም ሰጠ ሰጠ ሰጠ ሰጠ

ሙን ብዙ ስራሴ ሰም ሳውቅ ስትል አሰበች ፡ ዳያን ባልፎር ሰጠ መጠራትን አልወደደችውም። ምክንያቱም በዚህ ሰም ትጠራ ነበር። ይመን ተደሰተ በናቅር አበር የምትኖረው፡ ሙሽራው ሚስት ልጅሙ ሰ አበር ብዙ የመራችው፡ ብዙ ራሱዋን ከመሰቀቅ በኋላ «ልጅን ጀብን ቀና አው፡ የእኔም ሰም ጀብን ቱርፔ ይሆናል» ስትል ወሰነች። ሰምዋን በመጠ ዋም የእስፈሙን የሥቃይና የመከራ ኦሮ ትዝታ አምዝግዝጋ ሳጎደ የሙት ልጅዋ ትዝታ ግን ከጎሲናዋ ሲወጣ አልቻለም። እንግዲህ ስምዋ ለመሰወርና ባልዋንና ቤትዋን ለመርሳት ስትችል ሌላው ለመርሳት ከሙንትላትዋ ውስጥ ለማስወጣት ያልቻለችው የጋብቻዋ ሰንሰለት ኦሮ ቡሩናን ብትወሳውም ሰማንያኛው ሰላልወረደ ሚስቱ ናት።

«ወይ ጣጣ፡ የማይለት እድፍ፡ የማይበጠስ ሰንሰለት» ስትል ተናገረች በዚህም ተስፉ ከመቁረጥ ሌላ ምንም ምርጫ አልነበራትም። «ግድ የለም» አለች ዳያን፡ «ከዚህ በኋላ ሳዝንና ታጋሽ ሴት እሆናለሁ። ቀደም ሲል ሳዝንና ብርቱ ታጋይ ለመሆን ብሞክርም ሳይሳካልኝ ቀረ። አሁን ግን ላርችዲል ውስጥ አያሁን እንጂ የትም ቢሆን ሥራዬን በትጋትና በብሪቱ እሠራለሁ። ችግሬንም በጉብዝና እሸከማለሁ። ከሄስተርና ከቡሩኖ ሌላ የማንንም ትእዛዝ አተበላለሁ። የማንንም አሸክር ሁኜ አገለግላለሁ» በሚል ራሰዋን መከረች

እና ዳያን በሕይወትዋ ለሁለተኛ ጊዜ ሰሕተት ትፈጽማለች። ግን ይሀን ለሠተት እንዳትፈጽም ያበተማራት ሰው አልነበረም። ዳያን በለንደን ከተማ አውራ ጎዳና ላይ ከበታ ቦታ ሥረች። እጅግ ደክሞአት ስለአበር ላታውቀው በድንገት አገርችዋ ተነስረው መገሉላሉበ ተነናቸው። በዚህ ጊዜ እህል ከቀመስች ሁለት ቀንዋ መሆኑ ታወላት። እዚያው ከነበረችበት እንደ ቆመች ከፈን ሰፊትዋ አንዲት ትንሽ ቡና ቤት አየች። ከቡና ቤቱ ገብታ ሻይ አዘዘች። ሻዩ ቀርቦላት ስትጠጣ ሰውነትዋ ትንሽ መለስ አለላት።

«እዚህ ለግደር እችላለሁን» ቦነ ሰትጠይት ያገኘችው መልስ «በደስታ ወይዘሪት» የሚል ነበር።

«እንግዲያውስ ከፍሌን በቶሎ አባዩኝ» አለች ዳያን። «ከሩቅ አገር ስለመጣሁ በጣም ደክሞኛል። በውነቴ ሁሉ ዝሎአል»

«ያመመሽ ትመስያለሽ ወይዘሪት» አለች ያስተናገደቻት ሴት።

«እንደገና ወይዘሪት እያለች ጠራችኝ እኮ» ስትል ጸያን አሰበች። አሳላፊዋ ተመልሳ ለጸያን እራት ስታቀርብ ስምዋን ጠየቀቻት።

«ዘወትር የእንግዶቻችንን ስም ከመዝገብ ላይ እናሰፍራለን። ይህም ከሆቴላችን ጣን እንዳደረ ለማመሳከር ይረዳናል» በማለት ስምዋን የጠየቀችበትን ምክንያት ገለጸችላት።

«ስሚ ወይዘሪት ቱርቼ ነው» ስትል ጸያን መለሰች። አሳላፊዋ ተደንቃ ጸያንን ቀና ብላ አየቻት።

«ይቅርታ አድርጊልኝ በትጡ አልሰማሁሽም» ስትላት «ወይዘሪት ቱርቼ» በማለት በድጋሚ ስምዋን ነገረቻት። በዚህ ጊዜ አሳላፊዋ በመጀመሪያ ፊትዋን ፈገግ አድርጋ ከተመለከተቻት በኋላ ትሰቃለች።

«ምናልባት እንግሊዛዊት አትሆኝ ይሆናል ወይዘሪት» ስትላት «እንግሊዛዊት! ኑኝ እንጂ፣ ምነው?» ስትል ጸያን ጠየቀች።

«ምክንያቱም» አለች አሳላፊዋ፣ «እንግሊዝ አገር ውስጥ አንዲት ሴት የጋብቻ ቀለበት ካሠረች በኋላ ወይዘሮ እንጂ ወይዘሪት ተብላ አትጠራም።» የጸያን ፊት በድንጋጤ ተለዋወጠ። ግን አሳላፊዋ ሰውጡን ሳትገነዘብ ወጣ ሄደች።

«እንኳንም ደፍሬ ነገርኳት። በጣም የተዋበች ሴት ናት። እመቤቴ ይህን ቢሰሙ ከዚህ ቤት አያሳድርዋትም ነበር። አርሳቸው እንደሆነ ተፈጥሮአቸው ሆኖ እንደዚህ ያለውን ጥቃቅን ነገር አንኳን ቢሆን ሰምተው እንጸልሰማ ሆነው ማለፍን አይወድዱም» እያለች አሳላፊዋ ብቻዋን እያጉረመረመች ነው የሄደችው።

ጸያን የጋብቻ ቀለበትዋን አተኩራ ተመለከተች። ምን ታድርግው? ከወርቅ የተሠራ የጋብቻ ቀለበት አድርጋ ትዙር? የለም አይሆንም። አሳላፊዋ እውነትዋን ነው፤ አንዲት ሴት የጋብቻ ቀለበት ካሠረች ወይዘሪት ተብላ አትጠራም። ታዲያ ቀለበቱን ታውልቀው? ቀለበቱን ያጠለቀችበትና ከሞት በስተቀር የሚለየን የለም፣ በማለት የገባችው ቃል ኪዳን ከፊትዋ ድቅን አሉ። ቃል ኪዳኑን ለመሻር ሥልጣንና መብት አላት?

ሳታስበው በድንገት «ቀለበቱን አድርጌ አልሞርም» ስትል ፎክ ብላ ተናገረች። ከጣትዋ ላይ አወለቀችው። «በምናምን ከሰርኩና ከጠቀስኩት በኋላ አመልስለታለሁ» አለች ለራስዋ።

እውነትም እንጸለችው ቀለበቱን ለባልዋ ላከችለት። ቤትዋን ለቅቃ

በወጣች ልክ በወሩ ቀለበቱን የያዘ ፖስታ ላርችዬል ደረሰ። ሆኖ ቀለበቱ እንደ ደረሰ ሄስተር ለቡሩኖ አላሳየችውም። ከጥቂት ጊዜ በ ግን ትሰጠዋለች። ቡሩኖ ብርሃን ካለበት ሄዶ የሚሰጠን የጋብቻ ቀ አተኩሮ ተመለከተው። «እሞን» አለ፣ «የዳያን የጋብቻ ቀለበት ነ እንድ ቀን ስጡሪዳት ለምስክርነት አቀርበዋለሁ» ሲል ለራሱ ነገረ

በሚቀጥለው ቀን አሳላፊዋ ዳያንን ስታይ ፈገግ ትላለች። ከዳያን ግ ላይ ቀለበት አልነበረም። «ጥቆማዬ ሠራ» ማለት ነው ስትል አሰላሰለ ያን እለት ጠዋት ዳያን ስትነሳ ቀለል ብሎአት ተነሳች። የራስዋ አዛዥ ተቆጣጣሪ ሁና በመገኘትዋ እጅግ ደስ አላት። «ይሀን አትልበሽ፣ ያን አታደርጊ» ብሎ የሚቃወምና የሚያናድድ ሰው ካጠገብዋ ባለመኖሩ ነፃነትዋን ያገኘች መሰላት። ሆኖም የልጅዋ መሞት ትዝ እያላት ተደሰተ እንዳትኖር እንቅፋት ሆነባት።

«ከእስር ቤት ከተለቀቀ ሰው ይበልጥ ትስሚ የተሰበረ ነው። ያንነ ሕይወት ኑሮ ብዙ መቀመጫ ምንኛ ሞኝ ብሆን ነው?» ስትል ራስዋን ጠየቀች። ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ የወጣትነት፣ የመንፈስ መታደስ የመሻሻል፣ የተስፋ ምልክት ይታይባት ጀመር። ያ ያልተባረከ ጋብቻ ምንኛ የጨለመ እንደ ነበር እያሰላሰለች ጋብቻው በማክተሙ እጅግ ተደሰተች። ከፊትዋ ለፊትዋ የተደቀነው ችግር የኑሮን ትግል መቋቋም ብቻ ሆነ።

እንዴት ብላ ኑሮዋን እንደምትመራ ታሰላስል ጀመር። ኑሮን ለማሸነፍ ከመታገልና ከመጋፈጥ በስተቀር ሌላ ምርጫ እንደሌላት ተገነዘበች። «እንዴት ነው የኑሮን ትግል የምጋፈጠው?» እያለች ደጋግማ ራስዋን ጠየቀች። የእለቱ ጋዜጣ ከፊት ለፊትዋ ቁጭ ብሎአል። እያንዳንዱን ዓምድ ተመለከተች። ክፍት የሥራ ቦታ የሚል ማስታወቂያ እንዳለ ፈለገች። ፍለጋዋ መና ሆኖ አልቀረም። ክፍት የሥራ ቦታ የሚል ማስታወቂያ ስለነበረ ያንን አየች። ሥራው ከቢት ውስጥ ሕፃናትን ማስተማር ሲሆን ሠራተኛ የፈለጉ ሰዎች ስልክ ቁጥር በማስታወቂያው አልተገለጠም። ስለዚህ በአድራሻቸው ማመልከቻ ከመላክ በስተቀር አማራጭ አልነበራትም።

ዳያን ባልዋን ጥላ ብትሄድም ባል ማግባትዋን ግን አልረሳችም። ሆኖም ከወንዶች በሙሉ መራቅ እንዳለባት ትገነዘባለች። መጀመሪያ ማድረግ ያለባት የተከበረ ግቢ ፈልጋ ቤት መከራየትና ሥራ ማጠያየት ሲሆን የሆቴል ቤቱን ሒሳብ ከፍላ የሚከራይ ቤት ፍለጋ ወጣች። ተስማሚ የሆነ ጥሩ ባለሁለት ክፍል ቤት በደኅና ዋጋ ኪንቲሽ ታውን ከተባለ ሥፍራ አገኘች። ከዚያም ለራስዋ ጥቁር ልብስ ገዛች።

«ለምንድነው የጎዘን ልብስ የለበስሽው ተብዬ ብጠየቅ ልጁ ስለ ሞተብኝ ነው ለማለት አልችልም፣ አባቱ ነው ብል ይሻላል» አለች ጸያን እርስ በራስዋ ስትነጋገር። «ጥቁር ልብስ ደግሞ ኮስተር ያለች አሮጊት ያስመስለኝ ይሆናል» ስትልም አሰበች። ቢሆንም የጎዘን ልብስዋን ስትለብስ «አሮጊት መስዬ እታያለሁ» ብላ የተመኘችው አሳብ ልክ አልመጣላትም። ምክንያቱም ቆንጆ ፊትዋንና ወርቃማ ጸጉርዋን በመስታወት ስትመለከት እንዲያውም ከነአካቴው ልጅ መስላ መታየትዋን አረጋገጠች።

ማስታወቂያውን ወደ አስወጣው ወኪል መሥሪያ ቤት ሄደች። የመመዝገቢያ ሂሳብ ስትከፍል አንዲት ሴት በአድናቆት ስትመለከታት አየች። ፊት ሳትሰጣት ስምዋንና አድሜዋን አስመዘገበች። ስምዋ ሄለን ቮርጌ፣ አድሜዋ አሥራ ስምንት ዓመት።

«አድሜሽ ለሥራው ተስማሚ ይሆናል ተብሎ ከተገመተው እድሚ በጣም ዝቅ ያለ በመሆኑ ሥራውን ለማግኘት ያለሽ እድል ዝቅተኛ ነው» አለች ኃላፊዋ።

ጸያን ስለችሎታዋ ስትጠየቅ «ፈረንሳይኛ በደምብ ለመናገር ስችል ጣልያንኛ ያደግሁበት ነው። በሥእል ደግሞ ጎበዝ ነኝ» በማለት ገለጸች።

«ሙዚቃስ?» ብለው ሲጠይቋት «በእሱ እንኳን እስከዚህም አይደለሁም» ባለች ጊዜ «ይህማ ጥሩ አይደለም። ሙዚቃ ለሥራው ከሚፈለጉ ችሎታዎች አንዱ ነው» ካለች በኋላ «ተጠሪ ማለት ስለአንቺ የሚጠየቅ ዘመድ ወይም ወዳጅ ስም ብትነግሪኝ?» ብላ ሴትዮዋ ጠየቀቻት። በዚህ ጊዜ ጸያን በጣም ደነገጠች።

«ከዚህ በፊት ከቤተሰብ ተለይተሽ ርቀሽ ሄደሽ ታውቂያለሽ?» ስትል ሴትዮዋ ሌላ ጥያቄ ጠየቀቻት።

«በፍጹም» በማለት ጸያን በአጭሩ መለሰች።

«እሺ ብቻ ለማንኛውም ብዙ ሴቶች እኔን ለማነጋገር ይጠብቃሉና መልካም ፈቃድሽ ከሆነ የተጠሪሽን ስም ብትነግሪኝ።»

«ስለእኔ የሚጠየቅ ወይም ስለእኔ የሚዋስ ዘመድ ወዳጅ የለኝም» አለች ጸያን።

«የለሽም?» ስትል ኃላፊዋ በድጋሚ ከጠየቀቻት በኋላ ቀና ብላ አየቻት። «አንድ ሰው ማወቅ አለብሽ። ለምሳሌ አስተማሪሽ፣ ጎረቤትሽ ወይም ማንኛውም ዘመድ፣ ጓደኛ — ከዚህ ሁሉ እንዴት አንድ ሰው ይጠፋል! ሌላ ቢቀር አንቺንና ስለአንቺ ጠባይ የሚያውቅ አንድ ሰው

መኖር አለበት። ይህ ሰው ምናልባት ይህች ልጅ በከብር ያደገችና በጎ ጠባይ የታነጸች ናት ብሎ ሊመስክር ይችል ይሆናል» በማለት መንገዱን ሰጠችት።

«እሱማ የተከበርኩ ነኝ፣ አስተዳደጌም ከጥሩ ቤተሰብ ነው» ብዙ ስትመልስ «አምን ልትሆኚ ትችያለሽ፣ ይህን እኔም አልክድም። ግን ግንኙ ቢሆን በቃል ብቻ ሊያምንሽ አይችልም። ስለዚህ አንቺን የሚያውቅ ሰው ስለሚያስፈልግ የአንድ ሰው ስም ብትነግሪኝ ጥሩ ነው» ተባለች።

«አላገኝም» አለች ዳያን። «ስለእኔ ያውቃል የምለው ሰው በከተማው ውስጥ የለም። እኔ የኖርኩት ከአባቴ ጋር ነው። አባቴ ሠዓሊ ስለነበር ፈረንሳይና ጣሊያን አገር እንደዚሁም እዚሁ አገራችን ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወርን ነው የኖርነው። ከአንድ ቦታ ረዘም ላለ ጊዜ ስላልተቀመጥን ማንንም አላውቅም።»

«ሠዓሊ አልሽ? ስሙ ራሱ ተጠሪ ሊሆንሽ ይችላል። አባትሽ የታዘቀ ሠዓሊ ነበር?» ብላ ስትጠይቃት «አዎን» ካለች በኋላ «አባቴ በመጨረሻ የሳላቸው ሦስት ሥዕሎች እንኳን ሮያል አካዳሚ ከተባለ ሥፍራ ለሕዝብ ታይተው ለአባቴ ዝናን አትርፈውለታል» ስትል መለሰች።

«በዘመኑ የታወቁ ሠዓሊዎችን የማውቅ ይመስለኛል። ግን ከእነዚህ ሠዓሊዎች መካከል ቶርፔ የሚባል ስም ትገ አይለኝም» ስትላት የልጅትዋ ፊት ሳታውቀው ተለዋወጠ። እውነቱን አውጥታ ስሙ ባልፎር እንደ ነበር ለመናገር ፈለገች። ግን እውነቱን ያወጣች እንደሆነ መጥፊያዋ መሆኑን ስለተገነዘበች ከምላስዋ ጫፍ ደርሶ የነበረውን ቃል ዋጠችው።

«ይህ መቼም ሥራውን ለማግኘት የነበረሽን እድል እጅግ ይቀንሰዋል። ሆኖም ልትሞክሪ ትችያለሽ። ይኸውልሽ እዚህ ሳይ የሰፈረውን የስም ዝርዝር ተመልከች» በማለት የሠራተኛ ፈላጊዎች ስም ዝርዝር አድራሻ አቀረበችላት። ዳያን ዝርዝሩን ስታነብ አመቤት ብላይቶርን፣ ሚስስ ሐውተንና መዳም ደንስቢ የሚል ስሞችን አየች። «እነዚህን ሁሉ በየቢታቸው ማነጋገር አለብኝ ማለት ነው» ስትል ዳያን ኃላፊዋን ጠየቀች።

«አምን፣ እነዚህ ሦስት ሴቶች ለልጆቻቸው አስተማሪ ይፈልጋሉ። አመቤት ብላይቶርን አንዲት ልጅ ብቻ ናት ያለቻቸው። ሚስስ ሐውተን አራት ልጆች ሲኖሯቸው ሁለቱ ወንዶች ናቸው። ወንዶቹ ልጆች ትንሽ አስቸጋሪዎች ናቸው ይባላል። መዳም ደንስቢ ሁለት ልጆች ያልዋቸው ይመስለኛል። ወይዘሪት ቶርፔ መልካም እድል እንዲገጥምሽ እመኛለሁ» ብላ መልካም ምኞትዋን ስትገልጥላት ዳያን እጅ ነስታ ከሲተዮዋ ቢሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጥታ ሄደች።

«በትድሚያ እመቤት ብላይቶርንን ብሞክር ይሻላል» ብላ በማሰብ እመቤቲቱ ከሚገኙበት ሚፈር ከተባለ ሥፍራ ሄደች። ከዚያም ለአንድ ደቂቃ ያህል ከቤቱ በራፍ ከቆመች በኋላ አንድ ሰው ስምዋን ይጠይቃታል።

«እሜቴ ስላሉ የእርሶን ስም ማን ልበል?» አለ ሰውዬው።

«ወይዘሪት ቱርዜ፣ የመጣሁት ከመጸም ሲልቨር ቢር ነው።»

«አሃ! ሥራ ጠያቂ መሆንዎ ነው። ከጠዋት ጀምሮ ቢቆጠር አርስዎ አምስተኛዋ ሴት ናት» ካለ በኋላ ለእመቤቲቱ ሊነገር ወደ ውስጥ ወጥቶ ወዲያው ተመለሰ።

«እሜቴ ሊያነጋግሮት ፈትደዋል። መልካም ፈቃድም ቢሆን ይከተሉኝ።» ዲያን ሰውዬውን ተከትላ ወደ ቤት ጠጣች። ከፍሉ በአበባና በትርጻ ትርጽ ያጌጠ ሲሆን ከፊት ለፊት ለመናፈሻ የሚሆን ሰፊ ሰገነት አለ። ሰገነቱ ላይ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ተሰትለዋል። ሰውዬው አንድ ሳሳ ያለ መጋረጃ ሲገልጥ ከዚያ ውስጥ እመቤት ብላይቶርን ተጭው ብለዋል። ቤቱ አጅግ ማራኪና ለመርገጥ የሚያስፈራ ስለነበር ዲያን በአድናቆት ብዛት ፈዘዘች።

«ጠጋ በይ! ብርሃን ወዳለበት ብትሂጅና በደምብ ባያሽ እወድዳለሁ» ሲልዋት እመቤቲቱ ዲያን ቀሰ ብላ ወደፊት ተራመደች። ይህን በምታደርግበት ጊዜ ፊትዋ ቀላ፣ እንደ ማፈርም፣ እንደ መደንገጥም አደረጋት።

«አሁን ከልብሽ ነው? እውነትም ከእኔ ቤት ለመቀጠር ትፈልጊ ያለሽ?» ብለው እመቤቲቱ ሲጠይቋት «አምን አፈልጋለሁ» አለቻቸው።

እመቤቲቱ ተፈጥሮ በሰጣቸው ሳይሆን ሰው ሠራሽ በሆኑ ብልጭልጭ ነገሮች ከሚገባው በላይ አጊጠዋል። ፊታቸው ፖውደር ተቀብቶ ዓይናቸው ተኳኩሉአል።ትንድባቸው ተሳስቦ በቀለም ተነክሮአል። ሰው ሠራሽ ጸጉር አጥልቀዋል። በተጨማሪም ሴቶች ከሚያደርጉት ጊጥ አንድም የቀረ አይመስልም። ስለዚህ የሴትዮዋ ሁኔታ ለዲያን ፈጽሞ እንግዳ ነበር።

«ቆም በይ እስቲ!» አሉ ሴትዮዋ «መኪኪያሽን የት ነው የምትገ ዝው?» ብለው በጠየቅዋት ጊዜ «መኪኪያሽ» አለች ዲያን፣ «አልገባኝም።»

«በአንቺ እድሜ ካሉት ጋር ሲወያዩ አንድ ነገር ሳይገባቸው ቀርቶ እንዲገባቸው ማድረግ ዘወትር ችግር ይፈጥራል። መኪኪያሽ ያልኩት ፊትሽን በምንድነው የምትታጠቢው ማለቴ ነበር» አልዋት።

«በቀዝቃዛ ውኃ ነው የምታጠበው» አለቻቸው።

«ቀዝቃዛ ውኃ! ቀዝቃዛ ውኃ ያንቺን ፊት የመሰለ ውበት ሊ
እይችልም:: ፊትሽን የምትቀቢው ነገር ካለ ንግሪኝ» ብለው ሲያሳጥነ
«ከቀዝቃዛ ውሃ በስተቀር ሌላ የምጠቅምበት ነገር የለም:: እንዲያ
ቆዳዬ ውበት እንዳለውና ቆንጆ መሆኔን አስከ ዛሬ አላውቅም ነበ
በማለት በገርነት መለሰች::

«አላውቅም ነበር!» ስትል ሴትዮዋ በማፈዝ ያጉረመርማሉ... «እንኒ
ተፈጥሮ የቸረሽን ውበት አታውቂም? ግን ቆንጆ ነሽ አላልኩም፣ ብያለ
እንዴ?» ብለው ሲናገሩ «ኧረ የለም» ስትል ጻያን ፈጥና መለሰች.

«ጥሩ፣ አሁን ስለሥራው ብንነጋገር ይሻላል» አሉ አመቤቲቱ::

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

«ተያዥ ሽ ማነው?»

«አሁን ስለሥራው እንነጋገር» አሉ አመቤቲቱ:: «አንዲት ልጅ
ብቻ ናት ያለችኝ:: በልጂ መልክ እስከዚህም ስለማልኩራራ በትምህርቷ
እንድትበረታልኝ አፈልጋለሁ:: በፈረንሳይኛ ለጭር ጽሑፍ አንብቢልኝ
እስቲ» ሲልዋት ጻያን በፈረንሳይኛ የተጻፈ አንድ ልብ ወለድ መጽሐፍ
አነሳች:: ደሰ በሚል ድምፅ ስታወርደው ፈታኝዋ በጣም ያደንቅዋታል::

«በጣም ጥሩ ነው» አሉ ሴትዮዋ:: «አሁን ደግሞ ትንሽ ጣልያንኛ
ብታስሚኝ::» ለበለስ ባለ ድምፅ ጣልያንኛውንም ስታወርደው ከከንፈር
ችዋ ማር ጠብ የሚል ይመስል ነበር::

«ሥእልስ?» ብለው ሲጠይቅዋት «አባቴ በሥዕል ጎበዝ ነሽ ይለኝ
ነበር» ባለች ጊዜ «አባትሽ ደግሞ ስለሥእል ምን ያውቅ ኖሯል?» ሲሉ
በንቀት መልክ መልሰው ጠየቋት::

«ሠዓሊ ነበር» ብላ ጻያን ስትነግራቸው «እንግዲያውማ አንድ
ያልታወቀ ሠዓሊ መሆን አለበት:: ቶርፔ የሚባል የሠዓሊ ስም ጨርሶ
አይታወሰኝም» አልዋት:: ስለጻያን አባት የሥዕል ችሎታ ከተነጋገሩ
በኋላ አመቤት ብሳይቶርን የሚከፍሏትን ሲነግርዋት የገንዘቡ መጠን ብዙ
ስለነበር ጻያን ምንም ሳታቅማማ ተስማማች::

«አሁን እንግዲህ አንድ ነገር ብቻ ይቀረናል:: ይኸውም ስለማንኛውም
ነገር ተያዥ የሚሆንሽ ሰው ስም ነው::»

«ተያዥ የሚሆነኝ ሰው የለኝም» አለች ጸያን። «ከሕይወቴ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፍኩት ከአባቴ ጋር ከቦታ ወደ ቦታ በመዘር ስለሆነ ስለእሱ ችሎታም ሆነ ጠባይ የሚያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም።»

«ሌላ የምጨምረው ወይም የምጠይቅሽ ነገር የለም። መጸም ሲልቨር ማለቴ ወደ እኔ የላክችሽ ሴት ናት የምትለያው። ተጠሪ የሊላትን ልጅ ወደ እኔ መላኳ እንደ ስድብ ነው የምቆጥረው። ደኅና ሰንብች፤ ልትሄጂ ትችያለሽ» አሉ እመቤቲቱ።

ጸያን በጣም ደነገጠች። ልብዋን ከሁለት የሰነጠቁባት መሰላት። ከቤቱ ስትወጣ ፊትዋ ሁሉ በድንጋጤ ቱላ። ግን ተስፋ አልቆረጠችም።

«በዚህ ተበሳጭቼ ወደ ኋላ አልልም፣ ወይዘሮ ሐውተንን ደግሞ እሞክራለሁ» ብላ ጸያን ጉዞዋን ወደ ወይዘሮ ሐውተን ቤት ተጠለች። ከወይዘሮ ሐውተን ቤት እንደ ደረሰች አንዲት ሴት ምን እንደምትፈልግ ጠየቀቻት። ጸያን የምትፈልገውን ስትናገር እመቤቲቱ ከነበሩበት ከፍል ወሰደቻት።

ወይዘሮ ሐውተን የሥራ ፈላጊዋን ጥያቄ ከሰሙ በኋላ ስለችሎታዋ አንድ በአንድ ጠየቋት። የጸያን የትምህርት ደረጃ በቂ ሆኖ ስላገኙት ሴትዮዋ በችሎታዋ የተደሰቱ መሆናቸውን ገለጹላት።

«ከመስማማት የሚያግድን ነገር ያለ አይመስለኝም። እስከ ዛሬ ብዙ ሴቶችን አነጋግራለሁ፣ ግን እንዳንቺ የተስማማኝ አላገኘሁም። ከአንግዲህ የሚያስፈልገው ተያዥና ስለአንቺ የሚጠየቅ ተጠሪ ብቻ ነው። ስለዚህ ስለአንቺ የሚጠየቅ ተጠሪ ይሆነኛል የምትዪው ሰው ማነው?» በማለት ያው ከመጀመሪያዋ ሴት ቤት ሥራ እንዳትገባ አንቅፋት የሆናት ጥያቄ ተመልሶ መጣ። ጸያን እንደ ልማድዋ በድንጋጤ ፊትዋ ይቀላል።

«ተጠሪ የሚሆን ዘመድ የለኝም» ስትል በዝግታ መለሰች።

«ተጠሪ የሚሆን ዘመድ ወይም ወዳጅ የለሽም? እንግዲያውማ ወ/ት ቱርቴ ለምንድነው የምታስቸግሪኝ ብዬ ልጠይቅሽ?» ይልዋታል።

«ለመጸም ሲልቨር አንኳን ነግሬያት ነበር» ስትላቸው «ምን ብለሽ ነው የነገርሻት?» ሲሉ ጠየቅዋት።

«አባቴ ውዓሊ ነበር። ከእርሱ ጋር ከቦታ ወደ ቦታ ስዞር ነው የኖርኩት። ከአንድ ሥፍራ ለረጅም ጊዜ ተቀምጠን አናውቅም። አባቴ ትምህርቱን የተከታተለው ጣልያንና ፈረንሳይ አገር ውስጥ ነው። እዚህ እንግሊዝ አገርም ቢሆን ለሥዕል ሥራ የሚያመች ሥፍራ እየፈለገ ከቦታ ወደ ቦታ

እየዞረ ነው የኖረው:: በዓለም ላይ የነበረኝ ወዳጅና ዘመድ አርሱ ነበር:: ታዲያ እሱም ሞቷል» በማለት ታሪክዋን ዘረዘረች::

«ስለብቸኝነትሽ አዝናለሁ» አሉ ወይዘሮ ሐውተን:: ሆኖም እንኳ እምኜና ቃልሽን ብቻ ተቀብዬ ልጆቼን ልሰጥሽ አልፈቅድም ሰንብቺ» ሲልዋት ዳያን ልብዋ ቆስሉና መላ ሰውነትዋ በኀዘን ተ ከወይዘሮ ሐውተን ቤት ወጥታ ሄደች::

«አንድ ሰው ማነጋገር ብቻ ነው የቀረኝ:: ይህኛውም ቢሆን የለውም:: እርግጠኛ ነኝ፣ ከመዳም ደንስቤ ዘንድ መሄድ አይኖረውም» ስትል አሰበች:: ሆኖም «መሞከር አለብኝ» በማለት ሰትዮዋ ቤት ተጓዘች::

መዳም ደንስቤ ከቤት ውስጥ ሁነው «መዳም ሲልቨር ሥራ ላ ሳትልክ አትቀርም» በማለት እየተጠባበቁ ነበር:: ዳያን ከሰትዮዋ ቤት እንደ ደረሰች እጅግ በጣም ወደ ተዋበ ክፍል ይመሰጃታል:: የነፍሰ መስኮቶች ስለተከፈቱ አካባቢው ወለል ብሎ ይታያል:: ወዲያው የቤቱ እመቤት ዳያንን በፈረንሳይኛ ጽሑፍ እንድታነብ ይጠይቋታል:: ዳያ አነበበች::

«ፈረንሳይ አገር ኖረሻል ወይስ የፈረንሳይ ደም አለብሽ?» ብለው ሲጠይቋት ዳያን «እናቴ ፈረንሳዊት ነበረች» ስትል መለሰች::

«እኔም ጠርጥሬአለሁ:: በፈረንሳይኛ አነጋግሬኝ:: የድምፅሽ ለዛ እጅግ ደስ ይላል::»

ዳያንና እመቤቲቱ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ሲጨዋወቱ ሴትዮዋ ሁለት ትንንሽ ልጆች ስላልዋቸው እነዚህን ልጆች የሚያስተምርላቸውና የሚጠ ብቅላቸው ሰው እንደሚፈልጉ ገለጹላት::

«ብቸኛ ነኝ» አሉ መዳም ደንስቤ:: «ባለቤቴ ብዙውን ጊዜ ከቤት አይቀመጥም:: ብዙ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ የእንግሊዝ ሴቶች ብርቱዎች ናቸው:: ሊደንሱ፣ ሊዘምሩ፣ ፈረስ ሊጋልቡ፣ መኪና ሊነዱና ሳይደክማቸው ብዙ ሊጫወቱ ይችላሉ:: እኔ ግን ደካማ ሴት ስለሆንኩ ይህን ሁሉ ለማድረግ አልችልም:: በዚህም የተነሣ ብቸኝነት ስለሚያጠቃኝ የሚያጫውተኝ ሰው በኃይል እፈልጋለሁ» በማለት መዳም ደንስቤ ችግራቸውን ያዋይዋታል::

«እርስዎ የፈለጉትን መፈጸም ይችጠኛል» ብላ ዳያን ከመለሰች በኋላ «አሁንስ በመጀመሪያ ዋስ የሚሆነኝና ስለእኔ ማንነት የሚናገር ሰው እንደሌለኝ በቅድሚያ እኔው ራሴ እናገራለሁ» ስትል ታስባለች:: «መዳም ደንስቤ» አለች ዳያን፣ «አንድ በቅድሚያ ልገልጽልዎት የምፈልገው ነገር

አለኝ። ይኸውም ሰለእኔ ዋስ የሚሆነኝ ዘመድ ወይም ወዳጅ እንደሌለኝ ነው። ከአባቴ ጋር ከሆኑ ወደ ቦታ በመዘዋወር ከጣልያን፣ ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ አገር ውስጥ ነው የኖርነው። ከእነዚህ ከተለያዩ ሥፍራ ስንቀመጥ ከእንድም ቦታ ለረጅም ጊዜ አልቆየንም። ሰለዚህ ሰለእኔ የሚጠይቁት ወይም ተያቫር የሚሆነኝ እንድም ሰው ባለማወቁ አዝናለሁ።»

መጻም ደንስቢ ሳት ይላሉ። «ገርንት ያጠታሻል ልበል። የልብሽን ግልጥልጥ አድርገሽ ነው የምትናገሪው። እንቺን የመሰለ ልጅ ተጠያቂ ዘመድ አያስፈልጋትም። ተፈጥሮ ጠባያሽን ከፈትሽ ሳይ በግልጽ ጽርታል» ሲልዋት የዳያን ልብ አመታት ከጥ አለ። የምትሰማው ነገር እውነት አልመሰላትም።

«ደግ ሰው ኖት» አለች። «እምነትም ከአጉል ቦታ አለመውደቁን አሰ መስክራለሁ» ስትላቸው «ይህን አልጠራጠርም» ይላሉ መጻም ደንስቢ። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው በሩን ከፍቶ ይገባል።

«እንደምን አደርሽ የኔ ፍትር» ሲል ሰላምታውን እጅ በመንሳት ካቀረበ በኋላ ዳያንን በአድናቆት እየተመለከተ አፈጠጠባት። ዳያን እንደ ማፈር ብላ ፊትዋን አዞረች። በዚህ ጊዜ ሰውዬው መደ ባለቤቱ ፊቱን ይመልሳል።

«ይህቺ ደግሞ ማን ናት? መልእክ ወይስ ሰው? የእኔ እመቤት አታስተዋውቂኝም?» ሲል የመጻም ደንስቢ ባል በልጅትዋ ውበት ተደንቆ ባለቤቱን በተልድ መልክ ይጠይቃል። ባለቤቱ የትናት ስሚት አድርባቸው ፈታቸው ሲለዋወጥ ዳያን ተመለከተች። የሰውዬው ፊት ግን በደስታ ይፈካል።

«ቆንጆ ባየሀ ቁጥር መቁነጥነጥህን ብተትወኝ አይሻልም! ይህቺ ወጣት ልጆቹን ለማስተማር ሥራ ፍለጋ ነው የመጣችው» በማለት ዳያን የመጣችበትን ምክንያት ይገልጹለታል። በዚህ ጊዜ የሰውዬው ፊት እንደ መስከረም ፀሐይ በይበልጥ ፈካ ይላል።

«እርግጠኛ ነኝ፣ ለሥራው ትስማማለች። እኔም ራሴ አስተማሪ ወይም ተማሪ ብሆንና በቀን ለሁለት ሰዓት ጊዜ ያህል ከልጆቹን ጋር ትምህርት ቤት ገብቼ ጊዜዬን ባሳልፍ ደስ ባለኝ» ካለ በኋላ ሰውዬው ማራኪ የሆነ ንግግር እንዳደረገ ሰው ይስታል። ግን ንግግሩ ቤቱን ይበጠብጣል። የመጻም ደንስቢ ፊት ተነፋ። የባላቸው ንግግር ልባቸውን አቆሰለው።

«በምን ዓይነት ፍርጃ ነው ይህችን የመሰለች ቆንጆ አስተማሪ የምትሆነው? ይህን የመሰለ መልክ ይዞ በአስተማሪነት ልተጠር ማለቱ

ጥሩ ምርጫ ነው እንዴ?» ብሎ ሲጠይቅ «መልስ መስጠት አለብኝ ግቢ ነው?» ብላ ጻያን ትጠይቃለች::

«የለም፣ ባለቤቴ ይቀልዳል:: የእኔ ከዚህ መኖር ረስቷል መሰለኝ ለጥያቄው መልስ መስጠትም ሆነ የሚናገረውን መስማት የለብሽም ሲልዎት ሰውዬው ይስቃል::

«ለዚህ መቼም የተፈጥሮ ስጦታ ያሻል» አለ ባል ተብዬው:: «ገና ጨዋታ ነው፣ አይደለም እንዴ? ለጠየቅኩት ጥያቄ መልስ መስጠት ግን አለብሽ:: የባለቤቴን አነጋገር ችላ በዪው:: እርስዋ እንደሆነ የቆንጆ ልጃገረዶች ፍራቻ ያጠቃታል» ካለ በኋላ ወደ ባለቤቱ ዞር ብሎ «የእኒ እመቤት ይህችን የመሰለች ልጅ ከመቅጠር ሌላ የተሻለ ምርጫ አይኖርም:: ለማንኛውም ሥራዬን ጥዬ ከዚት ብዙ ተቀመጥሁ:: የእኔ ከእዚህ መገኘት ደግሞ እንዳትስማሙ ሊያደርግ ስለሚችል እኔ ልሂድ:: ከሲቶች ሁሉ የበላይ የሆንሽ ውድ ባለቤቴ ደህና ዋይ:: በተዋቡት እግሮችሽ ሥር ብነጠፍ እንኳን ደስ የሚለኝ ወይዘሪትም ደህና ሰንብቺ:: ስመለስ እዚሁ ተቀጥረሽ ከቤቴ እንደማገኝሽ ተስፋ አደርጋለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ በልጅቺ ሳልቀና አልቀርም» ሲል ቀባጠረ::

ሰውዬው ይህንን ከተናገረና ባለቤቱን ከተሰናበተ በኋላ ተነስቶ ወጣ:: ከመውጣቱ በፊት ግን ጻያንን አፍጥጦ ያያል:: ጻያን ደግሞ እንደዚያ ከሚያፈጥባትና የባለቤቱን አንጀት ከሚያሳርር ሞቱን ትመርጣለች:: ቤቱን ዘግቶ ሲወጣ የሰውዬው ባለቤት ዓይናቸውን ይጨፍናሉ:: እኚህ ሴት ራሳቸውን ለመቆጣጠር ያደረጉትን ጥረት ጻያን በግልጽ ታያለች:: ሴትዮዋ ምን ዓይነት ቅናት እንዳደረባቸውና በባላቸው ላይ እምነት እንደሌላቸው ጻያን ተገነዘበች:: መጻም ደንበቢ ጻያንን ቀና ብለው ተመለከትዋት::

«አዝናለሁ» አሉ ሴትዮዋ:: «አንቺ ገና ሕፃን ልጅ ነሽ:: ከአንቺ ችጋሽ በእድሜ በብል ያለችዋን ሴት ነበር የምፈልገው:: ልቀጥርሽ አልች ልም»ሲልዎት ጻያን ነገሩ በደምብ ገባት:: የዋህና ገር ልጅ ስትሆን በቦጊዜው አጻፊስ ነገሮችን እየተማረች ነው:: መጻም ደንበቤ በምን ምክንያት አሳባቸውን እንደለወጡ አወቀች:: ረጋ ባለድምፅ «እኔም በጣም አዝናለሁ» አለች::

«አዝናለሁ» አሉ ሴትዮዋ በድጋሜ:: «ልጄ ሰው እንዴት ደነግማ ነው? ባለቤቴ ለንግግሩ የሚሰጠው ትርጉም ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ ሊገባሽ አይችልም:: ግን ብዙ ባሳቀይሽ ይሻላል፣ ሕፃን ልጅ መሆንሽን በመጀመሪያ አልታየኝም ነበር:: ባለቤቴ እንደሆነ ቀንሻጅትን በጣም ስለሚያደንቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

እኩን ሲያይ ሰውነቱ ይቅበጠበጣል። ይህ ደግሞ ተፈጥሮው ስለሆነ ምንም ለማድረግ አይቻልም። እዝናለሁ ደጎና ሁኝ» ብሰው ሲትዮጵ ጸያንን ሲጨብጡ እቹቸውን ዘረጉ። ጸያን ስትጠጣም እስከ በሩ ሸኝዋት።

«ወይዘሪት ቱርፔ» አሉ ሲትዮጵ፣ «ምክር ልለግስሽ። በጣም ቆንጆ ነሽ፤ ግን ገና ሕፃን ልጅ ነሽ። የዋህና ገር እንደሆንሽም እርግጠኛ ነኝ። ባለቤቱ አድራሻሽን ቢጠይቅሽ ያለሽበትን አታስታውቂው። ይህን የምታደርጊው ለራስሽ ብለሽ እንጂ ለእኔ ብለሽ አይደለም።»

ጸያን የተሰጣትን ትእዛዝ ተቀብላ ከሲትዮጵ ቤት በቶሎ ወጥታ ወደ ቤትዋ ተመለሰች። ጊዜው በመምሸቱ ከሌላ ቦታ ሥራ እንጸለ ለመጠየት ወይም ወደ መጸም ሲልቨር ለመመለስ አልቻለችም። በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ወደ መጸም ሲልቨር መሥሪያ ቤት ሄደች። ጸያን ከቢሮዋ ስትገባ መጸም ሲልቨር በጣም ተቆጥታ አነጋገረቻት።

«እንደምን አደርሽ ወይዘሪት ቱርፔ» አለች መጸም ሲልቨር። «በጣም ጥሩ ከሚባሉት ደንበኞቼ አንድዋን በአንቺ ምክንያት ማጣቴን ታውቂያለሽ? በአንቺ ምክንያት የተፈጠረውን ውዝግብ ለማስተካከል ካልቻልክ ከደምበኛዬ ጋር ለዘላለም መቆራረጤ ነው» ካለች በኋላ ተጠለ አድርጋ «መሥሪያ ቤቱ እምነት የተጣለበትና ሰው ሁሉ የሚያከብረው መሆኑን ከመጀመሪያው ነግሬሽ ነበር። እስከ ዛሬ ወደ እኔ መሥሪያ ቤት መጥተው ሥራ ከጠየቁኝ ሰዎች መካከል ሰለእነርሱ የሚመሰክርና እነርሱን የሚያውቅ ሰው እንደሌለ ተናግረው አያውቁም። የአንቺን ማመልከቻ በመቀበሌ በጣም አዝናለሁ። ወይዘሪት ቱርፔ የከፈልሽውን ገንዘብ እመልሳለሁ። ብቻ ነገር ቢበዛ ዋጋ የለውም። አሁን ደህና ሁኝ » በማለት አሰናበተቻት።

«ኑሮ እጅግ ከባድ ነው፣ ከባድ ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ነው» አለች ጸያን ለራስዋ ወደ ኑሮ ሳጸና ከሚያስገባው በር አንዱ የተቆለፈባት እየመለሳት። ጸያን ከሲትዮዋ ቢሮ ወጥታ ብትሄድም የኑሮን ትግል ለመቋቋም ሳትሰለች እንደገና መሞከር እንጸለባት ለራስዋ ነገረች። ሥራ ካላገኘች ደግሞ በረሃብ የምትሞት መሆንዋን ስለምታውቅ በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነስታ ሥራ ፍለጋ ወጣች።

የትም ስትሄድ የየሰዉ አቀባበል የተለመደ ሆኖ አገኘችው። ሰዎቹ አፍጥጠው እያዩ በፈገግታ በማነጋገር የማይፈጸምና የማይጨበጥ ተስፋ ይሰጥዋታል። ታዲያ ይህ ሁሉ የሚሆነው «ስለእኔ የሚያውቅና ዋስ የሚሆነኝ ዘመድ ወይም ወዳጅ የለኝም» ብላ እስከምትናገር ድረስ ብቻ

ነበር። ሁሉም ልፋትዋ ዋጋ እንደሌለው ይገልጹላታል።

ቀኑ ሳምንት፣ ሳምንቱ ወር ሆነባት። እግሮችዋ መራመድ እስኪሳናቸው ድረስ ከመዞርና ከዛሬ ነገ ሥራ አገኛለሁ በማለት በተስፋ ከመቁመጥ ሌላ ምርጫ አልነበራትም። ከጊዜ በኋላ ሐሞትዋ እየፈሰሰና ተስፋ እየቆረጠች ሄደች። ከአንድ ማተሚያ ቤት የትርጉም ሥራ ማስታወቂያ ወጥቶ ስለነበር በማመንታት ማመልከቻ አስገባች። ግን በለስ ቀናትና በአርባ ታውንድ ተቀጠረች። ይህ ከብዙ ልፋት በኋላ ያገኘችው ሥራ የመጀመሪያዋና የመጨረሻዋም ነበር።

አንድ አላብ መጣላት። አባትዋ «በሥዕል ሳበዝ ነሽ» ያላትን አስታወሰች። «ለምን ሥዕል አልሞክርም?» የሚል ጥያቄ ከጎለናዋ ውስጥ ገባ። ስለዚህ ለሥዕል የሚያስፈልጋትን ዕቃ ገዛች። ቀኑን ሙሉ እየሠራች ሁለት ባለቅብ ሥዕሎችን አወጣች። ያቺ ምስኪን የሥራ ፍሬዋን ስታይ ሰድልዋ የተከፈተ መሰላት።

ሥዕሎቹን ለመሸጥ ወደ ገበያ ወጣች። ግን ከሰዓት ወደ ሰዓት ብትዞር የሚገዛት በማጣትዋ ተስፋዋ ሁሉ ኩምሽሽ አለ። ባለሱቅች «በቂ ሥዕል ስለገዛን የአንቺን ስእል አንፈልግም» አልዋት። «ሥዕሎቹ ጥሩ ቢሆኑም ፈላጊ የላቸውም» ሲልዋትማ ለመሻሻል የነበራት ተስፋ ሁሉ የተተበረ መሰላት።

አንድ ነጋደ ሁናቴዋ አሳዝኖት ገዥ ከመጣ ስእሎቹን ሊሸጥላትና ከሱቁ ግድግዳ ላይ ሊሰቅልላት ተስፋ ሰጣት። ግን አንደኛውን እንኳን ቢሆን ገንዘብ እሙጥጥ ሊገዛት አልፈቀደም። የነበራት ተስፋ ትንሽ መለስ አለ። ለሕዝብ ከታዩ እንደሚሸጡ አመነች። ሆኖም ዳያን በየቀኑ ከሰውዬው ሱቅ በመሄድ ሥዕሎችዋ ተሸጠው ወይም አልተሸጡ እንደሆነ በመጠየቅ ሰውዬውን ለማስቸገር አልፈለገችም። ስለዚህ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት በሱቁ አጠገብ በሚያልፈው መንገድ እያለፈች የተንጠለጠሉት ሥዕሎችዋ መኖር አለመኖራቸውን ታይለች። ስትንከራተት ላያትና ሁኔታዋን ለተመለከተ አንጀት ትበላ ነበር። አንድ ቀን በዚያ ስታልፍ የሱቁ ባለቤት ስላያት አስጠራት። ወደ ሱቁ ዶሎ ብላ ሄደች።

ምዕራፍ አሥራ አራት

ባለቅጥብ ሥዕሎችዋ

የሱቱ ባለቤት ሚስተር ሬዲንገር ይባላል። ነጋዴው በሕያውት ዘመኑ ብዙ ሚሊዮኖችን አነጋግሯል። ዳያን ሚሊ ተብለው ከሚጠሩት መካከል አንድዋ ስትሆን በመጀመሪያው ቀን ዳያን ገና ከሱቱ ስትገባ በአድናቆት ፈዝዘ ተመለከታት። ከሳለችው ሥዕል ይበልጥ ራስዋ ሥዕል መስላ ታየችው። በእለቱ ሲያስጠራት «ሲያነጋግሩኝ ፈልገዋል እንዴ?» ስትል ዳያን በመጓጓት ጠየቀችው።

«እምን አረፍ በይ፤ ብቻ የእንድ ደቂቃ ጊዜ ሰጪኝ። እነዚያ ሁለት ሰዎች ሊያነጋግሩኝ ስለሚፈልጉ ደርሽ መጣሁ» ካላት በኋላ ነጋዴው ሰዎቹ ወደ ተቀመጡበት ሥፍራ ሄደ። ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ዝናው በዓለም የገነነው ፍራንክ ሚለር የተባለው ዝነኛ ሠዓሊ ሲሆን ሌላው የታወቀው የሥነ ጥበብ አሳቻሪና ደጋፊ ሱርድ ራይደር ይባላሉ።

«ሚስተር ሚለር ይቅርታ ያድርጉልኝና ስለአንድ ነገር ስትጠይቁ የለማሁ መሰለኝ። ስለጉዳዩ ከአንዲት ሴት ጋር ተነጋግሬ ነበር» አያለ የሱቱ ባለቤት ሲናገር ሱርድ ራይደር ጣልቃ ይገባሉ።

«ሚስተር ሬዲንገር የመጨረሻውን ሙለታ ዋልነስን ለማለት የምንችለው ከሲትዮዋ ጋር ስታገናኝን ብቻ ነው። ወደ ሲትዮዋ ከመሰድከን እንግሊዝ አገር ሙሰጥ ከምትገኘው ከመጨረሻዋ ቁንጅ ሴት ጋር አገናኝሽን ማለት ነው» ሲሉት ነጋዴው ተመልሰ ሳቅ አያለ ወደ ዳያን ይሄዳል። ለሱርድ ራይደር ባይሆን ኖር ነጋዴው ከስታራ ሰው ነበር።

«ሚለር» አሉ ሱርድ ራይደር «ልትሠራው ሳተድከው ምስል እጅግ የተከፋች ግን በጣም ቁንጅ የሆነች ሴት ፊት ያላት ስትፈልግ ብዙ ጊዜ ፈጅቶብሃል። እስከ ዛሬ ያየሃቸው ቁንጅቶች ሁሉ አይስማሙኝም ብለህ መልሰሃል።»

«አምን፣ ይሀን አድርጌአለሁ» ሲል ዝነኛው ሠዓሊ መለሰ። «ምስሉ ዘላለማዊ እንዲሆን ስለምፈልግ ለምስሉ ጎዘን የገረፈው ቁንጅ ፊት ነበር የምፈልገው። አዙን የሚያሰፈልገኝ ሳቅ አያለ የሞት ጥላን የሚመለከትና የምፈልገው። አዙን የሚያሰፈልገኝ ሳቅ አያለ የሞት ጥላን የሚመለከትና የሞትን አስፈሪ ገጽታ በውስጡ ለመያዝ የሚጥር ዓይን ነው። ከዚህም በላይ ውበት እንደ ፀሐይ ሙራ ከላዩ ላይ የፈነጠተበት ግን በነዘን ብዛት ውበቱን ያጣ መልክ ነው የምሻው። በሥቃይና በሞንትት ባሕር የሰመጠ ፊት ነው ፈልጌ ያጣሁት።»

«እንግዲያውስ» አሉ ሉርድ ራይደር፣ «ይህቺ በሩቁ የምናያትን ሴት እንደ ምሳሌ ከመውሰድ ሌላ የተሻለ ምርጫ ያለህ አይመስለኝም:: ዓይኖችዋ የተደበቁ ምስጢር አላቸው:: ከዓይኖችዋ ሥር እየወጣ የሚታየው ነፍሰ እንደ ጥቅምት ውኃ የጠራ ነው:: ከንፈሮችዋን ተመልከት:: እንደ አዲ ረዳ አበባ በውበት ያጌጡ ናቸው:: የእርስዋን ፊት ትጂ በትክክል ከሠራህ ሥዕሉን ሳላወላውል በጥሩ ዋጋ እኔው ራሴ እገዛሃለሁ::»

«ግን» አለ ሠዓሊው፤ «ወደ ሴትዮዋ ሄጄ ከፊት ለፊቴ ቁጭ ብለሽ በእጅ ሥዕል መልከሽን ለመቅዳት እፈልጋለሁ ብሎ ለመጠየቅ የምደፍር አይመስለኝም::»

«ሚስተር ሬዲንገር» አሉ የዝነኛው ሠዓሊ ጓደኛ «የሥነ ጥበብ ነገር ሲነሳ ምንተ-እፍረቴን እረሳለሁ:: ደፈረኝ ባትለኝ እንጂ ይህቺ ሴት ሥራ ትፈልግ እንደሆነ አንተ ብትጠይቅልኝ::»

«የሳለቻቸውን ጥቂት ሥዕሎች እንድሸጥላት ከሱቁ አስቀምጣለች:: ትናንት አንድ ሰው ሥዕሎቹን ለመግዛት ፈልጎ ከተጠየቀው ዋጋ ግማሽ ብቻ እከፍላለሁ ስላለ ሳልሸጥለት ቀረሁ» አለ ነጋዴው::

«ሥዕሎቹ ጥሩዎች ናቸው ?» ብለው ሲጠይቁት «በጣም ጥሩዎች ናቸው» ሲል ነጋዴው መለሰላቸው::

«እንግዲያውስ ለእያንዳንዱ ሥዕል ሃያ አምስት ፓውንድ እከፍላ ታለሁ:: ሌላ ሥዕል አንድትሠራልኝ ደግሞ እዝዛታለሁና ካርዴን ውሰድና ስጣት:: ልተዋወቃት መፈለጌንም ግለጽላት:: ወደፊት ስለምትሠራልኝ ሥዕል አንዳንድ መመሪያዎችን ብሰጣት እወድዳለሁ» ሲሉ ሉርድ ራይደር የሱቁን ባለቤት ይልኩታል::

ካርዱን ወስዶ ሰጣት:: ዳያን ካርዱን ስትቀበል መገረምዋን ከእዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ተመለከቱ:: ከዚያም የሱቁ ጌታ ወደ ሰዎቹ ተመልሶ «ወይዘሪት ቶርፔ፣ የጌታዬን ትእዛዝ በደስታ ተቀብላለች» ሲል መልእክቱን አስተላለፈ::

ሁለቱ ሰዎች ወደ ዳያን ሄዱ:: ሉርድ ራይደር ቀረብ ብለው ሲያይዋት ተቅበጠበጡ:: ሰውነታቸው የተቅበጠበጠው በጎዘን ይሁን በፍቅር ወይም በሌላ ነገር አላወቁትም:: ዝነኛው ሠዓሊ አፍጥጦ ዳያንን ተመለከታት:: የዚያን ዓይነት ገጽታ የሰጣት ጎዘን ይሁን ፍቅር ወይም ሌላ ነገር እንደሆነ እርሱም ለመለየት ተሳነው::

«ጓደኛዬ በእንቺ ላይ በማፍጠጡ ይቅርታ አጠይቃለሁ:: ሠዓሊ ስለሆነ ያየውን ሁሉ አጥርቶ መመልከትን ይወድዳል:: አንዳንድ ጊዜ

ሰዎች ሐሙልት ይመስሉታል መሰለኝ ያፈጥባትዋል። ማንም ሰው ቢሆን አጭጥጠው ሲያዩት ቅር እንደሚሰኝ ይረሳል።» ዳያን ግን «ሰው ቢያየኝ ግድ የለኝም» ስትል መለሰች።

ሱርድ ራይደር ስለሥዕሎቹ ዳያንን አነጋገርዋት። ከእነዚያ ጋር የሚሄድ ሁለት ሌሎች ሥዕሎች እንደሚፈልጉም ገለጹላት። ዳያን ትእዛዙን በደስታ ተቀበለች።

«ሚስተር ሚለር አንድ ሥዕል እየሠራልኝ ነው» አሉ ሱርድ ራይደር። «ምስሉ የሠዓሊውን ችሎታና ስም ዘላለማዊ ያደርጋል ተብሉ እምነት የተጣለበት ነው። ስለሥዕሉ ሥራ መሳካት ውለታ እንድትውይለት ይፈልጋል።»

«ዝነኛው ሠዓሊ ሚስተር ሚለር ማለት እርሳቸው ናቸው?» ብላ ዳያን ከጠየቀች በኋላ «አባቴ የሠዓሊዎች ንጉሥ እያለ ይጠራዎት ነበር። አባቴ የእርስዎን ሥዕል እጅግ በጣም ያደንቅ ነበር» በማለት ሳታውቀው ተናገረች። በዚህ ጊዜ «አባትሽ ሠዓሊ ነበር?» ብሉ ሚስተር ሚለር ጠየቃት።

«አዎን፣ ግን ዝናው የገነነው ከሞተ በኋላ ነው እንጂ የታወቀ ሠዓሊ ነበር።» በዚህ ጊዜ «ስሙ ማን ኖሯል?» ሲሉ ሱርድ ራይደር ጠየቁ።

ዳያን የአባትዋን ስም ሲጠይቋት ቀደም ሲል እንደሆነው አልደነገጠችም። ከአጠገብዋ የነበሩት ሰዎች ተጉረ-ተሳል አለመሆናቸውን ስለተገነዘበችና ማንነታቸውን ስለገመቱት ነበር ያልደነገጠችው።

«ልነግራችሁ አልችልም» አለች። «ሆኖም አባቴ የታወቀ ሠዓሊ ነበር። እርሱ የሠራቸው ሥዕሎች ለሦስት ዓመት ሮያል አካዳሚ ውስጥ ለሕዝብ ታይተዋል። ሕዝቡ ደግሞ ባየው ሥዕል መደሰቱን በግልጽ መስክሮአል። አባቴ የሞተው በቅርቡ ሲሆን እሱ ከሞተ ጀምሮ ብዙ ችግር ደርሶብኛል። በዚህ የተነሣ ስሜን እንድለውጥ ተገድጃለሁ።»

«በገንዘብ እጦት ምክንያት ይሆን?» ሲል ሚስተር ሚለር ሲጠይቃት «የለም፣ ስሜን የለወጥኩት አንድ እጅግ የምጠላው ሰው ፈልጎ እንዳያገኘኝ በማለት ነው» አለቻቸው።

«የሠዓሊ ልጅ በመሆንሽ ደስታዬ እጥፍ ነው።» አሉ ሱርድ ራይደር። «ለሥዕል ያለሽ ፍቅር ደግሞ ብርቱ በመሆኑ የጓደኛዬን ጥያቄ እንደምትፈጽሚለት ተስፋ አደርጋለሁ።»

«ማንኛውንም ሠዓሊ ለማስደሰት ስል የጠየቁውን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ አልልም» አለች ዳያን።

«አንድ ሙሰታ አንድትሙይልኝ አፈልጋለሁ» አለ ሚስተር ሚለር። «ልፈጽመውና ላያርገው የማልችለው ነገር ብለሽ ታሳፍሪኝ ይሆናል በግሌ አሳብ አድሮብኛል። ሆኖም የፈለጉትን ከመጠየቅ መቦዘን ፈሪነት ነው ብሎ የታወቀው ሰአሊ ሲናገር «እኔ ግን የማልፈትደውን ነገር ይጠይቁኛል ብዬ አልጠራጠርም» አለች ጸያን።

«አንድ በጅምር የቀረ ሥዕል አለኝ። ለዚህ ሥዕል አንደ ሞዴል አድርጌ የምወስደው ታሪክ ያለው ቁንጅ ፊት አፈልጋለሁ። ታዲያ ውበት ብቻ ያላት ሲት ፊት የማይበታ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለምስሉ የሚያስፈልገው ልክ የአንቺን ፊት የመሰለ ፊት ነው።»

«የእኔ ፊት ታሪክ እንዳለው ይገልጻል እንዴ?» ስትል ጸያን ጠየቀች።

«አዎን» ሲል መለሰላት ሰአሊው። «የተለየ ታሪክ እንዳለው በግልጽ ያሳያል። የአንቺን ፊት እያየሁ ስዕሉን እንዳጠናቅት ትፈቅጂልኛለሽ? ከፈቀድሽልኝ ከአናቱ ጋር አስተዋውቅሻለሁ። እኔን የምትቆጣጠር ሚስት ስለሌለኝ ከቤት ውስጥ ሁሉም ነገር ላንቺ በሚስማማ አኳኋን እንዲሠራ አደርጋለሁ።»

«ጥያቄውን በደስታ አቀበላለሁ» ስትል ጸያን መስማማትዋን ስትገልጽ «ባለውለታሽ ነኝ። ምስጋናዬም ከፍ ያለ ነው» አለ ፍራንክ ሚለር። «ለዚህ የምትጠይቂው ነገር ካለ ሳላወላውል በደስታ አከናውላለሁ።»

«ምንም አልፈልግም» ብላ ጸያን ኮመለሰች በኋላ «የጠየቁኝን መፈጸም ደስታ ይሰጠኛል፣ ይህን በማጋርግበት ጊዜ የጥንቱ የደስታ ኑሮዬ የተመለሰ ነው የሚመስለኝ» አለች።

ሁለቱ ሲጨዋወቱ ሉርድ ራይደር አተኩረው ጸያንን ይመለከትዋታል። «ልትደብተው የፈለገችው ምስጢር የሚያሳፍር አይመስለኝም። ሲያይዋት ደግ ሴት ትመስላለች። እንደ ሕፃንም የዋህ ናት። ልክ ኑኃ ባል አሳገባችም» አያሉ ለርድ ራይደር ያሰላስላሉ። ምክንያቱም ጸያን የአድ ጓንትዋን ሰታወልቅ ከእዚያ የነበሩት ምስት ሰዎች ጣቶችዋን ተመለከቱ። ከሚያማምሩ ጣቶችዋ ሳይ የጋብቻ ቀለበት የተባለ ነገር የለም።

«መልካም ፈቃድሽ ሆኖ አድራሻሽን ብትነግሪኝ፣ አናቱና እኔ ነገ እንጠይቅሻለን። ከዚያም ከሥዕሉ መሥራያ አስቲዲዮ ለመምጣት በምን ሰዓ አንደሚመችሽ እንነጋገራለን» አለ ፍራንክ ሚለር።

ጸያን ሳቅ ብላ «ከንቲሽ የሚባለውን ሰፈር ያውቁታል?» ስትል ጠየቀች።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎን፣ ተማሪ ላለሁ ኖሬበታለሁ» ሲላት ትክክለኛ አድራሻዋን ሰጠችው። ከዚያም «ነገ እንጠይትሻለን» ብለው ሁለቱ ሰዎች እጅ ነሰተዋት ወጡ።

የሰዎቹ ሁኔቴ ሰዳያን ሕልም መስሎ ታያት። ሥዕሎችዋን ሰለሸጠች ገንዘብ አገኘች። ሴላ ሥዕል ከሠራች ደግሞ ተጨማሪ ገንዘብ ታገኛለች። ከዚህም በላይ ወደፊት ከምታፈራቸው ሠዓሊዎች ጋር ልትውል ነው። እጅግ ደስ አላት። መላ ሰውነትዋ በተስፋ ተሞላ። «ችግሬና ሥቃዬ ሁሉ ወደ ጥጸሜ የደረሰ ይመስላል» አለች ለራሰዋ።

ምዕራፍ አሥራ አምስት

የሠዓሊው ሞዴል

የሠዓሊው እናት ልጃቸው በኃይል ሲለምናቸው ይሰቃሉ። እናቱ የሰዘበ ጠባይ ነው ያላቸው። ልጃቸው ፍራንክ ሚለር ከዚያን ቤት እንሂድ አያለ ይጠተውታቸዋል። እሺ ከማለት ሌላ የተለየ መልስ ሊሰጡ አልቻሉም።

«ፍራንክ ላቀድከው ሥዕል ሞዴል ይሆነኛል ብለህ የመረጥከውን አይልሃለሁ» በማለት እናቱ የልጃቸውን ጥያቄ መተበላቸውን ሲገልጹለት «የመረጥኩት የእንጨት ወይም የላስቲክ ሞዴል አንዳይመስልሽ። እጅግ የተዋበችና ግርማዋ ሞገስዋ የሚያስፈራ ሴት ናት። ደግሞም የሠዓሊ ልጅ ናት» አላቸው።

«ቀደም ሲል እንደ ነገርከኝ ከሆነ ሴትዮዋ ልትገለጠው የማትቸ የተደበቀ ምስጢር አላት። ሆዳቸው ውስጥ አምቀው ምስጢር የሚይዙ ሰዎችን እጅግ አድርጌ አፈራቸዋለሁ» አሉ ወይዘሮ ሚለር።

«እሷን የመሰለ ሰው አይተሽ እንደማታውቂ እርግጠኛ ነኝ» አለ ፍራንክ። «ፊትዋ ምንም እንኳን እጅግ የተዋበ ቢሆንም በጎዘን ብዛት መጠውለጉንና በችግር አለንጋ መገረፉን በግልጽ ያሳያል» እያለ ነገሩን ሊያራዝም ወይዘሮ ሚለር አሁንም ይሰቃሉ።

«እሺ ተወው፣ ይብቃ። የውበት ምሳሌ አድርገህ የወሰድካትን ሞዴል ሂጂ አያታለሁ።»

«እንኳ ለሁለም ርኅሩኅ መሆንሽን አውቃለሁ» ካለ በኋላ «ለዚህች

ልጅ ግን ከሁሉም ይበልጥ ደግና ርኅሩኅ እንድትሆኚላት እፈ
ብሎ ሲለምናቸው «ግድ የለህም፣ ለአንተ ስል ያልከውን ሁሉ እፈጽ
ይላሉ።

የልጁ እናት በልጃቸው ዝና፣ ክብርና ሞገስ እጅግ ይመካሉ
ቸው ደግሞ ስለሁለት ነገር እንጂ ስለሌላ ነገር ደንታ አልነበረው
እነዚህም እናቱና የሚሠራቸው ሥዕሎች ናቸው። የሴቶች ፈገግታ በሥ
ተቀርጾ ደስ ይበለው እንጂ ሌላ ስሜት አይሰጠውም።

እናቱ እሱን ለማስደሰት ሲሉ ሠረገላ እንዲዘጋጅ አዘዙና ጳ
ከነበረችበት ሠፈር ሄዱ። ወይዘሮ ሚለር ጳያንን ከአሰብዋት በላይ ው
ያገኘዋታል። በውበትዋ ዘመትር ከሚያይዋቸው ሴቶች ሁሉ የተለየች
ስትናገር ግርማ ሞገስ ያላት መሆንዋን በማየታቸው ወይዘሮ ሚ
በአድናቆት ይፈዝዛሉ። ሠዓሊው ጳያንንና እናቱን ካስተዋወቀ በኋላ ወይ
ሚለር የሚከተለውን ይናገራሉ።

«ወይዘሪት ቶርፔ፣ ስለደግነትሽና ስለችሮታሽ ላመሰግነሽ ነ
የመጣ ሁት። ልጄ ለሚሠራው ሥዕል ሞዴል ሁነሽ ሥዕሉን በሚሠራበት
ጊዜ ከፊቱ ለመቀመጥ በመፍቀድሽ እጅግ ነው የተደሰትኩት። ሥዕሉ
ውጤት ኖሮት፣ አምሮና ደምቆ ከወጣ ያማረው በእኔ የተነሳ ነው ብለሽ
ትኮራብታለሽ።»

«እሱን እንኳን የልጅዎ ችሎታ እንጂ የእኔ ሊሆን አይችልም» አለች
ጳያን። «አባቴ የልጅዎን ሥዕል እጅግ ያደንቅ ነበር። እኔም ሕፃን ሳለሁ
ስለሚስተር ሚለር ሥዕሎች ስለሰማሁ ይህ ሰው የሚሠራቸው ሥዕሎች
ምን ዓይነት ይሆኑ? እያልኩ አስብ ነበር። ግን እሱ በሚሠራው ሥዕል
እሳተፋለሁ የሚል እምነት አልነበረኝም።»

«ልጄ ከሠራቸው ሥዕሎች በሙሉ አሁን የጀመረውንና አኒ ቦሊን
የተባለው ሥዕል ከሁሉም ይበልጥ አደንቀዋለሁ» ብለው ወይዘሮ ሚለር
ሲናገሩ «እስካሁን በሰማሁት እኔም ደስ ብሎኛል» በማለት ጳያን ጣልቃ
ትገባለች።

«እኔም እንዲሁ በጣም እወድደዋለሁ፤ ግን ከሥዕሉ ይበልጥ የሱ
ትዮዋ ውበት ነው ደስ የሚለኝ። የተጀመረው ሥዕል የሚያሳየው
ንግሥት አኒ ቦሊን በሚቀጥለው ቀን እንገትዋ እንዲቆረጥ ተፈርዶባት
ሳለ በዋዜማው ከእስር ቤት ውስጥ ከመስኮት አጠገብ ተምበርክካ ፀሐይ
ስትጠልቅ ታያለች። የፀሐይ ጨረር በመስኮት ገብቶ ከደፋችው ዘውድ
ላይ ሲያርፍ ጥላው በግልጽ ከግድግዳው ላይ በመታየቱ ንግሥቲቱ ያንን

አትኩራ ትመለከታለች። ያንን ትርዒት ነው ልጄ ለመሳል የፈለገው።»

የጸያን ፊት በጉጉት በራ። «እንዴት ያለ የሚደነቅ አሳብ ነው» በማለት ድጋፍዋን ገለጸች።

«አምን፡ ይሆን ሥዕል ከፍጻሜ ለማድረስ ሞዴል የምትሆን እርስዋን የመሰለች ጥሩ ቁንጅና ያላት ሴት ታስፈልግ ነበር። የእኔ ቦሊን ፊት በተለይ በዚያች ሰዓት በትካዜ ተውጦ ስለነበር በኑሮዋ እጅግ ተደላች የሆነች ቁንጅ ሴት እንደ ሞዴል ብትወሰድ ሥዕሉን ያበላሸዋል። ልጄ ለጀመረው ሥዕል ሞዴል ለማድረግ እንዳንቺ ፊት የሚስማማ አስክ ዛሬ አላየሁም። ልጄ እንደሚነግረኝ የጀመረውን ሥዕል ለመጨረስ ቸኩሉአለ። ታዲያ ወይዘሪት ቱርፔ፣ ለዚሁ ሥራ ከቢታችን ለመምጣት መቼ ይመችሻል? ስትመለሽ ደግሞ እኔ አደርስሻለሁ» ሲልዋት «እርስዎ የሚመቾት ከሆነ ከነገ ጀምሮ በማንኛውም ሰዓት ይመቸኛል» አሰቻቸው።

«እሱማ ጥሩ ነው። ሥራውም ተፋጠነ ማለት ነው። ታዲያ የዛሬ ውንም ቀን አብረን ብናሳልፋት የምትችዪ ይመስልሻል? ምናልባት ለውጡ የሳሊና ሰረጥት ያስገኝልሽ ይሆናል» በማለት ሲጋብዟት ጸያን ሰበር ብሉ የነበረው አንገትዋን ቀና በማድረግ እመቤቲቱን ተመለከተቻቸው።

«ለሚስተር ሚለር ውለታ እንድውል ሲጠይቁኝ ለእኔ ውለታ እንደዋሉልኝ ነው የምቆጥረው። ወደ ቤትም እንድመጣ ሲጋብዙኝ ደግሞ እንደ ተጨማሪ ውለታ አድርጌ ነው የማየው። ይህም ለንደን ከተማ ውስጥ ለጥቂት ወራት ስቀመጥ የደረሰብኝን እንድገልጽልዎት ይገፋፉኛል። ዋስ የሚሆን ዘመድ ወይም ወዳጅ በማጣቴ ማንም ቃሌን አምኖ ሊያስጠጋኝ አልቻለም። 'ወሮበላ ናት' እያሉ ሊሆን ይችላል ሥራ ከጠየቅሁበት ሥፍራ ሁሉ ሊቀጥሩኝ አልፈቀዱም።»

«ምነው ወይዘሪት ቱርፔ? ተጠያቂ ዘመድ ወይም ወዳጅ ለመስጠት ያልቻልሽው እንዴት ነው?» ሲሉ ወይዘሮ ሚለር ጠየቅዋት።

«ስሜ ቱርፔ አይደለም» አለች ጸያን። «ይህ እኔ የፈጠርኩት ስም ነው። የማውቃቸውን ሰዎች ስም ብሰጥ እኔ የት እንዳለሁ ያውቃሉ። የት እንዳለሁ ደግሞ እንዲታወቅ አልፈልግም።»

«ምክንያቱን ልትነግሪኝ ትፈቅጃለሽ?» በማለት ወይዘሮ ሚለር ሲጠ የቁ «ሙሉ በሙሉ ባይሆን በከፊል ልነግሮት እችላለሁ» አለች ጸያን።

«አባቴ ማለቴ የአባቴ ስም ለእኔ ትልቅ ክብርና ሞገስ ይሆነኝ ነበር። ግን ማን እንደሆነ ለመናገር አልችልም። አባቴ ሲሞት ከአንድ ሰው እጅ ጣለኝ። ከዚያም በየዋህነት ወይም ባለማወቅ ሊሆን ይችላል አንድ

ትልቅ ስሕተት ሠራሁ:: አሁንም ስሜን የምደብቀውና የምሸሸው ያ
ያሳሳተ ሰውና እጎቱ እንዳያገኙኝና ፊታቸውን እንደገና እንዳላይ ነ
እነሱ ከሚያገኙኝ ሞቴን እመርጣለሁ:: ሰዎቹን በኃይል ነው የምጠላቸ
የእነሱ ጥላቻ ቤቴንና ወዳጆቼን እንዲሁም የምወድደውን ነገር ሁሉ ን
እንድጠፋ አስገድዶኛል:: እኔ ወይም እነሱ እስክንሞት ድረስ ከመያዘ
እነርሱን ከመሸሽ አላቋርጥም::»

ዳያን ታሪክዋን ባጭሩ ስትዘረዝር ወይዘሮ ሚለር አተኩረ
ይመለከትዋታል:: ከዚያም «ታሪክሽ ጨርሶ እንግዳ ነው» አለዋት

«ሁለቱ ሰዎች በጣም በድለውኛል» ካለች በኋላ ዳያን ግልፃ
ጀመረች:: «ግንም ሰው ይቅር ሊለው የማይችል በደል ነው የፈጸሙብኝ
በማለት ዳያን እምርራ ስትናገር ወይዘሮ ሚለር ግራ ገባቸው::

«የእኔ ሕይወት አልፎአል» አለች ዳያን:: «ኑሮዬ ተሰፋ፣ ፍቅርና
ደስታ የተለየው ስለሆነ በዚህ ዓለም ላይ ምንም ደስታ የለኝም» ስትላቸ
ደግሞ «የእኔ ልጅ፤ ይህን እንኳን ለማለት አትችዪም» ሲሉ ወይዘሮ
ሚለር መለሱላት::

ወይዘሮ ሚለር እንደዚህ ያለ ችግርና ስቃይ በሴት ላይ ይደርሳል
ብለው አስበው አያውቁም:: ዳያን ዓይናችዋ በእንባ እንደ ራሱ ቀና ብ
ታያቸዋለች:: ከዚያም የሴትዮዋን እጅ ሰማ የሚከተለውን ተናገረች::

«ይህን ሁሉ ከነገርኩዎት በኋላ አሁንም ከቤትዎ እንድመጣ ከጋበዙኝ
እመጣለሁ:: ሆኖም አሁን እንደ ነገርኩዎት ጥሩ ሰም፣ ቤት፣ ወይም ገደኛ
የለኝም:: ሁሉንም ከጥንት ኑሮዬ ጋር ጥዬ ነው የመጣሁት:: ከእንግዲህ
ወዲህ ስለእኔ በበለጠ ለማወቅ ቢፈልጉ ሌላ የምነግሮት ነገር የለኝም::
የጥንቱን ኑሮዬን ከራሴ ላይ በማውረድ አምዘግዝጊ ጥዬዋለሁ:: ታሪክ
እንዲህ የተዘበራረቀ ሁኖ ላለ እኔን ለማስጠጋት ከፈቀዱና ካዘኑልኝ ኑ
መርሮአት የትም የወደቀችዋን ልጅ ማፍቀርዎን ይገንዘቡ::»

«ልጄ» አሉ ወይዘሮ ሚለር «እንዲህ ብለሽ አትናገሪ:: እርግጠኛ ነኝ
አስፈሪ የሆነ ኑሮ ነው ያሳለፍሽው:: ግን ልጅ ስለሆንሽ ያለፈውን ችግርሽን
በቶሎ ትረሻለሽ:: የደስታ ዘመን እንደሚጠብቅሽ አልጠራጠርም:: እንድ
ጥያቄ ብቻ ልጠይቅሽ:: ግን ይህን ጥያቄ የምጠይቅሽ ስለተጠራጠርኩሽ
ሳይሆን የእምነትሽን ጥናት ለማወቅ ስለፈለግሁ ብቻ ነው:: እናቴ ሞታለች
ብለሻል:: ታዲያ አንድ ቀን እንደምትገናኙ ታውቂያለሽ?»

«እምን አውቃለሁ» አለች ዳያን:: ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ሠዓሊውና እናቱ
የዳያንን የዋህነትና ንጽሕና አልተጠራጠሩም:: ዳያን አብራቸው ሄደች::

ከዚያም አባትዋ «ዳያንዬ» እያለ ይጠራት እንደ ነበር የሚያስታውሱ ብዙ ነገሮች አጋጠምዋት::

ሎርድ ራይደር ስለሥዕሉ አሳብ ለማካፈል ከጓደኞቹው ቤት ይመጣሉ:: ወይዘሮ ሚሰር አዚያው ከሥዕል ቤት ቁጭ ብለዋል:: ዳያን ንግሥት አኒ ቦሊንን እንድትመስል ልክ እንደ ንግሥቲትዋ አለበሰዋት:: ልብሱን ለብሳ ቢያያት ፍራንክ ሚለር እጅግ ደስ አለው:: ዳያን ቁርጥ አኒ ቦሊንን መሰለች:: ሠዓሊው እጹ ዝሉ በሩሽ መያገ አስኪያትተው ድረስ ሠራ::

«ወይዘሪት ቶርፔ ከዚህ ይበልጥ ልሠራ አልችልም፣ አሰፈራሽኝ:: አኒ ቦሊን ራስዋ ከነነፍስዋ መጥታ ከፊቴ የተንበረከከች ነው የመሰለኝ» አለ አርቲስቱ::

«እንዴት አንድ ሰው ሌላውን ለመምሰል ይታገላል? ምን ዓይነት አሳዛኝ ታሪክ ነው» አለች ዳያን በቀልድ መልክ::

«አምን» አሉ ሎርድ ራይደር:: «አኒ ቦሊንን ለመምሰል መታገልሽ በፊትሽ ይታወቃል:: ይህ ሥዕል ሲያልት ትልቅ ዋጋ ያለው ይሆናል:: ዙኤታሽ አንድ ነገር አስታወሰኝ:: ባለፈው ሳምንት አንድ ሥዕል ገዝቹ ነበር:: ሥዕሉ የተፈጥሮን ውበት የሚያሳይ ሲሆን የተሳለው ባልፎር በተባለ አንድ ሰው ነው:: አባትዋ የሠራው ሥዕል መሆኑ ነው:: ስለዚህ ሰው የምታውቂው ነገር አለ?» ብሉ ዳያንን ጠየቃት::

«ባልፎር?» ሲል ሠዓሊው ሚሰር ግልቃ ይገባል:: ስለዚህ ሰው የሰማሁ ይመስለኛል:: የሠራቹው ሥዕሎች እንኳን አንድ ጊዜ ከሮያል አካዳሚ ውስጥ ለሕዝብ እንዲታዩ ቀርበው ሳለ አይቻቸዋለሁ:: ጥሩ ጥሩ ዓይነት ሥዕሎች ነበሩ:: አሁን ግን ይህ ሰው በሕይወት ያለ አይመስለኝም::»

ዳያን ቃል አልተነፈሰችም:: ሆኖም ፊትዋ በአንድ ጊዜ ተለዋወጠ:: የፊትዋን መለዋወጥ ሚስተር ፍራንክ ሚለር ይገነዘባል::

«እማዬ፣ ወይዘሪት ቶርፔ ደክሞአታል:: ለዛሬ ከዚሁ ባቆም ይሻላል:: ወደ እንግዳ ቤት ውሰጃትና ትረፍ::»

ሁለቱ ሴቶች ተያይዘው ከወጡ በኋላ «እንዴት ያለች ተዋናይ ይመጣት ነበር» አሉ ሎርድ ራይደር:: «እንደ እርስዋ ያለች ሴት አይቼም አላውቅ! ወደር የሌላት ቆንጆ ናት::»

በሚቀጥሉት ቀናት ሠዓሊው ዳያንን ከፊቱ እያስቀመጠ ሥራውን ቀጠለ:: አንድ ቀን ሠዓሊው ቡሩሾቹን ሲያነሳ ሳቅ ይላል:: ሥዕሉ ከጥጻሜ ሲደርስ ጥሩ ሆኖ ስለወጣ ያዩት ሁሉ ተደነቁበት:: «ለሕዝብ መታየት

አለበት» አሉ ሱርድ ራይደር:: «እንዲያውም ከሥዕል ኤግዚቢሽን መቅረ
ይናርበታል::»

«ሥዕሉ ካለቀ በኋላ ለሕዝብ ስለታየ የእንግሊዝ አገር ሰው በሚ
ስለሥዕሉ ያወራ ጀመር:: 'እንደዚያ ያለ ሥዕል ተሠርቶ አይታወቅም
እየተባለ ወሬው ባገሩ ሁሉ ተነዛ:: የሥዕሉ ማማር የፍራንክ ሚለርን
ስም ዘላለማዊ አደረገው:: በዚህ ጊዜ የወይዘሮ ሚለርና የዳያን ዝምድና
እየጠነከረ ሄደ:: ከዚህም በላይ የልጅትዋ ጠባይ ማለት ገርነትዋ፣ ትህትናዋ
ቅንነትዋ የሠዓሊውን እናት ልብ ይማርካል:: ሴትዮዋ እንደዚች ልጅ ያለ
ጥሩ ሴት አይተው አያውቁም:: ዳያን ብዙውን ጊዜ ከሴትዮዋ አትለይም
ሴትዮዋ ደግሞ ምክንያት እየፈጠሩ ከቤታቸው ያስቀርዋታል:: ከጊዜ
በኋላ ግን የሠዓሊው እናት አንድ ዓይነት ጭንቀት ገባቸው::

«እማማ» አለ ሠዓሊው፣ «ሌላ ሥዕል ለመሥራት አሰቢአለሁ
ለረጅም ጊዜ ያለ ሥራ ጊዜዬን አቃጠልኩ» ብሎ ሲናገር «መቼ ሥሪ
ፈትተህ ታውቅና ነው ልጄ?» ይሉታል::

«የለም የሚያኮራ ሥዕል ከሠራሁ ቆይቻለሁ ማለቴ ነው:: ግሪ
እስትዋርት ከፈረንሳይ ባሕር ጠረፍ ስትጓዝ የሚያሳይ ሌላ ሥዕል
ለመሥራት እፈልጋለሁ:: ታዲያ አሁንም ቢሆን ሞዴል የማደርጋት
ወይዘሪት ቶርፔን ነው::»

«ልጄ፣ የወይዘሪት ቶርፔ ቆንጆ ፊት በየሥዕሉ ላይ ሊወጣ አይችልም
ሰዎች ይተቹሃል» አሉት እናቱ::

«በተቻለኝ ሁሉ መልክዋን ለመቀያየር እሞክራለሁ:: እስከ ዛሬ
ካዩኋቸው ሴቶች ሁሉ ወይዘሪት ቶርፔን የመሰለች ቆንጆ አላየሁም
ስለውበትዋ ደግሞ ዓለም ከእኔ ጋር እንደሚስማማ አልጠራጠርም» ሲል
ፍራንክ ሚለር የዳያንን ውበት በማድነቅ ይናገራል::

«ታዲያ ምናልባት ዓለም ከእርስዋ ፍቅር ይዞት ነው እያለ ቢያማህለ
አሉ እናቱ ዝግ ብለው:: «ብታማ በውሸት አይሆንም:: ውበትዋ እንኳን
ሥጋዬን ነፍሴንም የሚያሳድድ ይመስለኛል:: ስለእርስዋ ብዙ አስባለሁ»
በማለት ሚለር ለእናቱ የደረሰበትን ሲገልጽ ወይዘሮ ሚለር ወደ ልጃቸው
ጠጋ ብለው ያቅፉታል::

«ልጄ» አሉ፣ «በዓለም ላይ ተደስተህ እንድትኖርልኝ እንጂ ሌላ
የምፈልገው ነገር የለኝም:: ደስ ካለችህ የለማኝ ልጅ ላግባ ብትለኝ እንኳን
እኔ አልቃወምም:: ግን የተደበቀ ምስጢር ያላትን ልጅ የትዳር ጓደኛ
ለማድረግ ባታስብ ደስ ይለኛል::»

t.me/OLDBOOKSPDF

« ግን እማማ፣ ሆድዋ ውስጥ የተቀበረው ምስጢር ወንጀል አለ መሆኑን ሁሉንም የምናምንበት ይመስለኛል።»

«ይህን እኔም አውቃለሁ፣ ብቻ ምነው ትስቃለህ? መቼም ደስ ትበልህ እንጂ ፍቅር አልያዘህም። እውነቱን ንገረኝ አስቲ፣ ልታገባት ትፈልጋለህ? በአርግጥ መቼም ከፍቅር መጥመድ ውስጥ አልገባህም! »

«እኔ አንቺን ከሁሉም ይበልጥ ስለማፈቅር እንጸንቺ የምወድደው ሰው የለም። ግን በዓለም ላይ ከማደንቃቸው ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ወይዘሪት ቶርፔን የበላይ አደርጋለሁ። ውበትዋ እጅግ ያስደንቃል። ቢሆንም በጥቅርዋ ጎሊናዬን አልሳትኩም። ምክንያቱም ጎሊናዬ በሥነ ጥበብና በእንቺ ፍቅር ተይዟል። ግን ከወይዘሪት ቶርፔ ጋር ለብዙ ጊዜ ከቆየሁ እሷን እንደጣዛ እገደዳለሁ የሚል ጥርጣሬ አድሮብኛል። ልጅትዋ በጣም ደስ ትለኛለች።»

«ስለልጅትዋ አንድ አሳብ አለኝ» አሉ ወይዘሮ ሚለር። «እኔ እንደ ምገምተው ባል ለማግባት ነፃ አትመስለኝም። ዕድሜዋ ገና አሥራ ዘጠኝ ዓመት እንኳን በቅጡ ሰላልሞላ ውበትዋ አልረገፈም። ስለዚህ አስከ ዛሬ እርስዋን ያፈተረ ይጠፋል ብዬ አልጠራጠርም። ልቧገራድ ከተባለች ጋብቻንና ፍቅርን የማታልም የለችም። እርስዋ ግን የዚህ ዓይነት አሳብ ከጎሊናዋ ውስጥ የለም። ስለወንዶች ብዙ አጫውቼአታለሁ። አንዱ ወንድ ሳበዝ ሲሆን ሌላው ለሰው አሳቢ፣ እንዲሁም ሌላው ደግሞ የዋህና ገር ነው በማለት ብዙ ነገርኳት። እርስዋ ታዲያ ስሜት አልሰጣትም። አንተን እንኳን ቢሆን ለእርስዋ ጥሩ ሠዓሊ እንጂ በአንተ ላይ የምታየው የተለየ ነገር ኖሮ ስሜት የምትሰጣት አይመስለኝም።»

«አንዱን ለማግባት ቃል ገብታለች ነው የምትዪው?» ብሉ ሲጠይቃቸው «የለም፣ ምን ማለቴ እንደሆነ ልነግርህ አልችልም። ምክንያቱም ትክክለኛውን ነገር እኔም አራሴ አላውቀውም። ግን ወይዘሪት ቶርፔ ነፃ ለው አይደለችም የሚል ስሜት ነው ያደረብኝ።»

ወይዘሮ ሚለር ለልጃቸው ደስታ ሲሉ ዴያንን ሲያነጋግሯት ይወስናሉ። አንድ ቀን ስለሴቶች ሠዓሊዎች ጨዋታ ተነሥቶ ሲወያዩ የወይዘሮ ሚለር ልጅ እንደሚለው ከሆነ ዴያን ጥሩ ሠዓሊ ልትሆን እንደምትችል ገለጸችላቸው።

«ጥሩ ሠዓሊ ለመሆን ጥረቴን አላቋርጥም ማለትሽ ነው?» ሲሉ ወይዘሮ ሚለር ጠያቂት።

«አዎን፣ ደጉ ልጅም ሊያስተምረኝ ተስፋ ሰጥቶኛል።»

«ግን» አሉ ወይዘሮ ሚለር፣ «ዕድሜሽን በሙሉ ከዚያ ከሚገኘው ትንሽ ቤት ውስጥ ለመኖር የወሰንሽ አይመስለኝም!»

«እዚያም ባይሆን የትም ብሄድ ስሜት አይሰጠኝም» አለች ዳያን

«ይህ ሁሉ ቆራጥነትና ውሳኔ አንድ ቀን መረሳቱ አይቀርም» አሉ ወይዘሮ ሚለር:: «ፍቅር ይዞሽ ባል ስታገቢ ይህ ሁሉ ይረሳል» ሲልዋት «የለም» አለች ልጅትዋ ቁርጥ አድርጋ:: «ፈጽሞ የማላደርገው ነገር ነው. ፍቅርና ጋብቻ ለእኔ አልተፈጠሩም» በማለት መለሰችላቸው::

«እንዲህ ያለውን ውሳኔ ለማላለፍ ገና ልጅ ነሽ:: ውበትሽ ማንነም ይማርካል» አሉ ወዳጅዋ:: «ወንዶች በእንቺ ፍቅር እንደሚነደፉ ሳያታለም የተፈታ ነው:: ይህ ደግሞ አንቺ ልታስቀሪው ወይም ልታስወግጂው የምትችዪው ነገር አይደለም::»

«ማንም ከእኔ ፍቅር ይይዘዋል ብዬ አላምንም:: እንዲህ ያለው ነገር ያለ እኔ እውቀት ሊሆን አይችልም:: እኔ ደግሞ ይህ ቢደርስ ያ ሰው ወዲያውኑ ከእኔ እንዲርቅ አደርጋለሁ» አለች ዳያን::

«ለመከላከል የማትችዪው ፍቅር ሊይዝሽ እንደሚችል ጊዜው ሲደርስ ታዪዋለሽ» አሉ ወይዘሮ ሚለር:: ከዚያም እጃቸውን ከልጅትዋ ትከሻ ላይ አሳረፉ:: «አንድ ነገር ልንገርሽ:: ይህም በሁለታችን መካከል የሚቀር ምስጢር ነው:: ልጄ ከእንቺ ፍቅር ሊይዘው ነው:: ጨርሰሽ ባል ለማግባት የማትፈልጊ ከሆነ ልጄ በብዛት ዓይንሽን ባያይ መልካም ነው::»

ዳያን ደነገጠች:: ዓይኖችዋ እንባ አቀረሩ:: «ስለነገሩኝ አመሰግናለሁ:: እንዲህ ከሆነ እኔ ከዚህ እሄዳለሁ:: ግን ከዚህ እንድጠፉ ሊረዱኝ ይፈቅዳሉ?»

«አዎን፣ ለልጄና እንዲሁ ለእንቺም ስል እረዳሻለሁ:: የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ» ባልዋት ጊዜ ዳያን ባል በማግባትዋ የደረሰባትን ስቃይ አስታወሰች:: ጋብቻ ከሚሉት ነገር ለመሸሽ የነበራት ፍላጎት ብርቱ ሆኖ ሳለ በየሄደችበት እየተከተለ አስቸገራት:: የዚህ ዓይነቱ ስሜት ባይኖራት ኖሮ በዓለም ላይ ዝናው የገነነውን አዋቂውንና ብልሁን ሰው ከማግባት ወደ ኋላ አትልም ነበር:: የሚገርመው የፊትዋ ውበት ደስታን አላስገኘላትም::

የሠዓሊው እናት የነገርዋት ነገር እውነት ቢሆንም አላዘናት እንጂ አላስደሰታትም:: ፍራንክ ሚለር ለዳያን ጥሩ ጥሩ ሥዕሎችን መሥራት የሚችል ታዋቂ ሠዓሊ እንጂ ለፍቅር ሟች መሆኑን አላሰበችውም ነበር:: ዳያንና ወይዘሮ ሚለር ጥቂት እንደ ተጫወቱ የሆዳቸውን ሳይደብቁ ያወሩ ጀመር:: ዳያን ማንኛውም ሆድዋ ውስጥ ተቀብሮ የቀረውን ምስጢር

እንኪን ለመደበት አልፈለገችም። ወይዘሮ ሚለር ለልጃቸው ያላቸው ፍቅር ምን ዓይነት እንደሆነ ዳያን ተረዳች።

«የልጅ አሳብ ምን እንደሆነ ከማንም ይበልጥ ይገባኛል» አሉ ወይዘሮ ሚለር። «አስከ ዛሬ ልጅ ፍቅር ይዞት አያውቅም። አንድ ቀን ግን እንደ ሕልም ቀስ ብሎ አካሉ ውስጥ እንደሚገባ አልጠራጠርም። ፍቅር ሲይዘው አሳቡን በሙሉ ከእዚያ ላይ ያሳርፋል። ፍቅሩ የደስታ ከሆነ ትልት ሰው እንደተባለ ነብሩ ሳይቀንስ ተደስቶ ይኖራል። አለበለዚያ በኑሮው በጣም ይዘናል። በዚህም የተነሳ ያለውን የተፈጥሮ አውቀት ሁሉ ያጣል። ስለዚህ ዘላቂ የሆነ ደስታ የማያስገኝ ፍቅር ይይዘው ይሆን? እያልኩ ዘወትር አጨነቃለሁ።»

«ወይዘሮ ሚለር በእኔ የተነሳ ልጅም እንዲነሩ አልፈልግም። ስለዚህ ከዚህ በቶሎ እሄዳለሁ» ስትላቸው «መይዘራት ቶር፣ ልጄን በምንም ዓይነት መንገድ አታገቢውም?» ሲሉ ጠየቅዋት።

«የለም፣ አልችልም» ብላ ስትመልስም «በፍጹም?» ሲሉ በድጋሚ ጠየቅዋት።

«በፍጹም» አለች ዳያን። «ሞት ወይም ሌላ ከዚያ የከፋ ስቃይ ቢደርስብኝ ይሻላል እንጂ ጋብቻ የሚሉትን ነገር አልፈልግም።»

«እንግዲያውማ አላፈተርሽውም ማለት ነዋ!»

«ማፍተር አሉ!» ብላ ዳያን ለማረጋገጥ ያህል ቃላቸውን ከደገመች በኋላ «ልጅዎን ነው የምወድደው! አዎን፣ እርስዎን እንደምወድዶት ሁሉ እርሱንም እወድደዋለሁ። እርሱን እንደ ሠዓሊዎች ልሁል፣ እንደ ጓደኛ፣ እንደ ምርጥ፣ ጥሩና ቸር ሰው እወድደዋለሁ። እርሱን ለማገልገል ሕይወቴን አሰጣለሁ። ግን ፍቅረኞች እንደሚሉት ዓይነት ፍቅር አይነካኸኝም፣ ሊሆን ደግሞ አይችልም።»

«ሳትወጅ በግድ ሰው አፍቅረሽ አታውቂም?» ብለው ወይዘሮ ሚለር ሲጠይቅዋት «የለም፣ ፍቅር ደርሶብኝ አያውቅም» አለቻቸው።

ወይዘሮ ሚለር ጥርጣሬያቸውን አረጋገጡ። ዳያን በአንድ በማይታመት ምክንያት ነፃነትዋን እንጸጣች ተገነዘቡ።

« የእኔ ልጅ» አሉ፣ «የብዙ ዓመት ታላቅሽ እሆናለሁ ። ስለዚህ አንዳንድ ነገር ልነግርሽ የምችል ይመስለኛል። በግድ ወይም በውድ አንድን ሰው ማፍተር የሰው ልጅ እጣ ክፍሉ ነው። ታዲያ አንቺ ከዚህ አንዴት ታመልጪያለሽ? ለምንስ በዚህ ዓለም ውስጥ ብቻሽን ኖሪሽ

ብቻሽን ትሞቻለሽ? ከፍቅርስ እንዴት ትለያለሽ?» በማለት ወይዘሮ ግሩ ጥያቄዎችን ደረደሩላት::

«ምክንያቱም ጨርሶ የማይቻል ነገር ስለሆነብኝ ነው» አለች ዳያን «ለማንኖውም ወንድ ቢሆን በፍቅር አልወድቅም:: እንዲያውም ስሙን መጥራቱ ራሱ ያስፈራኖል፣ ያስጠላኖል:: ሆነም ቀረም በምንም ዓይነት መንገድ ለወንድ ልጅ ፍቅር እጄን አልሰጥም::»

«ጥሩ፣ ነገሩን እንዲሁ እንዳለ ብንተወው ይሻላል:: ግን ይህ የእኔ ትንቢት ነው:: አንድ ቀን ጠዋትና ማታ የምታስቢው፣ ፍቅሩ ከጎሊናሽ ውስጥ ገብቶ የሚያስጨንቅሽ ሰው ትወጃለሽ:: ለካስ ፊትሽ በጎዘን መዋጡ በከንቱ አይደለም! ሆኖም አሁን የተጫወትነውን ለልጄ እንደማትነግሪው ተስፋ አለኝ» ሲልዋት «ይመኑኝ» አለች ዳያን በዝግታ::

«እሄዳለሁ ነው ያልሽው:: ልጄ በሰላም እንዲኖር ከዚህ የተሻለ ምርጫ የለም:: ብርቱ ፍቅር ሳይዘው ከዚህ ከሄድሽ በቀላሉ ይረሳሻል:: እዚህ ከቆየሽ ግን ፍቅሩ ስር ይሰድና ፍቅርሽን ለመንቀል እጅግ ያስቸግረዋል::»

«ግድ የለም፣ እሄዳለሁ» አለች ዳያን:: ወይዘሮ ሚለር ጨዋታቸውን ቀጠሉ:: «እንድረዳሽ ከፈቀድሽልኝ ጓደኞቼን አጠያይቄ ሥራ አፈላ ልግልሻለሁ:: ግን ይህን ባደርግ ደስ ይልሻል?»

«አዎን፣ ደስ ያለዎትን ያድርጉልኝ» አለች ዳያን:: «ነገር ግን ያ የተለመደው ጥያቄ የሥራ በር እንደሚዘጋብኝ አልጠራጠርም:: ገና ስሜ ሲጠራ 'ዋስ የሚሆንሽ ዘመድ ወይም ወዳጅ ማነው'? ተብሎ መጠየቁ አይቀሬ ነው::»

«የለም! ካሁን በኋላ እንኳን በዚህ ጉዳይ አትቸገሪም» አሉ ወይዘሮ ሚለር:: «ከእኔ የተሻለ ተያዥ የምታገኝ አይመስለኝም:: እኔ ምን ጊዜም ቢሆን አፈቅርሻለሁ፣ ሁልጊዜም ደግሞ ወዳጅሽ እሆናለሁ::»

ዳያን ከእዚያ ቤት ብትቆይ እጅግ ደስ ይላት ነበር:: ግን አልሆነም፣ ዳያን ከዚያ ቤት ወጣች:: ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ቀን ጠዋት ወይዘሮ ሚለር ዳያንን ስለፈለግዋት መልእክተኛ በመላካቸው ዳያን ወደ ቤታቸው ሄደች::

«እርግጠኛ ነኝ ደስ ይልሻል» አሉ ወዳጅዋ:: «እመቤት ክራይተን ደንጊጡር ትፈልጋለች:: አንቺ ደግሞ እንደምትሰማሚያት ግልጡላታ ለሁ:: እርሷም ደስ ያላት መስሉኖል! ከጤትዋ ትጠብቅሻለች::»

«እንዴት ያሉ ሴት ናቸው?» ስትል ዳያን ጠየቀች::

«እመቤት ክራይተንን እንደምታፈቅሪ አልጠራጠርም። ዕድሜዋ ሠላሳ አምስት ዓመት ሲሆን ባል የላትም። እጅግ ብልህ ሴት ናት። እመቤት ክራይተን ያልተባረከ ጋብቻ ከገጠማቸው ሴቶች መካከል የመጀመሪያውን ደረሽ ላትይዝ አትቀርም። ዝርዝር ሁኔታውን አላውቅም፣ ግን በኑሮዋ ተደሳች አይደለችም ሲልዋት» «እና አሁን ብቻቸውን ነው የሚኖሩት?» አለች ጸያን ጓዘን እየተሰማት።

«አዎን» አሉ ወይዘሮ ሚለር፣ «ነባ ሴት ናት። ከእንግዲህ ወዲህም ባል የምታገባ አይመስለኝም። እኔም በሁለተኛ ጋብቻ ስለማላምን ጸግም ባል አላገባም በማለትዋ አልነቅፋትም። ወደ ውጭ አገር ስለምትሄድ አብራት የምትሄድ ወጣት ሴት ትፈልጋለች። ከእርሰዋ ጋር ደስ ብሎሽ የምትኖሪ ይመስለኛል» በማለት የተሰማቸውን ሲገልጹላት ጸያን «ከአናንተ ጋር ብቀመጥ በይበልጥ ደስ ይለኝ ነበር፣ ቢሆንም ወደ እመቤት ክራይተን ቤት ዛሬውኑ እሄዳለሁ» ትላለች ጸያን።

ጸያን ወደ እመቤቲቱ ቤት ሄደች። እመቤት ክራይተን መልከጥራ ሴት ሲሆኑ ደም ግባታቸው ግን ደስ ይላል። ግርማቸው ያስፈራል። ፊታቸውን አተኩረው ሲመለከቱት ግን የዋህ ይመስላሉ።

«እንቺ ነሽ.....? » በማለት መድፈር አትቷቸው ጥያቄያቸውን ያቋርጣሉ።

«ወይዘሪት ቶርፔ እባላለሁ» አለች ጸያን። «ሊያነጋግሩኝ መፈለግ ምን ወይዘሮ ሚለር ነገረውኛል።»

«አዎን ልክ ነሽ፣ አልተሳሳትሽም። አብሮኝ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ሰው አፈልጋለሁ። የዚህ ዓይነት ሥራ ይስማማሻል?»

«ይስማማኛል፣ እንዲያውም ይህን ዓይነት ሥራ አወድዳለሁ» ስትል ጸያን መለሰች።

«የእንግሊዝን አገር ለቅቄ ለመውጣት አቅሻለሁ። ከእዚህ ብዙም ደስ ብሎኝ አይደልም የምኖረው። ለጥቂት ጊዜ ጣሊያን አገር ውስጥ ለመቀመጥ ፈልጌአለሁና ይህስ ይስማማሻል?»

የጸያን ፊት ወገግ አለ። «ይስማማሻል?» ስትል ጥያቄአቸውን ደገመች። «በጣም የምፈልገው ነገር በመሆኑ እውነት አልመሰለኝም። ሕፃን ሳለሁ ጣሊያን አገር ኖሬአለሁ።»

በጸያን የጋለ ስሜት እመቤት ክራይተን ይደሰታሉ። «እጅግ የተከፋሁ ሴት ስለሆንኩ ምናልባት ጣሊያን አገር ብሄድ የተፈጥሮንና ሰው ሠራሽ

ውበትን በማየት ይሻለኝ ይሆናል ብዬ ነው:: ምን ይመስልሻል?»

«እምን፣ ጣልያን አገር የጠራ ሰማይ በጉልህ ይታያል:: የፀሐይ ወርቃማ ቀለም፣ የአበቦች መዓዛና እዚያ የሚታየው የሥነ ጥበብ ምርት ዓለም የሚመስጥ ስለሆነ ከእዚያ ቦታ ደስታ ይጠፋል ማለት ያጠራጥራል::»

«ፈረንሳይኖና ጣልያንኛ መናገር ትችያለሽ?» ብለው ሲጠይቋት «ሁለቱንም ቋንቋዎች ከልጅነቴ ጀምሬ የምናገራቸው ናቸው» ስትላ መለሰች:: እመቤት ከራይተን ቀና ብለው ተመለከትዋት::

«ወይዘሪት ቶርፔ ይቅርታ አድርጊልኝና በጣም ልጅ ነሽ፣ ለቁንጅ ናሽም ወደር የለውም:: ቆንጆ በመሆንሽ ደግሞ በዚህ ዓለም ውበትና በሥጋ ፍላጎት በቀላሉ ትደለያለሽ የሚል እምነት አለኝ:: እኔ አገሬን ለቅቄ የምሄደው ሰላምንና ብቸኝነትን ፈልጌ ነው:: ታዲያ የብቸኝነት ኑሮስ እንዴት ነው? ይስማማሻል?»

«እምን፣ ከእዚህ የተሻለም የምፈልገው ነገር የለም» ስትል ጳያን መለሰች::

«እዚህ ከመምጣትሽ በፊት ስለውበትሽና ስለገብዝናሽ ወይዘሮ ሚለር ነግራኛለች:: ግን ከእኔ ጋር ብዙ የምትቆይ ይመስልሻል?» ባልዋት ጊዜ «እመቤቴ እስከ ፈቀዱልኝ ድረስ ለመቆየት ፈቃደኛ ነኝ» አለች::

«ይህን የጠየትኩበት ምክንያት ተሉ ባል ታገቢያለሽ ብዬ በመጠርጠሬ ነው::»

«ባል ታገቢያለሽ!» በማለት ጳያን ጣልቃ ገባች:: «እባክዎትን ይህን ነገር ዳግም ባያነሱብኝ ደስ ይለኛል:: ጋብቻን ምን ያህል እንደምጠላ ከእሁኑ እንዲያውቁልኝ እፈልጋለሁ::»

«እኔም ያለኝ ስሜት ይኸው ነው» አሉ ሴትዮዋ:: «ታዲያ ጋብቻን የጠላሁበት ምክንያት አለኝ:: እንቺ ግን ምናልባት መጥፎ ነው ብለሽ ታስቢ ይሆናል እንጂ የተለየ ምክንያት ሊኖርሽ አይችልም:: እኔ ግን መጥፎ አጋጣሚ ደርሶብኝ ነው::»

ጳያን የእመቤት ከራይተንን ፊት አተኩራ በመመለከት «ብዙ ሰዎች ሌላውን ለመምሰል ብለው የማያምኑበትን ነገር ይተባጥራሉ:: ግን እኔ ከልቢ ነው፣ ይመኑኝ:: ባል ታገባለች ብለው አይጠርጥሩ» አለች::

«አነጋግርሽ አስደስቶኛል:: እኔ ብዙ ችግር ያሳለፍኩ ሴት ነኝ:: አሁን ሰጥቂት ጊዜ እንኳን ቢሆን የብቸኝነትና የሰላም ኑሮ ነው የምፈልገው:: አሁንም ደስ የሚያሰኝና የሚያጫውተኝ ጓደኛ ባገኝ እጅግ እወድጓለሁ::

በወጣትነት ወይም በጥቅር የተነሳ ግን ከምንም ዓይነት ውዝግብ እንድገባ አልፈቅድም። ሁሉንም ነገር በደምብ አዘጋጅቼአለሁ። ግን አንደ ጓደኛ አድርጌ የመሰድኳት ደንገጡር ጥላኝ ብትጠፋ በይበልጥ ያስከፋኛል። ለማለት የፈለግሁት ነገር እንደገባሽ ተስፋ አደርጋለሁ። ኑርዬ ወንዶች፣ ጥቅርና ጋብቻ ከሚልዋቸው ነገሮች የራቀ እንዲሆን ምኞቴ ነው።»

«እንግዲያውስ እኔንና እርስዎን ያገናኘን አንድ የተለየ ኃይል ሳይሆን አይቀርም። እኔም የምፈልገው ይኸው ነው» አለች ዳያን።

«እንዲህ ከሆነስ ሰለዝርዝር ሁኔታው እንነጋገር። በሚቀጥለው ሳምንት ከእኔ ጋር ወደ ጣሊያን አገር ለመሄድ ትችያለሽ?» ብለው ሲጠይቋት «የሚያግደኝ ነገር የለም» በማለትዋ እመቤት ከራይተን ብድግ ብለው ዳያንን ጨበጥዋት።

«ከእሁን ጀምሮ አብረን መኖራችን ስለሆነ እኔን ለማፍቀርና ከእኔ ጋር በደስታ ለመኖር መሞከር አለብሽ። ፈታዱ ከሆነ ለረጅም ጊዜ አብረን ሳንቀመጥ አንቀርም። ሁለት ሰዎች አብረው ሲቀመጡ ደግሞ አንዱ በሌላው ተደስቶ ሲያዩት እጅግ ያስቀናል።» ከአንድ ሳምንት በኋላ እመቤቲቱና ዳያን ወደ ጣሊያን አገር ጉዞ ጀመሩ።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

አርአያ የምትሆን ሚስት

ሁለቱ ሴቶች ጣልያን አገር እያሉ ሁለቱም ያለፈውን ችግሮቻቸውን ረስተው በሰላም ለመኖር ሞከሩ። አርኖ ከተባለ ወንዝ ዳርቻ ቤት ተከራዩ። የተከራዩት ቤት እጅግ ሰፊና በአበባ ያጌጠ ግቢና ብዙ ክፍሎች አሉት። እቤት ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ ሲወጡ እመቤት ከራይተን ዳያንን ከአርሳቸው አይለዩም።

ጣልያን አገር ዳያን በኑሮዋ እጅግ ተደሰተች። የዳያን ኑሮና ሁናቴ መለወጥ በቅርብ ለተመለከተው እጅግ አስገራሚ ነበር። ከጊዜ በኋላ የጥንት መልክዋ እየተመለሰና ጎዘንዋ እየተረሳት ሄደ። ሆኖም አልፎ አልፎ የልጅዋ ትዝታ በመኝታ ጊዜ እንኳን ከአንቅልፍ ይቀሰቅሳታል። በዚህም የተነሳ የባልዋና የእጎቱ የሄስተር ጭካኔና የልጅዋ በአነርሱ ምክንያት መሞት ትዝ ሲላት የነበራትን ደስታ በመጠኑም ቢሆን ይቀንሰዋል። ነገር ግን ይህም

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተራሳና ትዝታው እየመነመነ ይሄዳል። ጳጉ
ቤትዋንና ባልዋን ጥላ በመሄድዋ በደል የፈጸመች ስላልመሰላት የገሊና
ወቀሳ አልነበረባትም። እርስዋ ያየችው ጭካኔያቸውና የምትወድዳቸውን
ልጅዋን መግደላቸውን ብቻ ነበር። የሠራችው ሥራ ጥፋት መሆኑን
እንኳን ብትጠየቅ ምንም ጥፋት እንደሌለባት ትናገራለች። ግን አንድ ቀን
የእመቤት ከራይተን ዘመድ ልትጠይቃቸው መጥታ ከዚህች ሴት ጋር
ብቻቸውን ሲቀመጡ የወሰደችው እርምጃ ስሕተት መሆኑን ትገነዘባለች።

«እመቤት ከራይተን ተደስታ በማየቴ እጅግ ነው ደስ ያለኝ» አለች
እመቤት ካርተር። «ታሪክዋ በዓለም ላይ ከደረሱት አሰቃቂ ድርጊቶች
በሙሉ የከፋ በመሆኑ ስሜትዋን ለመለወጥ አትችልም የሚል እምነት
ነበረኝ። በልጅነትዋ በጣም ቆንጆ ነበረች። አሥራ ሰባት ዓመት ሲሆናት
ሪቻርድ ፔትሪል ከተባለ ሰው ፍቅር ያዛት፣ እርሱም አፈቀራት። ግን ፍቅ
ራቸው በእጭር ተቀጨ። የእመቤት ከራይተን እናት ስለሁለቱ ልጆች
ፍቅር ሰሙ። እናቷ ከፍቅረኛዋና ከርሳቸው አንደኛቸውን እንድትመርጥ
ጠየቅዋት። እሷም እናትዋን ትወድ ስለነበር እናትዋን መረጠች። ስለዚህ
ሪቻርድን ተወችው። ይህ ሰው ምን እንደነካው ሳያውቅ ጎሊናውን እንደ
ሳተና ራሱን እንደረሳ ሰምቻለሁ። በመጨረሻ ግን እንዲት የማትረባ ሴት
አገባ ነው የተባለው» ስትላት «ራሱን መርሳቱ ለፍቅር ብሎ ነው» አለች
ጳያን በዝግታ።

«አዎን፣ ለእውነተኛ ፍቅር ብሎ ነው ልጄ። ከዚያ በኋላ ጓደኛዩ
ሱርድ ከራይተንን እንድታገባ እናትዋ አስገደድዋት። ይህ ሰው ምንም
እንኳን የኑሮ ዓላማ የሌለው ጹርዬና ቀላዋጭ ቢሆንም እናትዋን ለማስደሰት
ስትል አገባችው። ታዲያ ከዚህ ሰው ጋር የኖረችው ኑሮ የስቃይና የመከራ
ነበር። እርስዋ ሁሉንም ነገር ችላ ዝም ስትል ዝምታዋ ያናድደዋል። ጠዋ
ትና ማታ እንደ ከብት ይቀጠቅጣታል። ብዙ ጊዜ 'ዛራስ በምንም ዓይነት
ከሞት አታመልጥም' እስኪባል ድረስ ይደበድባት ነበር።»

«ታዲያ ለምን ቤቱን ጥላለት አልሄደችም?» ብላ ጳያን ስትናገር
«ከልብሽ እንጻልሆነ እርግጠኛ ነኝ። ሁለት ሰዎች በጋብቻ ከተሳሰሩ በኋላ
አንዱ ሌላውን ጥሎ ሊሄድ አይችልም» አለቻት። ጳያን ተገርማ ቀና ብላ
አየቻት።

«በምንም መንገድ ሊለያዩ አይችሉም ማለት ነው? እንዲት ሊሆን
ይችላል? ብዙ ሰዎች ተጋብተው ከጊዜ በኋላ ይፋቱ የለም እንዴ?» ስትል
ጠየቀች ጳያን።

«እውነትኛ ያልሆኑትና የትዳርን ምንነት የማያውቁ ብቻ ናቸው ርግጠኞች። ሰድሜሽን በሙሉ አብረሽ ለመኖር ቃል የገባሽለትን ሰው ጥሰሽ መሄድ አትችዪም፣ መሐላውም አይፈርስም። ድንገት ችግር ቢያጋጥ ግ እንኳን ሞት እስከ ገላገለሽ ድረስ መታገል ብቻ ነው ያለብሽ» ብላ ሰጋጅዋ ስትናገር «እርስዎ ያሉትን ለመከተል ከባድ ነገር ይመስለኛል» አላች ዳያን አሁንም በዝግታ።

«በእርግጥ ለመፈጸም የሚያስችገር ብርቱ ነገር ቢሆንም የሚሻለው ግ መንገድ ነው። ይህ ደግሞ ማንኛዋም ሴት የማንኛውንም ወንድ ል ለመማረክ ያስችላታል፣ የመንፈስ ደስታም ያጎናጽፋታል። ይህን ል ተከተለ ግን ሁለቱንም ያጣል።»

«የሆነው ቢሆን ሴት እንድትሰቃይ የሚፈልግ ሰው ያለ አይመስለ ኝም» አለች ዳያን። «እንዲት ሴት ኑሮዋ አስፈሪ መስሉ ከታያት ከባልዋ ር መቀመጥዋ ትርጉም የለውም።»

«ላይሆን ይችላል ወይዘሪት ቱርቴ። ፍርድ ለመስጠት አልችልም። ስለጋብቻ ያለሽ አስተያየት ያረጀና ማንም ሊቀበለው የማይችል አሮጌ አሳብ ነው ትዪኝ ይሆናል፤ ሆኖም አምንበታለሁ። እመቤት ክራይተን ለሴቶች ሁሉ አርአያ የምትሆን ሚስት ነበረች።»

«በእመቤት ክራይተን ላይ የደረሰው ሁሉ በእኔም ላይ ደርሷል» በማለት ዳያን ታስባለች። ሆኖም «እርሷ የወሰድችው ነው ወይስ እኔ የወሰድኩት እርምጃ ትክክል?» ስትል ራስዋን ትጠይቃለች። ከዚያም «እመቤት ካርተር ምን ያህል እንደ ተሰቃየሁ ባለማወቅዋ ነው» በማለት ራስዋን አጽናናች። ቢሆንም ግን የሠራሁት ሥራና የወሰድኩት እርምጃ ልክ ነው ወይስ ስሕተት በማለት ጥርጣሬ የገባት በዚያች ትጽበት ብቻ ነበር።

አንድ ቀን ዳያን በጠዋት ትነሳለች። ይህ ቀን የእውነተኛ ሥቃይ መጀመሪያ እንደ ነበር ከብዙ ጊዜ በኋላ ታስታውሰዋለች። በዚህ ቀን ፀሐይ የብርሃን ፈገግታዋን በሰፈው አበርክታለች። ወፎች መንፈስን የሚመስጥ ዝማሬያቸውን ያሰማሉ። አየሩ በአበቦች ሽታ ታጥኖ መዓዛው ልብን ያማርካል። ዳያን ይህን የተፈጥሮ ውበት እያሰላሰለች «ከመሞት መሰንበት ይሻላል፣ መኖር ግን እንዴት ጥሩ ነው» ስትል አሰበታስባለች። የተፈጥሮን ውበት በአድናቆት በመለኮት እየተመለከተች መዝሙር ትዘምራለች። የዚያን ዓይነት መዝሙር ካዜመዘች ብዙ ዘመናት አልፈዋል። መዝሙሩን አያዜመች ሳለ የቁርስ ሰዓት ደርሶ ደወል ይደወላል። ዳያን ወደ ምድር

ቤት ሮጠች:: እመቤት ከራይተን ከምግብ ቤት ውስጥ ደብዳቤ በእጃቸ
ይዘው ፈገግታ እየታየባቸው ቁጭ ብለዋል::

«እንደምን አደርሽ ሚስ ቱርፔ? አንድ ትንሽ የሚያሳስብ ደብዳ
ደርሶኝ እርሱን እያነበብኩ ነው» አሉ እመቤት ከራይተን::

«ታዲያ እኔ የምረዳዎት ነገር አለ?» ሰትል ዳያን ጠየቀች

«አዎን ልትረጂኝ ትችያለሽ:: ደብዳቤው የተላከው ከሩት ዘመ
ነው:: ዝምድናችን በእናቴ በኩል ሲሆን ይህ ሰው ከዚህ በፊት ስለእኔ
ሆነ ስለቀድሞ ባለቤቴ ቤተሰብ ደንታ አልነበረውም:: እንዲያውም
ትዳር ይዤ ሳለ አይጠይቀኝም ነበር:: ታዲያ እሁን በመጨረሻ ደብዳ
ጻፈልኝ:: ዓለምን ዙር የመሳብኝት አባዜ ስለተጠናወተው ዓለምን ሲዞር
ነው የሚኖ ረው:: አሁን ደግሞ በቅርቡ ወደዚህ አገር እመጣለሁ ብሎ
ነው የጻፈልኝ::»

«ወደዚህ ወደ ፍሎሬንስ ነው የሚመጡት?» ሰትል ዳያን ጠየቀች

«አዎን፣ የሚመጣውም ብዙ ስለተራራቅን እኔን ለመጠየቅ ነው
ሲልዋት «ይቅርታ ያድርጉልኝና ታዲያ ይሄ ምን ያሳስባል?» ብላ ዳያ
ስትጠይቅ እመቤት ከራይተን ይስቃሉ::

«ይህን ጥያቄ የጠየቅሽው የሉርድ ከርስተንን ጠባይ ባለማወቅሽ
ነው:: አውሮፓ ውስጥ ኩሩ ከሚባሉትና ተፈጥሮ እሙቱት ከቸረቻቸው
ሰዎች አንዱ ስለሆነ ተደስቶ እንዲሄድ ምን ላደርግ እችላለሁ አያልኩ ነው
የተጨነቅሁት::»

«እስከ ዛሬ እንደ ተመለከትኩዎት ከሆነ ማንንም ለማስተናገድና አስ
ደስተው ለመስደድ የሚችሉ ሴት ናት» አለች ዳያን::

«እኔ በተፈጥሮዬ ድንጉጥ ነኝ» አሉ እመቤት ከራይተን:: «እርሱና እኔ
ልጆች ሆነን ስንጫወት በጣም እፈራው ነበር» ባልዎት ጊዜ «እኚህ ሰው
ከሌሎች ሰዎች የተለየ ጠባይ ነው እንዴ ያላቸው እስከዚህ የሚፈሩት?»
ስትል ጠየቀቻቸው::

«አዎን፣ ጠባዩ ትንሽ ለየት ያለ ነው:: የእርሱን ጠባይ ሙሉ በሙሉ
ለመገለጽ ብችል ደስ ይለኝ ነበር:: ኋላቺም የእርሱን ጠባይ በሙሉ
ብችሰሚ ከመደነቅ ወደ ኋላ አትዪም ነበር::»

«በመጠኑ እንኳን ቢሆን ቢነግሩኝ?» ስትላቸው «ጥሩ፣ ከማንም
የሚበልጥ ደፋርና ታማኝ ሰው ነው :: ለእውነት የሚሞት ሲሆን በሰው
ላይ ተንኮል የመሥራት ዝንባሌ አይነካውም:: የሰው ጠባይ በተላሉ

ይገባዋል። ሰውን ደግሞ በኃይል ያምናል። ግን አንድ ጊዜ ካታለልሽው ሁለተኛ አይጠጋሽም» አያሉ አመቢት ከራይተን ሲያጫውታት ጸያን ስሚት ስጥቷት አፍጥን ከፍታ ትሰግለች። በዚህ ጊዜ ጸያን «እውነትም ጠባያቸው ትንሽ ከሊላው ሰው የተለየ ነው» ትላለች።

«በእርግጥ እንደ ሉርድ ከርስተን ያለ ሰው አላየሁም። አንድ ሰው ደፍሮ ሄዶ 'ሰው ገድያለሁ' ብሎ ቢነግረው ነገሩን ተመልክቶ በቶሎ ይቅርታ ያደርግለታል። ግን አንድ ሰው ውሽት ከተናገረ ይቅርታን አያውትም። ጥሩትን፣ ወንጀልንና የመሳሰሉትን ሁሉ በተሳሉ ሊረዳና ምክረት ሊያደርግ ሲችል ውሸትን፣ ክፉትን፣ ልክስክስነትንና የመሳሰሉትን በኃይል ይጠላል።»

«የሉርድ ከርስተን ጠባይ የሚረሳ አይደለም» ካለች በኋላ ጸያን ከት ብላ ሳቀች።

«ግና ምኑን ሰምተሽ፣ ቆይ ታገሽ። ሉርድ ከርስተን ጎበዝ፣ ብልህ፣ ግሩም ሠዓሊና አዋቂ ሰው ነው። ጥሩ ድምፅ፣ ጥሩ ግርማና ውበትም አለው» ሲሉ «ግን ሰው መሆናቸውን አይርሱ። ሰው እንደ መሆናቸው መጠን ደግሞ ከስሕተት ሊርቁ አይችሉም» አለች ጸያን።

«እንደ እውነቱ ከሆነ በርግጥ ስህተት ሊሠራ ይችላል። ግን ለማንኛውም ነገር ኩሩ ሲሆን በማንኛውም የሥራ ዓለም ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ለማሳየት የሚጥር ሰው ነው። ስንፍናን ለማራቅ ያለው ስሚት ብርቱ ስለሆነ ቸልተኝነት አይታይበትም። እርሱ ካለበት ክፉትና ምቀኝነት የተባሉ ነገሮች ቢርቁ ይመድዳል። ግን መጥፎ ነገር አይቶ የማለፍ ትሰግሥት የለውም።»

«እንደ አባባልዎ ከሆነ ሉርድ ከርስተን ጨዋ ሰው ይመስላሉ። ገለጻውን ቢቀጥሉልኝ ደስ ይለኛል። ቁመናቸውስ እንዴት ያለ ነው? ጠባያቸው በመጠኑም ቢሆ ገብቶኛል።»

«ከቁመቱ ዘለግ ያለ ሲሆን መልኩ እስከዚህም በውበት ባያጊጥም ደስ የሚል ፊትና ቅርጽ አለው። በፊቱ ላይ የሚታየው ፈገግታ ልብን ይመስጣል። ከዚህም በላይ አገራችን ውስጥ አሉ ከሚባሉት ሀብታሞች አንዱ ነው።»

«መቼም በእርግጥ ሉርድ ከርስተን ትዳር ይዘዋል?» ብላ ጸያን ትጠይቃለች። ግን ይህን ጥያቄ ለምን እንደ ጠየቀች ብትጠየቅ ምን ብላ እንደምትመልስ አታውቀውም። ጸያን ሳይታወቃት ፊትዋ እንሰላ መሰለ። አመቢት ከራይተን ከት ብለው ሳቁና «ትዳር ይዞአል ወይ አልሽ! ቢያገባማ

ምንም ደስ ባለኝ:: የጨዋ ልጅ በመሆኑ ሴቶችን ማስቀየም አይወድም ግን እስከ ዛሬ ድረስ ለእኔ ትሆናለች የሚላት ሴት አላጋጠመውም እንዲያውም ከሴት ፍቅር ይዘናል ብሎ ሲናገር ሰምቼው አላውቅም እና መይዘራት ቶርቼ ወደ ተነሳንበት ነጥብ እንመለስና እንዲህ ያለው ሰው እንዴት አርድጌ ነው የማስተናግደው? እስቲ መላ አምጪ::»

«እንዲህ ያድርጉላቸው ብዬ ልነግሮት አልችልም» አለች ዳያን «ግን የሰሙዬው ጠባይ አሁን እንደ ነገሩኝ ከሆነ ራሳቸውን ለማስደሰት ከሌላ ሰው እርዳታ የሚፈልጉ አይመስሉም::»

«ሉርድ ከርስተን ከዚህ ድረስ መጥቶ እኔን መጠየቁ ለእኔ ትልቅ ክብር ነው» አሉ እመቤት ከራይተን::

«እመቤት ቢሉወር የተባሉ ሴት ልጃቸውን እንዲያገባላቸው ብቻ እንደ ጣሩ ሰምቻለሁ:: ብዙ ተከታተሉት፣ ጋበዙት፣ ግን ልፋታቸው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀረ:: እመቤት ቢሉወርና ቤተሰባቸው በአሁኑ ጊዜ ከእዚህ እኛ ካለንበት መኖራቸውን ሉርድ ከርስተን አያውቅም::»

«እዚህ ናቸው እንዴ?» በማለት ዳያን ከጠየቀች በኋላ «እኔ ግን እነዚህን ሰዎች የማውቃቸው አይመስለኝም» አለች::

«አንድ ቀን ወይዘሮ ሳርተን ቤት ያየናት ልጅ ትገ አትልሽም? ያቺ እንኳን ስለራስዋ ብዙ በማውራት ያስለቸችን?» አሉ እመቤት ከራይተን::

«እርሷ ናት እንዴ የእመቤት ቢሉወር ልጅ?» ብላ ስትጠይቅ «አዎን እርሷ ናት» አሉ እመቤቲቱ:: «እንግዲህ የሉርድ ከርስተንን ልብ ለማግኘት ምን እድል እንዳላት ልትገምቺ ትችያለሽ::»

«መቼ ነው ዘመድዎ የሚመጡት?» ስትል ዳያን ጠየቀች::

«ኧረ ደብዳቤው ዘግይቶ ነው እንጂ ምናልባትም የዳፈውን ደብዳቤ ቀድሞ ሳይገባ አልቀረም:: 'ስመጣ ሚድራ ሆቴል ነው የማርፈው' ስላለ ማን ያውቃል በአሁኑ ሰዓት ከሆቴሉ ውስጥ ቁጭ ብሎ ይሆናል:: ለደብዳቤው መልስ ባለመስጠቴ ይቀየመኝ ይሆናል::»

«ምን አለ፡ ደቤዳቤያቸው ቶሎ አለመድረሱን ይገልጹላቸዋላ! ዋናው ነገር ዛሬውኑ ሄዶ መጠየቅ ነው» አለች ዳያን::

እመቤት ከራይተን ፊታቸውን ፈገግ አድርገው ቱና ብለው ዳያንን አይዋት:: «እውነትሽን ነው፤ ለማረጋገጥ ያህል ከሆቴሉ ሂጀ ብጠይቅ መልካም ነው:: አሁኑኑ እሄዳለሁ» አሉ::

ግን አመቤቲቱ በቶሎ እንዳይሄዱ አንግዶች በድንገት ሰለመጡ ያዘገይዋቸዋል። ከቤታቸው ሳይወጡ ስድስት ሰዓት ያልፋል።

«ሎርድ ከርስተን አርሱን ለማየት ወይም ሊሳሙ ቢቀር ሰው ለመላክ እንኳን ያልፈለግሁ ይመስለዋል» ይላሉ። «እራት ከእኛ ጋር ቢበላ መልካም ነው፤ የተለየ አራት መዘጋጀት ስላለበት ወጥ ቤትዋን ታንጋግሪያታለሽ?»

«የአዘዙኝን አፈጽማለሁ» አለች ጸያን። «ተደስተው ሳይዎት መንፈሴ ይረካል።»

«ወይዘሪት ቶርፔ የባለጌ ደፋር እንደማትዪኝ ተስፋ እያደረግሁ አንድ ነገር ልጠይቅሽ?»

«አርስዎ ከፈለጉ ሺህ ጊዜ የተለያዩ ነገሮች ቢጠይቁኝ ደስታዬ ነው» አለች ጸያን ስትመልስ።

«ኧረ ግድ የለም አንዱ ይበቃል። ዛሬ እንግዳችን ሲመጣ አምረሽ እንድትታዪ አፈልጋለሁ።»

«እኔና አንቺ ለረጅም ጊዜ በብቸኝነት በመኖራችን አምረን ለመታየት መጨነት ከተውን ቆይቷል።»

«በተቻለኝ መጠን አምሬ ለመታየት እሞክራለሁ» ስትል ጸያን መለሰችላቸው።

«ያቺን የሐር ሰማያዊ ቀሚስሽን፣ ያቺን አንኳን ወይዘሮ ካርተን ቤት የሄድን እለት የለበስሻትን አንድትለብሺ ነው የምፈልገው። ከጸጉርሽም ላይ አበባ አድርጊ። በቀላሉ ሊደሰት የማይችለውን ሰው ለማስደሰት መሞከራችንን አትርሺ» ሲልዋት ጸያን ሳቀች።

«አንድን ወንድ ለማስደሰት ብዬ ያጌጥኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ዛሬ ግን ለአርስዎ ስል አደርገዋለሁ።»

እመቤት ክራይተን ርቆ ወደሚገኘው ሆቴል ሄዱ። ከቤት ርቀው እስኪሄዱ ድረስ ጸያን በዓይን ተከተሉቻቸው። ስለሎርድ ከርስተን ያሏትን አሰላሰለች።

«ከልብ ወለድ መጻሕፍት ውስጥ የዚህን ዓይነት ጠባይ ስላላቸው ሰዎች አንብቤአለሁ» አለች ጸያን አርስ በራስዋ ስትነጋገር። የሆነ ስሜት አንጀትዋ ውስጥ ሰርጎ ገብቷል። ግን በመጻሕፍት ውስጥ የሚነገሩ ጥጡሮች በእርግጥ በዚህ ዓለም ውስጥ ይገኛሉ ብላ አታምንም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

የዳያን ትልቁ አደጋ

ዳያን ከቤትዋ ከወጣችና ከጥንቱ አሰፈሪና አሰቃቂ ኑሮዋ ከተላቀቀች አሥር ዓመት ሆኖዋል። ስለዚህ ሃያ ስምንት ዓመት ሆኖአታል ማለት ነው። የጥንት ኑሮዋ ትዝታ እየተረሳት ስለሄደ ውበትዋና ግርማ ከመቼውም ይበልጥ አምሮአል። ጥንት ፊትዋ ላይ ይነበብ የነበረው ጭንቀትና አሳዛኝ መልክ ጨርሶ ተወግዶአል። ያያትና የተመለከታት ሁሉ በፍቅር ይነደፋል። ያያት ወንድ ሁሉ ከእርሷ የተሻለ ቆንጆ በዓለም ላይ ትኖራለች ብሉ ለማመን ያዳግተዋል።

ዳያን በሥራዋ ትጉህ ናት። አካባቢዋን ለመምሰል ስለምትጥር ከዚህ ሥፍራ የተወለደች እንጂ ከሩቅ አገር የመጣች አትመስልም ነበር። የዳያ ውበትና ግርማ ማንንም ስለሚማርክ አንዳንድ ጊዜ እመቤት ከራይተን እርሷን እየተመለከቱ «እኔ እንዳንቺ አምሮብኝ አያውቅም፣ አንቺ ግን ለቁንጅናሽ ወደር የለውም። አንቺን ሳይ መንፈሴ ትረካለች» በማለት የዳያንን ውበት ዘወትር ያደንቃሉ። በዚህ የተነሳ ምርጥ የሆኑ ልብስ እንድትለብስ ዳያንን ያስገድዷታል።

ፍሉረንስ ውስጥ ያለው ሰው በሙሉ እነዚህን ሁለት ሴቶች ለማየት ይጓጓል። በመጀመሪያ እመቤት ከራይተን ሴትን እንጂ ወንድን አላነጋግርም በማለት ይኮላተራሉ። ከጊዜ በኋላ ግን ጠባያቸው ተለውጦ አንዳንድ ወንዶችን እየተቀበሉ ያነጋግሩ ጀመር። በዚህ ጊዜ እርሳቸው እንዳሰቡት ወንድ ሲባል ሁሉም ጨካኝ፣ ጨቋኝና ባለጌ አለመሆናቸውን አውቁ። በአንድ ወይም በሁለት ወንዶች መጥፎ ጠባይ የተነሳ ሴሎችን ማስቀየም ስሕተት መሆኑንም ተገነዘቡ። ስለዚህ እመቤት ከራይተን ከእዚያ አገር ከነበሩት ከባላቸውና ከራሳቸው ዓይኖች እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር ይገናኙና ይጠያየቁ ጀመር።

ወንዶች ደግሞ ወደ እነዚህ ሁለት ሴቶች ቤት በብዛት ይመጣሉ። የእመቤት ከራይተን እንግዳ ተቀባይነት፣ ደግነት፣ ጨዋነትና ብልህነት፣ የዳያን ውበትና ግርማ ሞገስ የሁለቱን ሴቶች ፍጹምነት አረጋገጠ።

የፍሉረንስ ባላባቶችን ያስደነቀው የዳያን ውበት ብቻ ሳይሆን ግርማ ሞገስዋና እርጋታዋ ነበር። ሁሉንም ወንዶች በእንድ ዓይን ነው የምታያቸው። በሴቶች ዘንድ ተወዳጅና ተናፋቂ ናት። ከወንዶች መራቅ በሚያስፈልግበት ጊዜ አትቀርባቸውም። አለበለዚያም በመቆጠብ ታነጋግራቸዋለች። ነገርን

እርቅ የሚፃፍት ችሎታ አላት። ለነገሮች አዝማሚያ ንቁ ስትሆን ጠባይዋ
የተዋረደ ነው። ስለዳያን ብዙ ሰምት እመቤት ክራይተን ይጠይቃሉ።
ፖሊሬንስ ውስጥ ብዙ ባላባቶች የዳያንን ፈገግታ ለማግኘትና ቢቻልም
ከእርስዋ ጋር ለመጫወት ያላቸውን ሀብት በሙሉ ይሰጡ ነበር። ግን ዳያን
ለማንም የማትበገር ሁና ያገኝዋታል።

ለእመቤት ክራይተን ግን እጎት፣ ጓደኛና እጅግ ተናፋቂ ዘመድ
ነበረች። ዳያን ወንዶችን የጠላችበትን ምክንያት እመቤት ክራይተን
ስለማያውቁ ግራ ይገባቸዋል። ዳያንን ለማግኘት የሚፈልጉ ብዙዎቹ ስለነበሩ
ፈት ባትነሳቸው በወዳጅ አጥር ትታጠር ነበር። አርስዋን ደጅ ይጠኑ
ከነበሩት ወንዶች መካከል አንዱ ምንም እንኳን ዳያን ተስፋ ልታስቆርጠው
ብትሞክርም ሊተዋት አልቻለም። የትዳር ጓደኛው እንድትሆን ደጋግሞ
ጠያቃት።

«ምነው ወንዶች ሁሉ ከዚህ ዓለም ቢጠፉ» አለች ዳያን አንድ ቀን
ብቻዋን ስታወራ። «እነሱ ካሉበት ሰላምና ደስታ ላይኖር ነው። እኔ
ስለሶልዳና መስፍን ምንም ሳላውት እንዴት ላግባሽ ብሉ ይጠይቀኛል? ምን
ብዬ ብነግረው ነው የልቤን ሊያውቅልኝ የሚችለው» እያለች ስታሰላስል
እመቤት ክራይተን ዳያን ከነበረችበት ከፍል ይገባሉ።

«ላነጋግርሽ አፈልጋለሁ» አሉ እመቤቲቱ። «አዝናለሁ፣ አንደ ወትሮው
ብቻዬን ልተር ነው መስለኝ ወይዘሪት ቱርፔ። ይኸውልሽ ይህ ደብዳቤ
ከመስፍን ሶልዳና ነው የመጣልኝ።»

«መስፍኑ ለእኔም ደብዳቤ ጽፎልኛል» አለች ዳያን ፊትዋ እንሶስላ
መስሎ።

«የትዳር ጓደኛዬ እንድትሆን ምክርሽን ለማሽልኝ አያለ ነው የጻፈልኝ»
አሉ እመቤት ክራይተን። እመቤት ክራይተን በመጓጓት ዓይን ዓይንዋን
ያያሉ።

«የእኔ ልጅ፣ ሰውዬው በጣም መልከ ቀናና ስመጥር ሲሆን ሀብቱ
የተትረፈረፈ ነው። ከዚህ ወዲያ ምን ትፈልጊያለሽ?» ብለው ሲጠይቋት
«ምንም አልፈልግም» ብላ መለሰችላቸው። «እኔን ጠይቀኝ ቢሆን ኖሮ
አቅም ኖሮኝ እምቢ ለማለት አልደርፍም ነበር» አሉ እመቤት ክራይተን
እየሳቁ። «ወይዘሪት ቱርፔ፣ አንድ ነገር ልንገርሽ። የወንዶች ጥላቻ ከእንቺ
ጋር ለረጅም ጊዜ አይቆይም። ጊዜ ሁሉንም ነገር ይሽራል። እኔ እንኳን
በእዚኑ ጊዜ ስለወንዶችና ስለጋብቻ ያለኝ ስሜት ከጥንቱ እጅግ የተለየ
ነው። ወደ እዚህ ልንመጣ ሰሞን ምን ብዬ እንደ ነገርኩሽ ትገ ይልሻል?

የተቀደሱ ወንዶችና የተባረኩ ጋብቻዎችም አሉ:: ስለዚህ ሁልጊዜ
ፍሙን ወገን ብቻ አትመልከች::»

«እመቤት ክላይተን» አለች ጳያን፣ «ሁለተኛ» ቢሆኑ ራ
አይሰጡኝም:: የተባረከ ጋብቻ ወይም የተቀደሰ ወንድ ለእኔ ቁ
አይደለም::»

«ቢሆንም መስፍኑና አንቺ ብትጋቡ ደስ ይለኝ እንደ
እንድታውቂልኝ እፈልጋለሁ:: መስፍኑ ማንንም አስደሰቶ ለማኖር የግ
ስለሆነ ለባልነት የሚመኙት ሰው ነው:: እርግጠኛ ነኝ፤ አርሱን ከማ
ሌላ የተሻለ ምርጫ አይኖርም:: በሕይወትሽ ሙሉ ከዚህ የተሻለ እ
አይገጥምሽም ብዬ እገምታለሁና ከዚህ ይበልጥ የምነግርሽ ነገር የለኝ
አብረን በቆየንበት ዘመን ከእለት እለት በይበልጥ እየወደድኩሽ
የሄድኩት:: ይህንንም የምልሽ ከልቤ ነው::»

ጳያን ሳት አለችና በኃይል እየተነፈሰች «ስለምክርም እጅግ አደ
አመሰግናታለሁ:: የትዳር ጓደኛ እንድሆነው ስለጠየቀኝ ደግሞ መስፍኑን
እንዲሁ ሳላመሰግነው አላልፍም:: ላገባው ግን አልፈቅድም» ስትል ጸ
በተኮሳተረ ቃል መለሰች::

«መቼም መስፍኑ ያዝናል» አሉ እመቤት ክራይተን:: «በእንደዚህ
ያለው ጉዳይ ላይ መወሰን ያለብሽ ራስሽ ስትሆኚ ማንም ቢሆን ጣልቃ
መግባት የለበትም:: የኋላ ኋላ ግን የሚጸጽትሽና የሚቆጭሽ አይመስ
ልሽም?»

«የለም፣ አይቆጨኝም:: የሚያጸጽት ነገርም ያለ አይመስለኝም» አለች
ጳያን እየተከዘች::

«እንግዲያውስ በቶሎ መልሱን ጻፊለት:: እንደ እርሱ ያለውን ጨዋና
ትልቅ ሰው ብዙ ሲሰቃይ ለማየት አልፈልግም» ብለው ሲመክሯት ጳያን
በአጭር ቃላት የተሞላ ደብዳቤ ጻፈችለት:: መስፍኑ ደብዳቤውን ሲያይ
እጅግ አዘነ:: ድብዳቤው በደረሰው ማግስት ፍሎረንስን ለቅቆ ወጣ:: አገር
ለቅቆ የወጣው በጳያን ምክንያት መሆኑ በአካባቢው ስለተወራ ከዚያን
ጊዜ ወዲህ ጳያን በይበልጥ ታመቀች:: መስፍን ሶልጳናን የመሰለ ቆንጆና
በአገሩ የታወቀውን ሰው አላገባም ብላ መመለሰዋ ምን ማለትዋ እንደሆነ
ሕዝቡ ሊገባው አልቻለም:: ሌላው ቀርቶ እመቤት ክራይተንን እንኳን
እጅግ አሳሰባቸው::

«ወይዘሪት ቶርፔ ይህን የመሰለ ሰው አላገባም ማለትዋ በምን
ምክንያት ይሆን?» እያሉ ዘወትር ያስላስሉ ጀመር:: ከተማው ውስጥ

ደግሞ «መስፍኑን አላገባም በማለት ያህን የመሰለ አድል ያመለጣት የትኛዋ ሴት ናት» እየተባለ ሕዝቡ እርስ በእርሱ ተጠያየቀ። ያወቅሯትም ዘቢታቸው እንድትመጣ ጋበዝዋት።

ታዲያ በዚህ መካከል ጸያን እንደ ጦር የሚወጋውንና እንደ ከሰ የሚመረውን የጥንት ኑሮዋን ረስታ ይሆን? አምን፡ ሳትረሳው አልቀረችም። ዘቢታዎችም ከሕልም ባልተሻለ ሁኔታ የተበታተኑና የመነመነ ነበር። ነገር ግን የጨለማው ዘመን አልፎ አሁን የምትኖረው በሰላም ቢሆንም ከእርሷ ያልተለየ አንድ ነገር ነበር። ይኸውም የጥንት ኑሮዋ ትዝታ እርስዋን ከፍቅርና ከጋብቻ ማቆራረጡ ነው።

ሳርችዴልን ለትቃ ከመጣች ስለቡሩጥና ስለሄስተር ሰምታ አታውቅም። መከሜት ቀርቶ ትዝ ብለዋትም አያውቁም። በአሥሩ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ጸያን ነፃነትዋን አግኝታ በደስታ ኖረች። ግን አሥርቱ ዓመታት እንጻለፉና የደስታ ዘመን ኑሮዬ ዘላቂ ነው ብላ በምታስብበት ሰዓት እጅግ ባልተጠበቀ መልኩ አሳዛኝና አስከፊ የሆነው ኑሮዋ ይጀመራል።

ምዕራፍ አሥራ ስምንት

ፍቅርዋ መውደሚያዋ

«ይቅርታ አድርጊልኝና ፀሐዩ የሚጎዳሽ አይመስልሽም?» አለ አንድ ወፍራም ድምፅ። ከእንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ ሰው ጸያን ከነበረችበት ብድግ አለች።

አየሩ በጣም ይሞቃል። የጽጌረዳና የተለያዩ አበቦች መዓዛ ከዚያ ሥፍራ ሂዱ፤ ሂዱ አያስኝም። ምንም እንኳን ምክንያቱ ጨርሶ ባይገባትም መንፈስዋ ተረብሾ እጅግ ተቅበጥብጣለች። ለዚህ ነበር ከቤት ወጥታ ለረጅም ለዓት ብቻዋን ከውጭ ከአበቦች መካከል ቁጭ ያለችው። ከአርኖ ወንዝ ዳርቻ ጀምሮ የተሠሩት እርከኖች ቀያይ አበባ በሚያብቡ ሐረ ሳች ተሸፍነዋል። ጸያን እንዲን እርከን ተደግፋ ነበር ቁጭ ያለችው። በአበቦች መካከል ቁጭ ብላ ራስዋም አበባ መምሰልዋን ግን አላስተዋለችውም ነበር። የጠራው የወንዝ ውኃ የመርመስመስ ድምፅ አያለማ መፍሰሱን እያየች የወደፊት ሕይወትዋን ስለሚለውጠው ጎበዝ ታሰላስላለች። የሰውዬው ድምፅ ከአሳብ ሕልም ሲቀሰቅሳት ከዚያ ሥፍራ ለምን ያህል ጊዜ እንደ

ተቀመጠች አልታወቃትም። ቀና ብላ ስታይ ፍቅሩ መውደሚያዋ የሆነዉ ሰው አየች።»

«ይቅርታ አለምናለሁ» አለ ሰውዬው። «ከዚህ መኖሪያሽን እንዳይ እመቤት ከራይተን ናት የላከችኝ። እኔን ወደዚህ ልካኝ ስመጣ አርሰዋ ወደ ቤት ገብታለች።»

ባርኔጣውን አውልቆ ከፊትዋ የነበረውን ሰው ብታየው እጅግ ቆንጆና ማራኪ ሆኖ አገኘችው። የቁመናው፣ የወንዳወንድነቱ፣ የሳያኑ የአፍንጫው፣ የጥርሱ፣ የጸጉሩ፣ ምኑ ቅጡ እንዲያው በደፈናው አናዝ አደንግዝ ዓይነት ወንድ ነው። ሄይን ዓይኑን ስታይ የፈገግታ መልክ አሳያት። እርሰዋም በበለጠ አተኩራ ተመለከተችው። የእርሱን ቁመናና ፊት እንድታይ ያስገደዳት ምን እንደሆነ ሊገባት አልቻለም። ግን አንድ ዓይነት ኃይል ወደዚህ ሰው እንደ ሳባት አልተጠራጠረችም። እንደ ልማድዋ ፊትዋ እንሶስላ መሰለ። ልብዋ ቱሉ ቱሉ መታ። አእምሮዋ ስለደነዘዘ የማመዛዘን ኃይልዋ ዝት አለ። የሰውዬው ድምፅ እጅግ የሚጣፍጥ ሙዚቃ መሰላት። እርሱም በበኩሉ እንዲሁ አፍጥጦ አያት። ድንገተኛ የሆነው ፍቅር መጎለቶን ጣለ፤ ኪሚስትሪውም ሠራ።

«ስለእኔ የሰማሽና እመቤት ከራይተን የነገረችሽ ይመስለኛል። ሆኖም ብትፈቅጅልኝና ራሴን ባስተዋውቅ?» ብሎ ሲጠይቃት «ሉርድ ከርስተን የሚባሉት እርስዎ ኖት?» አለችው ዳያን ረጋ ባለ መንፈስ።

«አንቺስ ወይዘሪት ቱርፔ ነው ስምሽ? እመቤት ከራይተን እንደ ገለጸችልኝ ከሆነ ወይዘሪት ቱርፔ ማለት አንቺ መሆን አለብሽ» አላት።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሰዎች በእርከኑ አድርገው ወደ ቤት ሄዱ። ዳያን ሰውነትዋ ውስጥ የተፈጠረው ለውጥና የስሜትዋ ሁኔታ ምክንያት ምን እንደሆነ ሊገባት አልቻለም። ሉርድ ከርስተን በበኩሉ በልጅትዋ መልክ ተገርሞ «እስከ ዛሬ ድረስ እንደዚህች ያለች ፍጡር አይቼ አላውቅም» እያለ አሰበ።

አብረው እየተጓዙ፣ ግን ቃል ሳይለዋወጡ ከቤት ደረሱ። እመቤት ከራይተን ከምግብ ቤት ቁጭ ብለው ይጠብቁዋቸዋል። ከምግብ በኋላ ሰዓቱ እንዴት እንዳለፈ ዳያን ለማስታወስ ሞከረች። ግን እንደ ሕልም ሆነባት እንጂ በውን ለማስታወስ አልቻለችም። ከዘበተኋላ ሉርድ ከርስተን መዝሙር ማዜም ትችል እንደሆነ ጠይቋት ስትዘምርለት በሕይወቷ ሙሉ እንደዚያ እንዳልዘመረችና እሱም እንዴት አፍጥጦ ይመለከታት እንደ ነበር ቆይቶ ቆይቶ ነው ትዝ ያላት። ስለዘመረችለት መዝሙር ከልብ

ማመስገኑም ቆይቶ ታወሳት።

«መዝሙር የምትሹዪ አልመሰለኝም ነበር፡ እመቤት ከራይተን ደግሞ ይህን አልነገረችኝም» ብሎ ሉርድ ከርስተን ሲናገር እንግዳ አከባሪዋ እመቤት ፈገግታ በተሞላበት ዓይን አየችው። ይህን ያህል ጊዜ አብረው ሲኖሩ ዳያን እንደዚያ ጥሩ አድርጋ መዘመር እንደምትችል እመቤት ከራይተን አያውቁም።

«እስክ ዛሬ መይዘራት ቱርቴ እንደዚህ አድርጋ ስትዘፍን ሰምቻት አላውቅም። ግድ የለህም፣ የተቀበረውን ኃይል ፈልቅቆ የማውጣት ኃይል ሳይኖርህ አልቀረም» አሉት ሉርድ ከርስተንን።

መብራት በርቶ ሰውዬው እያዋራት ብዙ እንደ ቆየና ስለጎበዙች ታሪክ፤ ስለጣሊያኖች ሥነ ጥበብና እንዲሁም ስለሙዚቃ ሲያጫውታት ፈትሮ መለዋወጡን እንደገለጸላት፤ ደግሞም የሰውዬው ጨዋታ ሁሉ እንደ ሕልም የታያት እንጂ እውን አልመሰል እንዳላት አስታወሰች።

«ፈትሽ ትኩር ብለው ሲያዩት የዐሐይ ብርሃን ሙታ ላይ ሲያርፍ እንደሚቀያየር ሁሉ ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣል» አላት አብረው እየተጫወቱ ሳለ። ዳያን ሳቀች እንጂ ነገሩ ሁሉ ተዘበራርቆባታል። አንድ ሰው ስለውበትዋ ሲያወራት ለመጀመሪያ ጊዜ የደስታ ስሜት ተሰማት።

ሰውዬው ከሄደ በኋላ ጊዜው በመምሸቱ ሉርድ ከርስተን ለመሰናበት እንደ ተነሳና ያረፈበት ሆቴል ራት ያሰ ስለነበር ለመሄድ መቸኮሉ ታወሳት። ከቤት ከመውጣቱ በፊት ደግሞ «ከግቢው ሳንወጣ እስክ በራፍ ብትሸኝኝ ትር ይልሻል?» ብሎ ሲጠይቃት ዳያን በአድናቆትና በመገረም መልስ ሳትሰጥ ቱና ብላ ስታየው «የጨረቃ ብርሃን ከፈትሽ ላይ አርፎ ማየቱ ስሜት ይሰጠኛል ብዬ ስለገመትሁ ነው። የአንቺን ፊት የመሰለ ቆንጆ ፊት ካየሁ በጣም ቆይቼአለሁ። የጨረቃ ብርሃን ከወርቃማው ጸጉርሽ ላይ ሲያርፍ ምን እንደሚመስል ለማየት ስላጓጓኝ ነው አብረን እንውጣ ያልኩሽ» እንዳላትም አስታወሰች።

በፈቱና በድምፁ አወራረድ እንግዳ የሆነ ብርቱ ስሜት ይነበብ ስለነበር ዳያን እምቢ የማለት አላብ ከጎሊናዋ ውስጥ አልገባም። ሁለቱ ሰዎች ተያይዘው ሲወጡ እመቤት ከራይተን አብረዋቸው ወጡ። ግቢው ውስጥ ከሚገኘው የተከረከመ ሳር መጨረሻ እንደ ደረሱ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለው አወጉ። የበታው አቀማመጥ፣ የልጅትዋ ውበትና አርቃታ ከሉርድ ከርስተን ጎሊና ውስጥ ተቀርጸ ቀረ። በደማቅ ጨረቃ ብርቱካንና የተላጠ ሽንኩርት የመሰለ ፈትዋን፣ ሐር የመሰለ ጸጉርዋን፣ ወለላ የመሰለ

ከንፈርዋን፣ ስንደዶ የመሰለ አፍንጫዋን፣ ወተት የመሰለ ጥርስዋን፣ ማሲ የመሰሉ ጣቶችዋን ተመለከተ። ውበትን ከመጠን በላይ የሚያደንቁ ሉርድ ከርስተን ላልተወሰነ ሰዓት ከአጠገብዋ ሆኖ አፍጥጦ ቢያያት በእድናቆት ከመገረም በስተቀር አይሰለቻውም ነበር። ሰውዬው ይሉኝ ያለው ሰው ሆኖ ነው እንጂ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ቢቆይ በወደደ። ቢወድ ባይወድም ዳያንን ከጎሊናው ውስጥ ቀርጾ ወደ ቤቱ መሄድ ነበረበት. ለመጀመሪያ ጊዜ በሴት ውበትና ለዛ ድምፅ ነፍሱ ተያዘች። መላ አካሉ ደንዝዞ የማሰብ ችሎታው ተቀነሰ። ያ ከፉ ሰር ሰድዶ አካል ውስጥ ሲሠርጽ እንዲሁ ነው የሚያደረገው።'

እመቤት ከራይተን የዘመዳቸውን የፍቅር ስሜት ቢገነዘቡም ለዳያን አልነገሯትም። ሉርድ ከርስተንን እንደሸኙ ወደ ቤት ተመለሱ። እመቤቲቱ ብዙ አልተናገሩም እንጂ ብዙ ታገሠዋል፣ ከዳያን ፊት የደስታ ብርሃን መፈንጠቁን፣ ዓይኗ ቦግ ማለቱንና ዝምተኛዋ ልጅ አፍ ማውጣትዋን ጭምር።

ሉርድ ከርስተን ወይዘሪት ቶርፔን ቢያፈቅር ጥሩ ምርጫ እንደሆነ ሴትዮዋ ተኝተው አሰላሰሉ። ዳያን ግን ሉርድ ከርስተን በፍቅር ይወድቅልኛል ብላ አላለመችም። ሆኖም ምን እንዳስደሰታት ሳታውቅ እጅግ ደስ አላት፣ ስሜትዋ ሁሉ ረካ። ጤናዋ የተመለሰና መንፈስዋ የታደሰ መሰላት። ሰውዬውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታየው ከፍቅር ወጥመድ ውስጥ የተዘፈቀች መሆንዋን ግን አልተገነዘበችም። ፊትዋን በመስታወት ስታይ ለምን ተብሎ ፊትዋ እንደ ፈካ፣ ዓይንዋ እንደ በራና ከንፈሮችዋ እንደ ተዋቡ ምክንያቱ አልገባትም። ሉርድ ከርስተን ሳያቋርጥ ከጎሊናዋ ውስጥ ተመላለሰ። የተናገረውንና ያደረገውን ሁሉ ከሀሊና ውስጥ ተቀርጾ ቀረ። እስከዚያን እለት ድረስ ካየቻቸው ወንዶች ጋር ስታነጻጽረው ከሁሉም ይበልጥ ጀግና ሆኖ ነው የታያት። «ነገ እንደገና አየዋለሁ» ስትል ዳያን አሰበች ለመተኛት አልጋዋ ላይ እንደ ተጋደመች።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

የጴያንን ልብ ማግኘት

ሉርድ ከርስተን ወደ ፍሎሬንስ ከመጣ ሦስት ሳምንት አለፈው። ጴያን ሙብ ፈትና መርቃማ ጸጉር ለመጀመሪያ ጊዜ ካየበት ምሽት ጀምሮ ነፍሱና ሥጋው ይህችን ሴት ይመኛል። የጴያን ኑሮ በመለወጥና ሕይወትዋ ጨለማና ሁካታ ከበዛበት አካባቢ ወጥቱ የጠራ ብርሃን ሰዳለበት ሥፍራ በመሸጋገሩ መልክዋ ከምን ጊዜም ይበልጥ የፈካበትና ያማረበት ጊዜ ስለነበር ሰውዬው በ.ያፈትራት አያሰኝርምም።

ጴያን ምንም እንኳን አሳብዋ በሙሉ ስለዚህ ሰው ቢሆንም በእርግጥ በፍትር መያዝዋን አላስተዋለችውም። ቢሆንም ሰውዬው ጠጥቱ ዓይኑን እስካቸች ድረስ ከጭንቅላትዋ ውስጥ ሊላ አሳብ አልገባ አሳት። ብቅ እስኪልላት ድረስ ሰዓት ሳይሆን ደቂቃ ቆጠረች። በየሰዓቱና በየእለቱ በእሳብ ባሕር እየሰመጠች ስትሄድ ልምድ ስላልነበራት የፍትር ዋዚማ መሆኑን አልገባትም። ብታውቅ ኖር ወዲያው ከዚህ ዓይነት ፍትር ለመራቅ እስካለም ጸርቻ ትሸሽ ነበር። እመቤት ከራይተን አድፍጠው ይታዘባሉ። ግን ይህች ሙብ ሴት ዘመጻቸውን በበለጠ ብታፈትርላቸው ደስታቸው እጥፍ ይሆናል።

ሉርድ ከርስተን ፍትሩን ለመግለጽ አጋጣሚ ይጠብቃል። እንዲያውም ዘአለካቱው «ያለ እርስዋ ለመኖር አልችልም» የሚል እምነት አድሮበታል። በፍትር መያዙን ከመጀመሪያው ቢገልጽላት ይወድ ነበር። ግን ሁኔቲዋ ስላስፈራው ነገር እንዳያበላሽ ለጥቂት ጊዜ ለመታገስ ታገሰ። የዋህነትዋንና ምንም ነገር አለማወቅዋን ስለሚያውቅ ደፍሮ ለመናገር ፍርሃት አቅም አሳጣው። በተፈጥሮው ግን ስሜት በቀላሉ የሚፈታው ዓይነት ሰው አልነበረም። ጴያን እምቢ ካለችው በዚህ ዓለም ውስጥ ለምንም ነገር ደንታ እንደማይኖረው ልቡ ጠርጥሯል። አንዳንድ ጊዜ ወድጳለች እያለ ሲደሰት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ልትወድደኝ አትችልም የሚል ጥርጣሬ እየገባው ይጨነቃል።

ከረምትና በጋ እንኳን እንደዚያ ጊዜያቸውን ጠብቀው እንደ ጴያን ደስታና ጭንቀት አልተለዋወጡም። ሉርድ ከርስተን ጴያን ከነበረችበት ክፍል ሲገባ የዓለም ብርሃን በሙሉ እንደ በራሳት ሰው ፊትዋ ሁሉ በደስታ ይፈካል። ግን ወዲያው አንዳንድ ነገር ሲናገርና አተኩሮ ሲያያት ልቡ በድንጋጤ ብዛት እስኪፈርስ ድረስ ሙሽሽ ትልበታለች። በዚህ ጊዜ

«ይህችን ሴት በፍጹም አላገኛትም» እያለ ቢጠራጠርም ትሕትና በተ
አንደበት ሴትዮዋን ማሸነፍመሙን ይቀጥላል። ደስታ የሚሰ
አላብዋን በድንገት የሚለዋወጥባትን ነገር ቀስ እያለ ያጠናል። እ
ጌታዋ ሊሆን የሚችል ጌታ የጌታ ልጅ የበታችዋ ሲሆን ጥያቄው እነ
እንደዚያ የሚንሰፈሰፍላት ሴት በእርሱ ፍቅር ተነድፋለች ወይስ ሰ
አልሰጣት? የሚል ነው።

አንድ ቀን ጠዋት «ወይዘሪት ቱርዬ» አለ ሉርድ ከርስተን፤ «እ
ከራይተን ሥራ ስለሚበዛባትና ብዙ አላብ ስለሚያስጨንቃት ስለእኔ ደ
የምታስብና በሰው አገር ብቸኛ መሆኔን የተገነዘበች አልመሰለኝም። ሪ
ከእኔ ጋር ወደ ወንዝ ወርደሽ በጀልባ ትንሽ እንድንሽራሸር ብ
ትፈቅጃለሽ? እዚያም የፀሐይ ጨረር ከውኃው ላይ አርፎ ሲያንጸ
ውኃውን አተኩረሽ ለማየት ትችይና አትችይ እንደሆነ ትሞክሪያ
እያለ ሲነግራት ፊትዋን ፈካ አድርጋ ቀና ብላ አየችው።

«በጣም ደስ ይለኛል። አሁን የጠቀስካቸውን ነገሮች ማየት ከም
ነገር በላይ አብልጬ የምወድደው ነው። ተፈጥሮን የማድነቅ ሰ
አለኝ» ስትለው ዳያንና ሉርድ ከርስተን ተያይዘው ሄዱ። ከመሄዳ
በፊት ብዙ በመኪኪል ጊዜ አሳጠፉችበትም።

«ዛሬ ደፍሬ የልቤን እገልጥላታለሁ» ሲል አሰበ። ከፊት ለፊትዋ ቁ
አለ። ውብ በነበረች በዚያች አለት ጠዋት ዳያን ምንተ-እፍረት ዋ
ፍርሃትዋን አውልቃ በመጣልዋ ስለአየቻቸው ሥዕሎች፣ ስለእነበ በቻ
መጻሕፍት፣ ስለዘመረቻቸው መዝሙሮች፣ ስለወንዙ፣ ስለዛፎቹ በሰፊው ዓ
ዓይኑን እያየች አወራችው። ሉርድ ከርስተን በግልጥነ ትዋ፣ በእውቀትዋ
በግርማ ሞገስዋ እጅግ ይመሰጣል። ስለእውነተኛ ነትዋ፣ ስለልዕልና
ስለብልህነትዋና ስለትሕትናዋ በዚያን አለት በይበልጥ አወቀ።

«ከአንቺ ጋር መጫወት እጅግ የጠራን ውሃ እንደ ማየት ያህል ነው
እኔ ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ግልጥና የዋህ ሴት ነሽ።»

ዳያን እውነትም ግልጥ ነበረች ወይስ አእምሮው በፍቅርዋ ታውሮ
ነው? ዳያን ጎሊናዋ ስለገሰጻት ከአጠገቡ ሸሸት አለች። ታዲያ እንደዚያ
የልብዋን ግልጥልጥ አድርጋ ያወራችው የአለፈውን የጨለማ ዘመን ኑሮዋን
ረስታና እርግፍ አድርጋ ጥላው አዲስ ሕይወት መጀመርዋን አወ
ይሆን?

«እኔ መቼም እድለቢስ ሰው ነኝ። ዘወትር የሚያስደነግጥሽና የሚ
ስፈራሽ ነገር እናገራለሁ» አለ ዳያን የፈራች መስሉት። የቃሉ አወራረ

እድማ መሬበሹን የሚገልጽ ስለነበር ቱና ብላ አየቸው።

«ሽረ አልፈራሁም» አለችው። «ግን ስለእኔ ጥሩነት መልካም ነገር ስትናገር ደነቀኝ። ከሌሎች ሰዎች ይበልጥ ግልጥና እውነተኛ መሆኑን አሳውቅም ነበር።»

ሎርድ ከርስተን አሁንም ግልጥነትዋ ፈገግ እንዲልና አነጋገርዋ አሳቡን ስብስብ እንዲያደርግ ረዳው። ፊቱን ዞር አድርጎ ሲያያት ዓይኑ ውስጥ የጭር ብርሃን አንጸባረቋል።

«አንድ ልታደርገልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር የሕይወት ታሪክሽን በእጭሩ እንድትነግሪኝ ነው» ብሎ ሲጠይቃት «የሕይወት ታሪክሽ!» በማለት የጠየቃትን ቃል ደገመች።

«ስለአለፈው ኑሮሽ ማለቴ ነው። ረጅም እንዳልሆነ አውቃለሁ። ቢሆንም እስከ ዛሬ ምን እንደ ሠራሽ፣ የት እንደ ነበርሽ፣ በሕይወት ዘመንሽ ምን እንደ ደረሰብሽ፣ ስለምታውቂያቸው ሰዎች ብትነግሪኝ። እንቺን በሚመለከት ማንኛውም ጥቃትን ነገር ሊያስደስተኝ እንደሚችል አትጠራጠሪ።»

ጸያን በጣም ስለደነገጠች ፊትዋ እንደ ልማዱ ተለዋወጠ። ኩምሽሽ ብላ ከአጠገቡ ስትርት የሞንቶት ስሜት ከፊትዋ ላይ በታየ ጊዜ «አበሳጨሁሽ እንዴ?» ሲል ጠየቃት። «አርግጠኛ ነኝ፣ ያልኩት ሁሉ ገብቶሻል። የሕይወት ታሪክሽን ለማወቅ መጓጓቴ ተገቢ ይመስለኛል። ደግሞም ለማንም ለመንገር የማትፈቅጂው ምስጢር እንደሌለበት አልጠራጠርም።»

ጸያን ጎሊናዋ እየተመለሰ ሄደ። «ለምንድነው ይህን ደግ ሰው የማስጨንቀው?» ስትል ራስዋን ከጠየቀች በኋላ «በሕይወቴ ውስጥ አንድ ትልቅ ችግር ደርሶብኛል። ይህም ችግር ወደ ኋላ ተመልሼ የአለፈውን ኑሮዬን እንዳላይ ያደርገኛል» አለችው።

«አይ ምስኪን! የደረሰብሽ ችግር ምን ነበር?»

«ያልተባረከና ያልተቀደሰ ጋብቻዬ» ብላ ልትናገር ስትል ድንገት አንድ ነገር አፍዋን ዘጋው። ቶሎ ብላ በሴት ፈጣን ሞንቅላት ተጠቅማና አሳብዋን ለውጣ «የአባቴ ሞት» በማለት መለሰችለት።

«ይህ ነው ያጋጠመሽ ትልቁ ችግር? ትዝታው ከኅሊናሽ ውስጥ ቢመላለስ አያስደንቅም። አባትሽን በጣም ትወጂያቸው ነበር?»

«በዓለም ላይ ከሚገኝ ነገር ሁሉ አስበልጬ ነበር የምወድደው።»

«መቼ ነው አባትሽ የተለዩሽ? የእርሳቸውን ቦታ የሚተካ ሰ
አላገኘሽም?» አለ በገቨተኛ ድምፅ።

«እርሱን የሚተካ!» በማለት ሉርድ ከርስተን የጠየቀውን ከደገሙ
በኋላ «የለም፣ ሊኖርም አይችልም» አለችው።

«ከዚያን ጊዜ ወዲህ ማንንም ወድደሽ አታውቂም?» ብሉ ሲጠይቃ
«የለም» ብላ ስትመልስለት እውነቱን እንደምትናገር ከታልዋ አወራረደ
ያስታውቅ ነበር። በዚህ ጊዜ መንፈሱ ረካ። የተናገረችው እውነት እንደሆነ
አመነ። ከዚያ በፊት ሌላ ሰው ካልወደደች አዙን እኔን ማፍቀርዋ አይቀርም
በሚል ተስፋ ራሱን አጽናና። ከዚህም በላይ መንገዱ ከባት መሆኑን
ስለተገነዘበ ደስታው እጥፍ ሆነ።

«የፍቅር ነገር ከተነሳ ስለፍቅር የምገልጽልሽ ነገር ነበር» አለ ተጣል
አድርጎ። የዳያን ሰውነት ተንቀጠቀጠ፣ ፊትዋ እንሶስላ መሰለ፣ ልብዋም
ቱሉ ቱሉ ይመታ ጀመር።

«አይ፣ ቢቀርብኝ ይሻላል» አለች ፈጥና። «ሉርድ ከርስተን ባልሰ
ማው እፈቅዳለሁ። እኔ .....»

«የአንቺን ፈቃድ መፈጸም ግዴታዬ ነው» ሲል ከውንው ጸርቻ
ደርሰው ስለነበር ከጀልባው ወረዱ። ከጀልባው ሲወርዱ ሉርድ ከርስተን
ደግፎ ያዛት። እርስዋም በበኩልዋ ከንዱን ተደፈገች። ሉርድ ከርስተን
መጠጋጋታችውን በመገንዘብ የዳያንን እጅ በኃይል ሲስም ሰውነትዋ
በሙሉ በአንድ ዓይነት ኃይል የተወረረ፣ አካልዋ ሁሉ የደነዘዘና ደምዋ
ውስጥ እሳት የተቀጣጠለ መሰላት።

«ወይዘሪት ቱርፔ፣ ስሜት የሰጠሁሽ አልመሰለኝም። ግን ልብሽን
ለማግኘት የሚቻል ከሆነ አንድ ቀን አገኘዋለሁ» ሲል አጎረመረመ።

በዚያች ሰዓት በታል ሊገልጸው ያልቻለውን ከንፈሮችዋን በመሳም
ለማለት የፈለገውን በድርጊት አሳያት። ይህም የዳያን ነፍስ ለአዲስ
ሕይወት እንዲዘጋጅ ቀሰቀሰው። ልብዋም አንድ ጊዜ በኃይል ከመታ በኋላ
ሥራውን ዘንግቶ ቀጥ ብሉ ለመቆም ቃጣው። ዳያን ስሙን ለመጥራትም
ሆነ ልትገልጸው በማትችለው ደስታ መላ ሰውነትዋ ተዋጠ። ከንፈርዋን
ከሰውዬው ከንፈር ዝግ ብላ አሳቀቀች። ከንፈርዋን ከከንፈሩ ስታላቅት
በደስታና በፍርሃት በተሸፈነ ዓይን ተመለከታት።

«ወለላዬ! ሲበዛ ዓይን አፋርና ደመቀዝቃዛ ብትሆኚም እንደ ምንም
ታግዬ አገኝሻለሁ» አለ ለራሱ ፍላጎቱን ሲናገር።

ጸያን ፍቅረኛዋን አልጠበቀችውም። ከቢት ስትደርስ ወደ ክፍልዋ ሮጣ ሄዳ ጥግ ይዛ ቆመች። ፊትዋ ቀላ፣ ፍርሃት ፍርሃት አላት። ከሉርድ ከርስተን ጋር የተፈጸመው ትብጠት ትዝ ሲላት መላ ሰውነትዋ ተረበሸ።

«ሁለተኛ ዓይኑን እንዴት አያለሁ?» ስትል ራስዋን ጠየቀች። ግን «ቶሎ ተመልሶ እንደገና ባየሁት» ስትል ተመኘች። ወጥመድ ውስጥ እንደገባች ጠፍ መውጫ ከሊለው የፍትር ወጥመድ መያዝዋን ተገነዘበች። አሁን ገና ሉርድ ከርስተንን ከልብ እንዳፈተረችው ጉልህ ሆኖ ታያት።

«እወድደዋለሁ» ስትል አጉረመረመች። ቀደም ሲል ሉርድ ከርስተን የሳመውን እጅዋን አተኩራ ከተመለከተችው በኋላ እርሷም እንደገና ምጥ አድርጋ ሳመችው። አሁንም እንደ ጋለ ነው።

«ሳላውቀው እንዴት ነው በድንገት አንጀቴን የበላው? እወድደዋለሁ፣ ግን የፍቅሬ መጨረሻ ምን ይሆን? እውነተኛ ደስታ አገኛለሁ ብዬ ያላለምኩትን!» አለች ለራስዋ።

ሉርድ ከርስተንን ከልብ አፍቅራዋለች። እስከዚያን እለት ፍቅር ማለት ምን እንደሆነ አታውቅም ነበር። «ሁለተኛ ሲመጣ እንዴት ነው የማገኘው?» እያለች ስታሰላስል ሰውዬው ከእመቤት ከራይተን ጋር ሲነጋገር ድምፁን ሰማች።

ከደብተር ወደ ደብተር የሚገለበጥ ነገር ኖሮ ከምላ በፊት ሠርታ እንደምትሰጠው ታል ገብታለት ነበር። ግን ጣቶችዋ ስለተንቀጠቀጡ እርሳስ ለመያዝ አልቻሉም። ዓይኖችዋም የደስታ እንባ ስላዘሉ እንኳን ለመጻፍ ቀለምንና ቅርጽን ለመለየት አልቻለችም። ሥራዋና አሳብዋ ከሉርድ ከርስተን አልርቅ አላት። ከወዲህ ወዲያ እየተንቆራጠጠች «እወድደዋለሁ፣ በጣም እወድደዋለሁ! አሁንስ ተገንዝቤዋለሁ፣ ፍቅር ይሆኛል» ማለት ሆነ ሥራዋ ሁሉ።

ያ ከፉ ምንም ሳይታወቅ በድንገት አንጀት ውስጥ ሲገባ የሚይዙትን አሳጥቶ ህት ህት፣ ያዝ ለቀት፣ ሰፋ-ጠበብ እያደረገ ያስጨንቃል። ጸያንንም እንዲሁ ነው ያደረጋት። ጸያን ከዚህ ጭንቀት ውስጥ እያለች የነበረችበት ክፍል ተንኪኪና ወዲያው እመቤት ከራይተን ገቡ።

በጣም ስለተቀራረቡ ሚስ ቱርቺ በማለት ፈንታ በመጀመሪያ ስምዋ ሄለን ብለው ጠርተው «ምን ትሠሪያለሽ?» ሲሉ ጠየቅዋት። ሉርድ ከርስተንን በሥራ እረዳሃለሁ ብለሽ ታል ገብተሽለታል መሰለኝ ከአሁን ተአዙን ትመጣለች እያለ ብዙ በመጠበቁ አሳዝኖኝ መምጣቱን ልንገርሽ ብዬ ነው» ሲልዋት ፊትዋ ሲቀያየርና እጅዋ ሲንቀጠቀጥ ተመለከቱ።

«ምን ሆንሽ ሃለን?» ሲሉ በመጓጓት በመጠየቃቸው «ኃይለኛ የራስ ምታ ይዞኛል» ስትል መለሰችላቸው።

«የጠዋት ፀሐይ ስለመታሽ ይሆናል» አሉ እመቤት ከራይተን «በጠዋት ፀሐይ ይዞሽ በመሀሩ በመጠኑም ቢሆን ሳልገስጸው አልቀረ ሁሉ ግን ሱርድ ከርስተን የሚሠራውን አውታለሁ የሚል ስሜት ሰላደረበት ግሳፄዬን ከምንም አልቆጠረውም።»

«እባክዎን ይቅርታ አንዲያደርግልኝ ሱርድ ከርስተንን ቢጠይቁልኝ ከሰዓት በኋላ እሠራዋለሁ ብላለች በሉልኝ!»

«እሺ፣ እነግረዋለሁ» አሉ እመቤት ከራይተን። «ሃሰን እውነትም ያመመሽ ትመስያለሽ። ዓይኖችሽ እንደ ከሞከብት ብርሃን ስለበረሩ መጋረጃዎቹን መለስ ሳድርግልሽና አረፍ በይ አስተ» አሉ።

ከምንድነው የምታርፈው? ፍቅረኛዋን ለማነጋገር እንኪን አልቻለችም። ጸያን ፍቅረኛዋን ብታነጋግርና ዓይኑን ብታይ ደስ ይላት ነበር። ግን የሆነ ነገር መንገዱን ዘጋባት። እንደዚያ ልብዋ በኃይል እየመታና አእምሮዋ እየተረበሸ እንዴት ይሆን የምታርፈው? ለማረፍ እንደ ማትችል ጥርጥር የለውም። በዚያን ሰዓት ጸያን ብቻዋን ሁና ፍቅረኛዋን ከማሰላሰል በስተቀር ሌላ ነገር አልፈለገችም። ሆኖም ግን ከብዙ መቅበጥበጥ በኋላ እንቅልፍ ወሰዶአት ኖሮ የምሳ ሰዓት በመድረሱ ተቀሰቀሰች።

የተጫጫናት ነገር ሁሉ ለቅቋትና መንፈስዋ ታድሶ ነቃች። ሱርድ ከርስተን ምሳ ተጋብዞ ስለነበር ከምግብ ቤት እንደሚገናኙ ታውቃለች። ከወንድ ፊት ስትቀርብ ልብስ አማርጣ የማታውቀዋ ሴት የምትለብሰውን ልብስ ታማርጥ ጀመር። ለዚያ ሰዓት የሚስማማውንና እጅግ የሚያምረውን ልብስ መርጣ ለበሰች። ሆኖም የሰውዬውን ቆንጆ ፊት አፍጥጣ እንደማታይና እንደማታነጋግረው ወሰነች። እንደ ጠበቀችው ሱርድ ከርስተን ከምግብ ቤት ቁጭ በማለቱ አቀረቀረች። ሱርድ ከርስተንም በደስታ መፈንደቁን ለማየት ተስ ብላ ተና ስትል ሊጨብጣት ተነሳ።

«ደህና አለመሆንሽን እመቤት ከራይተን ስትነግረኝ በጣም ነው ያዘንኩት። ጠዋት በጀልባ ስንዞር ፀሐይ ስለመታሽ ይሆን ራስሽን ያመመሽ? ይህን በቅድሚያ ማሰብ ነበረብኝ። የግሉን ጥቅም ብቻ የሚመለከት ግድ የለሽ ሰው ነው» ብለሽ እንዳልገምትሽኝ ተስፋ አደርጋለሁ።»

«አሪ አልገመትኩም» አለች ጸያን እንዳቀረቀረች።

«መቼም ቅር ተሰኝተሽብኛል?» ብሎ በጠየቃት ጊዜ «ፈጽሞ» ስትል መለሰችለት።

t.me/OLDBOOKSPDF

...እኔ እዚ ተገድጄ አንጂ ሠድኜ አይደለም» አለ። «ይቅርታ አድርጊልኝ። ቃሌን የመጠበቅ ችሎታ ካለኝ፤ ግን እንደማልችል አውቃለሁ እንጂ፤ ከአንግዲህ ወዲህ እንዲህ ያለ ስሕተት አልሠራም። የማውቀው ነገር ቢኖር እነዚያ የተሞቡ ጣቶችሽ ሰውነቴን ሲዳስሱ የለስተሳስብ ችሎታዬን እንደሚያወድሙ ነው።»

ወደ ምግብ ጠረጴዛ ይዞአት ሄዶ ከአጠገብዋ ቁጭ አለ። ግን አሁንም ቢሆን ፈትዋን ተና አድርጋ ስላላየችው ፈትዋ ምን እንደ መሰለ ለማየት አልቻለም።

«ምነው ጨከንሽ?» አሰ ዝግ ብሎ። «ይትርታ አድርጌልሃለሁ፥ ትይኖለሽ። ሆኖም በማቀርቀር የሞንተት ግርፋት ታመርጅብኛለሽ። ቀና ብለሽ እኔን ለማየት ያልፈለግሽው ምን ምክንያት ቢኖርሽ ይሆን?» ሲላት ተና ብላ አየችው። ያንን ውብ ፈት አተኩር ሲመለከት እንሶስላ በመምሰሉ ብትወድደኝ ነው የሚል ተስፋ አደረበት።

«ምላ በልተን እንጸበታን ወላ ብንል ምን ይመስልሻል?» ሲል ድምፁን ዝቅ አድርጎ ሲፈራ ሲቸር ጠየቃት።

«አልችልም፥ እመቤት ከራይተን ሥራ ስገዘጡኛል» ብላ ስትመልስለት ላት ከማለት በስተቀር ወዲያው ሌላ ቃል ለመናገር አልፈለገም። ሆኖም ትንሽ ቆየት ብሎ «እስክ በር ብትሸኝኝ» ሲላት የእመቤት ከራይተንን እጅ አጥብቃ ያዘችው። ሌላም ሴት ምላ ተጋብዛ ስለነበር ለሮድ ከርስተን ሌትዮዋ እንሂድ እስክትል ድረስ ዝም ብሎ ቆየ። ግን ሴትዮዋ ስትነሳ «እሸኝሻለሁ» ብሎ ቃል ገብቶላት ስለነበር እርሱም ብድግ አለ።

«ደህና ዋይ ጨክነሻ ሂለን» አላት በሹክሹክታ። ዓይን አራር በመሆንዋ ግን በይበልጥ ወደጻት። «ሂለን እኮ ከሴቶች ሁሉ የተለየች ናት፥ ተመሳሳይ አይገኝላትም፥ ቅንዋ የእኔ ሂለን» እያለ አሰላሰለ።

ጸያን ባለማወቅ ሰውዬውን በማየት ልታገኘው ትችል የነበረውን ደስታ መስዋዕት በማድረግዋ ትልቅ ሥራ የሠራች መሰላት። ሆኖም መሽከርመምዋ የሰውዬውን ፍቅር አጠናከረ እንጂ ሌላ ፋይዳ አላገኘ ችበትም። አላብዋ ግን ይህ አልነበረም። ለሮድ ከርስተንን ለምን በሚ ገባ እንጸላስተናገደችው ምክንያቱን አላወቀችም። ለማንኛውም ልክ የመሆንና የለመሆን ጉዳይ ሳይሆን የፍቅርዋ ጽናት ስለአስፈራት ነበር እንደዚያ የሆነችው። ለሮድ ከርስተን በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ሻይ ለመጠጣት ከአነጻያን ቤት እንደሚመጣ ታውቃለች። ወዲያው እንደ መጣ እንደ ዚያ ያለ ሻይ በከተማው ስለማይገኝ ለጣፋጭ ሻይ ብሎ ከሩቅ ቦታ

መምጣቱን ለእመቤቲቱ ሲግለጽና ሴትዬዋ ደግሞ ለእርሳቸው
ከሩት ቢታ በመምጣቱ ደስ የተሰኙ መሆናቸውን ሲነግሩት ሄን
ሁና ትሰማለች። ነገር ግን ሎርድ ከርስተን ለሻዩ ብሉ ሳይ
በጠዋት እንደመጣ ብታውቅም ስለደከማት ቁርስ ላይ እነ
በመግለጥ ሰው ትልካለች። መግደርደር የሴት ልጅ ልማድ ስለ
ግና ድምፁን ስትሰማ ሰውነትዋ ያረበሸዋል፡ የነበራትም ኃይል ተ
ለመሆኑ መግደርደር ወይስ የሆነ ነገር ይዝዋታል?

«ወይዘሪት ቱርቲን የሚያስፈራራ አንድ ዓይነት ምሥጢር ቤ
አለ መሰለኝ» ብሎ ሎርድ ከርስተን ሲናገር እመቤት ነራይተን
አይተበለትም።

«ሂለንን ማነጋገር አለብኝ» አለ ሎርድ ከርስተን። «ዛሬውኑ
የማግኘት፣ በስተቀን አልሞትም።» ግን ሁኔታውን ረጋ ብሎ ሲያ
«የጀብዛ ችኩል ተንድ ይነነሳል» አንዲሉ መጥኩሉ ጥጋ እንደሌ
ተግነዘበ።

«ይትርታ፡ ከንደኞቹ ጋር ተጠርቶ ስላለኝ ከዚህ ይበልጥ ዘ
አልችለም» አለ ሎርድ ከርስተን። «ራት ብለን ስለምንሄድ ለም
አንመለስም ሲል ለዘመዱ ነግራትለት።» ስለዚህ ለምሳ ገበታ ሲቀ
ዘመዶቹው እንደማይመጣ ለዴያን ገለጹላት።

«አሁንማ ለምጅው ነው መሰለኝ ሲቀር ቅር ይለኛል» አሉ እመቤ
ነራይተን። ዴያን በበኩልዋም ሁኑን ሙሉ ነጥቅረኛዋ ጋር እንደማትኛ
ስላወቀች ተስፋ የመቁረጥ ምልነት ታየባት። ጨርሶ በዚያው የሚቀር
መሰላት። በዚህ ጊዜ የብቸኝነት ስሜት መረራት። ከሚቀር መነ
እንዲስማት እጅግ ተመኘች። አንዳንድ ሴቶች ልክ እንደ ጥላ ናቸ
ይባላል። ሲሸሽዋቸው ይቀርባሉ፡ ሲቀርቧቸው ይሸሻሉ። ስለዚህ ሎር
ከርስተን የወሰደው አርምኛ ትክክል ነው።

«አመድዋለሁ፡ አመድዋልሁ» አለች ዴያን አርስ በራስዋ ስትነጋገ
«የአርስን ዓይን ካላየሁ ቀኑ አስፈሪና አስጨናቂ ይሆንብኛል።»

ጊዜው እየመሸ ሲሄድ እመቤት ነራይተን «ደክሞኛል ለማረፍ
አፈልጋለሁ» ሲሉ ዴያን ግን «እኔ ደግሞ እንደ ልማዴ ከንቢው ውስጥ
እንሸራሸራለሁ» ትላለች። «መጽሐፍ ከማንበብ በጠራ ጨረታ መንሸራሸር
ይበልጥ የጎሊና አረፍት ይሰጣል።»

«ልጅ ስለሆንሽና ስሜት ስለሚያጠቃሽ ሊሆን ይችላል» አሉ
እመቤቲቱ። ዴያን ከቤት ሳትርቅ ወጣ አለች። አበቦች ወደ ነበሩበትና

በአትክልቲዮው ወደማሚገኝ ወንዝ ወረደች። አነባበጪው ጸጥ ያለ ነበር።

«እኔ ፍትር» አለ አንድ ድምፅ በድንገት። «ይኸው ልሽ ሰረጅም ሰንት ከዚህ ኩሪምት ብዬ ስጠብቅሽ ነው የቆየሁት፡ በመጨረሻ ግን አገኘሁሽ» የሚል ድምፅ ስትሰማ ዳያን በድንጋጤ ቀና ብላ አየች። ግን ከሎርድ ከርስተን በስተቀር ሴላ ሰው ሊሆን አይችልም የሚል ስሚት ስላደረባት ብዙም አልደነገጠችም። ሎርድ ከርስተን በፍትር ዓይን አፍጥጠ እያየ እጅትዋን አጥብቆ ያዘ።

«ሂለን ጎሽቸና ተደብቂ አመልጠዋለሁ፡ ሊያገኝኝ አይችልም ብለሽ አስበሽ ይሆናል። ግን ሊሆንልሽ አይችልም። አንዴ እንደሆነ ስሚሻለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ የምለቅሽ አይምሰልሽ። ሂለን በተፈጥሮሽ ጨካኝ ብትሆኚም እኔን ግን አታስጨንቂኝ።»

እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙ ቀሩ። ዳያንም ብትሆን እጆችዋን ለመንጠቅ ፍላጎትም ሆነ አቅም አልነበራትም። እጇን እንደ ያዘ ቢቆይ ትመድዳለች። በፍትር መጨነት፡ የወዳጅዋ ከእዚያ ሥፍራ በድንገት መገኘትና የሌሊቱ ድምቀት በአንድ ላይ ተዳምረው እጅዋን ከሰውዬው እጅ ለማላቀት ወይም ለመንጠቅ አቅም አሳጥዋት። ሆኖም በዚያ ክፉ ወጥመድ ማለት በፍትር ምን ያህል እንደተያዘች እንዳያውትባት የተቻላትን ጥረት ሁሉ አደረገች። ፊትዋን እንዳያይ በሐይ እንደ መታው ቅጠል አንገትዋን ሰበረች።

«ይህን ያህል ጊዜ ከተያየንና አብረን ከተጨዋወትን በኋላ ይረሳኛል ብለሽ ታስቢ ይሆናል፤ ግን አይምስልሽ። ስሚትሽን ለመደበት በምታደርጊው ጥረት የምበረግግም እንዳይመስልሽ። ሂለን በጣም እወድሻለሁ። የምወድሽም በፍጹም ልቤ፡ በፍጹም ነፍሴ፡ በፍጹም ሕይወቴ ነው። እኔ የምወድሽን ያህል ማንም ሰው እስከ ዛሬ ማንኛዋንም ሴት የወደደ አይመስለኝም። አንዳንድ ወንዶችና ሴቶች በፍትር ሲተልዱ ከማንም ሰው ጋር በመዳራታቸው ‘ፍትር ያዘን’ ይላሉ። እኔ ግን የዚህ ዓይነት ሰው አይደለሁም። በሕይወቴ ዘመን ዘወትር አልመው የነበረው የምወድዳትና የእኔ ናት የምላት ሴት እንዳገኝ ነበር። ስለዚህ አሁን ለብዙ ጊዜ የጠበቅሁት ነገር ስላጋጠመኝ ማንኛውም ወንድ ሊያበረክተው የሚችለውን ያህል ፍትር ሳበረክትልሽ ትቀበይኛለሽ?» ብሎ ሲጠይቃት እነዚያ የዳያን ቆንጆ ከንፈሮች እንቀሳቀስም ስላሉ መልስ አልሰጠችውም።

«ምን ያህል እንደምወድሽ የገለጽኩልሽ በፍርሃት እየተዋጥኩ ነው። ሂለን የበላዩ በመሆንዋ ልትወድደኝ አትችልም የሚል እምነት ቢያደርብኝም፡ አትቆጣኝም የሚል ስሚት ግን ተሰርጾብኛል። ሆነም ተረም እንዳልተቆጣሽኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ተቆጣሽኝ እንዴ? ጨርሳ ባትፈልገኝ

ኖሮ ከአጠገቤ ጥሩ ትለኝ ነበር ብዬ አስብኩ። ታዲያ ይህን ባሰ
የተስፋ ጭላንጭል ከጎሊናዬ ውስጥ ተቀረጸ። ሄለን በፍጹም ልቤ
የምወድሽ። ገና በመጀመሪያ ሳይሽ ልቤን ሰንጥቀሽ ከመሳ በሙሉ
ነው የገባሽው። እንደ ገባሽም አልወጣ ብለሽ ከዚያው በመቅረትሽ ከ
ጊዜ ጀምሮ አሳቤ ሁሉ ስለአንቺ ስለሆነ ከጎሊናዬ ውስጥ ሌላ አ
ሰፍኖ አያውቅም። ሕይወቴና ነፍሴ የተመረኮዙት የአንቺን ትገዛ
ለለጋው ፍቅሬ አጸፋ በሰፈው ባይሆን እንኳን በከፈለ መልሺልኝ። ወደፊ
በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ስለአንቺ ደስታ ብቻ እኖራለሁ። ጭንቀቴን እያ
እንድትራራልኝ አጥብቄ ስጠይቅሽ የፍቅሬንም ጽናት በማብሰር ነው።

የድንጋጤ መልክ እየታየባት ቀና በማለት አተኩራ ተመለከተችኝ
እንደዚያ ያለ ፍቅር ቀደም ሲል ስለማታውቅ ብርታቴና ሀት ሀት ማለ
እጅግ አስፈራት።

«ትንሽ ብቻ ውደጂኝ ሄለን» በማለት ቀደም ሲል የጠየቀውን ጥያ
ደገመላት።

«መውደዱንማ እኔም እጅግ በጣም እወድሃለሁ» አለች ፍጹማዊ በሆነ
ፍርሃት። «መድጂ ሳይሆን ተገድጂ ነው የመደድኩህ።»

ሎርድ ከርስተን ከደስታው ብዛት ሳያውቀው «የእኔ ፍቅር፣ የእኔ
ወለላ!» ሲል አጎላመተመ። «ባትገደጂ ኖሮ ስለፍትራችን ምን ታደርጊ
ነበር?» ሲል «ምንም፣ ምንም አላደርግም ነበር» ስትል መለሰችለት።

«ታዲያ ከእኔ ፍቅር የያዘሽ እንደሆነ ምን ችግር አለ? እኔ ላንቺ
ታማኝና እውነተኛ ሰው እሆናለሁ። እስከ አለተ-ሞቴ አንቺን ብቻ
እወድዳለሁ። ስወድሽ መወደዱ ምን ያስፈራሻል?»

«አልፈራሁም፣ ምንም ለማድረግ አልችልም። ፍቅር ይይዘኛል ብዬ
አላሰብኩም ነበር» አለችው።

«አሁን ታዲያ በታ፣ አገኘሁሽ ማለት ነው? አውነት አልመሰለኝም።
ሎርድ ከርስተን እያልሽ ሳይሆን ፊሊፕ እያልሽ ጥሪኝ። እስቲ ደግሞ
እንደገና እወድሃለሁ በዪኝ።»

ሰውዬው ጮቤ መታ። ሁለት እጆችዋን ወስዶ አንገቱ ላይ ካሳረፈ
በኋላ ዓይን ዓይንዋን እያየ ግጥም አድርጎ ሳማት፣ ግንባርዋንና አፍንጫዋንም
አንዲሁ።

«ሄለን» አለ፣ «ከዚህ በፊት የሴት ፊት ስሜ አላውቅም ብልሽ ታምኝ
ኖለሽ? አንቺ የመጀመሪያዬ ነሽ። ሌላም ሴት ስለማልስም የመጨረሻዬ

ትሆናለሽ።»

ዳያን ለመጀመሪያ ጊዜ ባፈቀረችው ሰው ስለተሳሙች ለሕይወትዋ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተ መሰላት። ይህም መንፈስዋን አነቃቃው። ሰውዬው አዲስ ሕይወት ሰጣት።

«በመኖርና ሌላውን ሰው በማጥቀር ይህን ያህል ደስታ ሊገኝ መቻሉን አላሙትም ነበር» አለ ሎርድ ከርስተን። «ወይ ሂለን! ምን ዓይነት ትምህርት ነው የሰጠሽኝ» ብሎ ሲናገር ሳይታሰብ በድንገት የአንዲት ሴት ድምፅ ጀርባቸው ሌለት ጸጥታ አደፈረሰው።

እመቤት ከራይተን «ሂለን የት ነው ያለሽው? ድምፅ የሰማሁ መስሎኝ ነበር! ውዲት፣ የት ነው ያለሽው?» ሲሉ በድጋሚ ተጣሩ።

«የእመቤት ከራይተንን ዓይን ለማየት አልደፍርም» ሲል ሎርድ ከርስተን ወደ ዳያን ጆሮ ጠጋ ብሎ አንሾካሾከ። በዛሬው ቀን በዚህች በተቀደሰች ሥፍራ ከአንቺ በስተቀር ከማንም ጋር ለማውራት አልፈቅድም። አብረን መቆየታችንን አትንገሪያት፣ ነገ እመጣለሁ። የአንቺን ፊት አይቼና ድምፅሽን ሰምቼ የሌላ ሰው ዓይን ለማየትም ሆነ ድምፅ ለመስማት አያሻኝም» ካለ በኋላ እቅፍ አድርጎ የከንፈሮች ስሮች የተበጠሱ እስኪመስላት ድረስ አጥብቆ ሳማት። ትንድብዋን ፡ ፊትዋን፣ ግንባርዋንና ዓይንዋን ሲስም የዳያን ፊት እንደ ልማዱ እንሶስላ መሰለ።

«ከብዙ ዘንቀትና ትግል በኋላ ያገኘሁሽ ውቢቱ ሂለን፣ የእኔ ወለላ! የእኔ ፍቅር፣ ደኅና እደሪ። ነገ ጠዋት ፀሐይ ብቅ ስትል እኔም ብቅ እላለሁ» ብሎ ሎርድ ከርስተን ከአጠገብዋ ሄደ። የጨረቃው ብርሃን፣ የአበቦች መዓዛና የምሽት ጸጥታም አብረውት ነጎዱ። ዳያን ግን ከፍቅር ሕልምዋ ነቅታ ከዛርቲ መካከል ብቅ ብላ ከአንዱ እርከን ላይ ቆመች።

«ሂለን» በማለት እመቤት ከራይተን እንደገና ሲጣሩ በሩቁ አይዋት። «ምነው ብቻሽን ነው እንዴ የቆምሽው? የሌላ ሰው ድምፅ የሰማሁ መስሎኝ ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ እንኳን በጣም ስለመሸ ከቤት ብትገቢ ይሻላል» ሊልዋት ዳያን ወደ ቤትዋ አመራች። ከሴትዮዋ አጠገብ ስትደርስ የእፍረት ስሜት ተሰማት። እመቤት ከራይተን ደግሞ አተኩረው ተመለከትዋት። ፊትዋ እንደተላና ሰውነትዋ እንደ ወባ ነበር።

«የጨረቃው ድምቀት ይሁን ወይም የጤዛው፣ አልገባኝም እጅግ አድርጎ አቆነጀሽ» አሉ እመቤቲቱ። «የሚያሳዝነው ይህን የመሰለ ውበትሽን ተመልከቶ የሚያደንቅሽ ሰው በአሁኑ ሰዓት ካጠገብሽ አለመኖሩ ነው። ሁለታችንም ደክሞናልና ከክፍልሽ ግቢና ተኚ፣ ደኅና እደሪ።»

ትሆናለሽ።»

ዳያን ለመጀመሪያ ጊዜ ባፈተረችው ሰው ስለተሳመች ለሕይወትዋ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተ መሰላት። ይህም መንፈስዋን አነቃቃው። ሰውዬው አዲስ ሕይወት ሰጣት።

«በመኖርና ሌላውን ሰው በማፍቀር ይህን ያህል ደስታ ሊገኝ መቻሉን አላውቅም ነበር» አለ ሎርድ ከርስተን። «ወይ ሄለን! ምን ዓይነት ትምህርት ነው የሰጠሽኝ» ብሎ ሲናገር ሳይታሰብ በድንገት የአንዲት ሲት ድምፅ የዚያን ሊሊት ጸጥታ አደፈረሰው።

እመቤት ክራይተን «ሄለን የት ነው ያለሽው? ድምፅ የሰማሁ መስሎኝ ነበር! ውዲት፣ የት ነው ያለሽው?» ሲሉ በድጋሚ ተጣሩ።

«የእመቤት ክራይተንን ዓይን ለማየት አልደፍርም» ሲል ሎርድ ከርስተን ወደ ዳያን ጆሮ ጠጋ ብሎ አንሾካሾከ። በዛሬው ቀን በዚህች በተቀደሰች ሥፍራ ከአንቺ በስተቀር ከማንም ጋር ለማውራት አልፈትድም። እብረን መቆየታችንን አትንገሪያት፣ ነገ እመጣለሁ። የአንቺን ፊት አይቼና ድምፅሽን ሰምቼ የሌላ ሰው ዓይን ለማየትም ሆነ ድምፅ ለመስማት አያጓጓኝም» ካለ በኋላ አትጥ አድርጎ የከንፈሮች ስሮች የተበጠሱ እስኪመስላት ድረስ አጥብቆ ሳማት። ቅንድብዋን ፣ ፊትዋን፣ ግንባርዋንና ዓይንዋን ሲስም የዳያን ፊት እንደ ልማዱ እንሶስላ መሰለ።

«ከብዙ ውጣ ውረድና ትግል በኋላ ያገኘሁሽ ውቢቱ ሄለን፣ የእኔ ወለላ! የእኔ ፍቅር፣ ደኅና አደሪ። ነገ ጠዋት ፀሐይ ብቅ ስትል እኔም ብቅ እላለሁ» ብሎ ሎርድ ከርስተን ከአጠገብዋ ሄደ። የጨረቃው ብርሃን፣ የአበቦች መዓዛና የምሽት ጸጥታም አብረውት ነጎዱ። ዳያን ግን ከፍቅር ሕልምዋ ነቅታ ከዛፎቹ መካከል ብቅ ብሳ ከአንዱ እርከን ላይ ቆመች።

«ሄለን» በማለት እመቤት ክራይተን እንደገና ሲጣሩ በሩቁ አይዋት። «ምነው ብቻሽን ነው እንዴ የቆምሽው? የሌላ ሰው ድምፅ የሰማሁ መስሎኝ ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ እንኳን በጣም ስለመሽ ከቤት ብትገቢ ይሻላል» ሲልዋት ዳያን ወደ ቤትዋ አመራች። ከሲትዮዋ አጠገብ ስትደርስ የእፍረት ስሜት ተሰማት። እመቤት ክራይተን ደግሞ አተኩረው ተመለከትዋት። ፊትዋ እንደተላና ሰውነትዋ እንደ ወባ ነበር።

«የጨረቃው ድምቀት ይሁን ወይም የጨዛው፣ አልገባኝም እጅግ አድርጎ አቆነጇሽ» አሉ እመቤቲቱ። «የሚያሳዝነው ይህን የመሰለ ውበትሽን ተመልክቶ የሚያደንቅሽ ሰው በአሁኑ ሰዓት ካጠገብሽ አለመኖሩ ነው። ሁለታችንም ደክሞናልና ከክፍልሽ ግቢና ተኚ፣ ደኅና አደሪ።»

«አልበገር ባይዋ ዳያን በመጨረሻ ተሸንፋ ይሆን? ወይስ ገና ነው ነገሩ? አረፍት አለ አሳጣት። ከፊትዋ ሳይ ደግሞ የደስታ ፍሬ ይታያል» በማለት እያሰላሰሉ አመቤቲቱ ከክፍላቸው ገቡ።

የጠዋት ጀምበር ገና ብቅ ስትል ሎርድ ከርስተንም እንዲሁ ይላል። መምጣቱን የሚያበስር አትፍ አበባ በሥራተኞ ላከላት። ቤተ ጊዜ ከአበቦች መካከል እንደሚጠብታት አወቀች። አበቦች ወደሚገኙበት ሥፍራ ሮጠች። ፊትዋን ተና አድርጋ ያየችው እንደሆነ ምን ያህል እንደምትወድደው የሚያውቅባት ስለመሰላት እንደ ልማድዋ አቀፈቱረት እሹን ዘርግቶ ተጠጋት።

«ሃለን ድምዕሽን ካልሰማሁና ዓይንሽን ካላይሁ አረፍት አላገኝም ማታ ያደረግነው ነገር ሁሉ ሕልም ነው የመሰለኝ። እንደዚያ ያለ ደስታ በውን ሊሆን አይችልም። ሕልም አለመሆኑን ላረጋግጥ የምችለው ድምዕሽን ስታሰሚኝ ብቻ ነው።»

ዳያን ፈትዋን ወግግ አድርጋ «ሕልም አልነበረም» ስትለው «እንግዲያውማ መቼ ነው የምንጋባው? በሚተጥለው ሳምንት ከመጋባት የሚያግደን ምን ነገር አለ? ውድ ባለቤቴ የምትሆኚው መቼ ነው?» ብሉ ሲናገር ግራ ተጋባች። ጋብቻ የሚሉት ቃል ስትሰማ ዳያን በድንጋጤ ልብዋ ፈሰሰ። ዓይኖችዋ እንባ አቀረሩ፤ ታለቅስም ጀመር።

ባል ልታገባ! ሕልም ነው ወይስ ቅዠት! ምን መልስ ትስጠው? ምንም እንኳን ቢለያዩም አሁንም የቡሩኖ ሲቨርን ሚስት ናት። ሰማንያዋን ካላወረደች ሌላ ሰው ልታገባ አትችልም። ስለዚህ ድንጋጤው አይግደላት እንጂ አስደንብሮአታል። ከማስደንበርም አልፎ ክፉኛ ያስጨንቃታል። ተስፋ በመቁረጥ ተና ብላ ሎርድ ከርስተንን አየችው።

«ሃለን አስደነገጥኩሽ እንዴ? እኔ እኮ የጠየቅኩሽ 'ውድ ባለቤቴ የምትሆኚው መቼ ነው' ብዬ ነው?» ሲል ያስደነገጣትን ጥያቄ ደግሞ ጠየቃት።

እጅዋን አጣጥፉ ተና ብላ እያየችው «ምንጊዜም....ምንጊዜም ቢሆን ባለቤትህ ልሆን አልችልም» አለችው።

«ይህን ለማለት ጊዜው አልፎአል። አድልሽ እንደሆነ እንዴ ተወስኖአል። ደግሞም እወድሃለሁ ብለሽኛል። ስለዚህ እኔን ማግባት አለብሽ። እኔን ከማግባት የሚያግድሽ ነገር በዓለም ላይ ሊኖር አይችልም» ባለ ጊዜ ዳያን «እኔ እኮ ባል አለኝ» ለማለት ሞክራ አቃታት። እነዚህን ቃሎች ለመተንፈስ በቂ ጉልበት አልነበራትም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለምንድነው የሚያስገቢኝ? ፍቅር ብጋብዙ እንደሚጸናና እንደሚታሰር አውቃለሁ። እኔን ለማግባት ያልፈለጓቸበት ምክንያት ምንድነው?» ብሉ ለመለመን የሚያስከፋ መልስ አልጠበቀም። ተድናግጣ ነው ሲል አሰበ።

«ልነግርህ አልችልም። ምን ላድርግ ሎርድ ከርስተን ላገባህ አልችልም» ዓይኑ ጸያን ቃሉ እየተፈራራ መልስ ሰጠችው።

«እናያለና!» ካለ በኋላ ሎርድ ከርስተን ፈትዋን ቱና አድርጎ ሲሰግት ፈትኖ መገርጣቱን አስተዋለ።

«ሂልን፣ ከሆድሽ ውስጥ አንድ ነገር ተቀብሮ ያሰቃይሻል። ነገሩ ምን እንደሆነ ልትነግሪኝ ትፈቅጂያለሽ?» ብሉ ሲጠይቅ «አልችልም፣ ግን አምነኝ፣ በምንም ዓይነት መንገድ ባልቤትህ ልሆን አልችልም» ስትል ፈጽሚ ገለጸችለት።

ፈትዋን ቱና አድርጋ በጎዘን በተዋጠ ዓይን አፍጥጣ አየችው። ከመጠን በላይ ማዘንዋን ፈትዋ በግልጽ መሰከረ። እትፍ አድርጎ በኃይል ሲስግት ፀደ ኋላ ሸሸች።

«እንዲህ ያለውን ነገር ብንተወው፣ የትዳር ጓደኛህ ልሆን ስለማልችል ላትመኝ ይሻላል» ብላ ስትናገር «ምን ትመጂኝ የለም ሂለን?» ሲል ጠየቃት።

«አምን፣ በጣምፐ እጅግ በጣም እወድሃለሁ» አለች። «ቢሆንም ላገባህ አልችልም። «ቻለውና እንድሄድ ፍቀድልኝ።»

እጅዋን ቱስ አድርጎ ሲለቅላት ወደ ቤትዋ ሮጠች። ሎርድ ከርስተን ግራ ተጋብቶ ከቆመበት ፈገዠ ቀረ።

ምዕራፍ ሃያ

አባብሎ አግኛት

የተጠፈረችበትን ጨካኝ ሰንሰለት መርሳት እንዳለባት ባለላለች ጊዜ አላቡ ዘገነናት። ምን አሳብዶዋት ነው ከዚያ ከሚያሳብድ የፍቅር ርጥመድ ውስጥ የገባችው? ዳያን ከመስከት አጠገብ ቆማና በመስከቱ በኩል አንገትዋን ብቅ አድርጋ ባለፈው ሌሊት የኑሮና የፍቅር ጣዕም የቀመስችበትን ሥፍራ ተመለከተችው። ያንን ሥፍራ ስታይ ከሚገባው

በላይ አዘነች።

«ያሆናል ብዬ ሳሳስበው በድንገት በከፉ ፍቅር መያዜን አ
ነበር። ፍቅር እኔ እንደፈለግሁት ይሄዳል የሚል ግምት ነበረኝ
እርሱ እንደ ፈለገው ነው ሰውን ሁሉ የሚያሯሩጠውና የሚያሸነ
አሁን ገና ገባኝ» አለች ለራስዋ።

ጸያን ገና ልብዋ ከፋት ያልሰፈነበት የዋህ ከረዳ ናት። እሱ
እለት ድረስ ኑሮዋ ደስታ የተለየው የትካዜ ኑሮ ነበር። አሁን በ
የገጠማት ወር ቃማው ሕልም በጣም አስጨነቃት፣ ለመሸከም ከ
ከወደደችው ሰው መለየትዋን ስታስታውስ ሀዘንዋ መሪር ሆነ።
ያስለቅሳልና የደም እምባ አስለቀሳት። ከሎርድ ከርስቱን ጋር የ
ጨዋታ መጫወትዋና መዳራትዋ በአንድ በኩል ደስታ ሲያነሳ
በሌላ በኩል ዘላቂ ባለመሆኑ አንገበገባት። ሊታረም የማይችል ስ
መረጸምዋ በይበልጥ አሰቃያት። በቃላት ለመግለጽ በማይቻል ሁ
ሰውዬውን ትወድደዋለች። ግን አብራው ለመኖር አትችልም። ምን ዓይ
ፈተና ስቃይ ነው?

«ሚስት» የተባለውን ታላል አስከ ጠራባት ድረስ ከፍቅረኛዋ ጋ
እለያለሁ የሚል ጥርጣሬ ከነሊናዋ ውስጥ አልገባም ነበር። አሁን ግ
ከምትወድደው ሰው መለየትዋን ስለተገነዘበች እጅግ ተሰፋ ቆረጠ
ከራት ይበልጥም መረራት።

በዚያ ባልተባረከና ባልተቀደሰ ጋብቻ ባትታሠር ኖሮ ተደስታ ትኖ
ነበር። በፍቅር የጣላት ሰው ቆንጆ ከመሆኑም በላይ ረጋ ያለ ጨዋ የዉ
ልጅ ነው። ሀብትም ተትረፍርፎታል። በእርስዋ ዓይን ይህ ሰው የጎደለዉ
ነገር የለም። ከዚህም በላይ እሱም ከልብ አፍቅሮአታል። ያ ደግሞ ትልቁ
ነገር ነው። ያለውን ሀብት በሙሉ በእርስዋ ላይ ቢያጠፋ ደስታውና
ምኞቱ መሆኑን በትጠ ተገንዝባለች።

ከመጠን በላይ በምትጠላው ሰንሰለት ባትታሠር በሚተጥለው ሳምንት
የወደደችው ሰው ባለቤት በሆነች ነበር። ከዚህ ሰው ጋር አብራ ብትኖር
በዓለም ላይ ከእርስዋ የበለጠም ተደላች ሰው ላይገኝ ይችል ነበር። ከአማሪና
ከደመቀው ቤተ ገብታ ብዙ ሳታስብና ሳትጨነቅ በሰላም በኖረች።

ሀዘንዋ እየከፋና ተስፋቢስነትዋ እየከረረ ሲሄድ አንድ አሳብ ብቻ
መጣላት። ይኸውም ዳግም የወደደችውን ሰው ዓይን አለማየትና ፍቅሩ
ሸዋን ከእዚያ ሥፍራ ማባረር። ምክንያቱን ገልጣ አትነግረውም ማለት
የቡሩና ኢቨርን ሚስት መሆንዋንና የልጅዋን መሞት አትገልጽለትም።

ልትነግረኝ ያልፈለገችበትም ዋናው ምክንያት ነገሩ ከብርን የሚነካና ታክስ እጅግ ዝቅ የሚያደርግ መስሎ ስለታያት ነው።

ምሥጢሩን ቢያውቅ ደግሞ እንደዚያ ሊያፈቅራት እንደማይችል ታውቃለች። ባል ያገባችውም መጠጊያ ለማግኘት ስትል ነው ብሎ ላያምን ይችላል። በዚያን ወቅት መጠጊያ ምን ያህል ያስፈልጋት እንደነበርም ሊገነዘብ አይችልም። ታዲያ በፍቅር ላበደላት ሰው ይህን ታሪክ እንዴት ብላ ትግለጽለት!

«ታሪኬን መቼም ቢሆን እንደማያሰማ ተስፋ አደርጋለሁ። ከእኔ እንዲርቅና በምንም ዓይነት መንገድ የትዳር ዓጋሩ ልሆን እንደማልችል እነግረዋለሁ። ቢሆንም ግን ምክንያቱን አልገልጽለትም» አለች ለራስዋ በንይል እየተነፈሰች።

ከልብ እንደሚያፈቅራትና በእርስዋ ላይ ያለው ግምት ከፍተኛ መሆኑን ታውቃለች። እርሱም ከሌሎች ይበልጥ ታማኝና ግልጥ ሴት እንደሆነች ያምናል። ከዚህ ሽጋ ጠባይ ካለውና ፍቅሩ እምነቱ ስር ከሰደደ ሰው ስትለይ እጅግ እንደምትከፉ አላጣችውም። መለያየቱ እጅግ ቢያስከፋትም፣ ሌላው ቢቀር ከተለያዩ በኋላም ቢሆን፣ 'መወደድ የሚገባት ሴት ነበረች' ብሎ እንዲያስብ ፈለገች።

ስለዚህ ደብዳቤ ልትጽፍለት ቁጭ አለች። ዓይንዋ የእንባ ዝናብ እያዘነበ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አሳዛኝ ደብዳቤ ጻፈች። እጅግ በጣም እንደምትወድደው ግን ልታገባው እንደማትችል በደብዳቤዋ አሳምራ ገለጸችለት። በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ አስበልጣ እንደምትወድደውና እንደምታፈቅረውም በዝርዝር ጻፈች። ሆኖም እንዲረሳት ለመነችው። ይህ ሰው ከገሊናዋ ውስጥ ጎጆ ሰለሠራ ደስታ ከእርሱ እንዳይርቅ በማሰብ ወደፊት ጥሩ እድል ገጥሞት ተደስቶ እንዲኖር የዘወትር ምኞትዋ እንደሆነ ከደብዳቤዋ ውስጥ ጠቀሰች። ከደብዳቤው ውስጥ የሰፈረው አያንዳንዱ መስመር የፍቅርዋን ጽናት የሚያበስርና የህዘንዋን ስፋት የሚገልጽ እንደ ነበር ጸሐፊዋ አልተገነዘበችም። ከነአካቴው ደብዳቤው ማንኛውንም ብርቱ ወንድ ቢሆን በቀላሉ ሊፈታና ሊያሳብድ የሚችል ዓይነት ስለነበር 'ይህችን ሴት በፍጹም አልለቅም' የሚል ስሜት የሚፈጥርና ፍቅር እንዲያገረሽ የሚያደርግ እንጂ 'ጸሐፊዋን ተዋት፣ ትቅርብህ፣ ምን አባትዋ' የሚያሰኝ አልነበረም።

ሱርድ ከርስቱን እጅግ ግራ ተጋብቶ ፈጽሞ ሊገባው አልቻለም። ነገሩን አውጥቶና አውርዶ ሲያሰላስለው የሚይዘውንና የሚጨብጠውን አላጣው።

እርሱን መውደድዋ ግልጽ ነው። በደብዳቤዋ እርሱን ያለመውደድን ጥንድ ለማላየት አልሞከረችም። መጋባታቸውን የሚቃወም ነገር ወደፊት ሊኖር ዘመድ የላትም። አባትዋ ከሞተ ወዲህ ደግሞ ማንንም እንዳላፈቀረች ገልጻልኛለች። ታዲያ ለምን ይሆን አሳገባህም የምትለው? ለምንድነው ከእርስዋ እንድርት የፈለግኸው? ለእርስዋ ስል ሕይወቴን እንኳን ባጠፋ ትር እንደማልሰኝ ታውቃለች።

ሉርድ ከርስቱን ምክንያቱ ጠፍቶበት በአሳብ ማጥ ተቅበዝብዞ ሲዋትት ላየው እጅግ ያሳዝን ነበር። «ሲቆችን ለ.ያባብልና ወደ ጠንድ ሊያስጠጋ ይችል የነበረው ነገር እርሷን ከእኔ እንድትርቅ አድርጓታል» ሲል አሰበ። ጸያን የት እንዳለች የማትታወቅ ድንጉ ሴት ሰትሆን እርሱ ግን አገር ያወቀው ጨዋ፣ የጨዋ ልጅ ከመሆኑም በላይ ሀብቱ የተትረፈረፈ ትልቅ ሰው ነው። በለምች ዘንድ የነበረውም ክብርና ሞገስ ተላለ አይደለም። ያሸሸዋት እነዚህ በሰው ዓይን እጅግ በጣም ተራማጊ የሆኑ ነገሮች እንደሆኑ ገመተ። ስለዚህ በሁለቱ መካከል ያለው የደረጀ ልዩነት አሰፈርቻት ነሽ ያለች እንደሆነ ምናልባት ክብሯን የምትነካ መስሎአት ይሆናል በማለት ሁኔታውን አሰላሰለ። ይህ አሳብ ሲመላለት ፡ ትንሽ ፡ ተንፈስ አለ።

«መለሳቤን፣ ጥቅሬን ምን ላድርጋት?» ብሎ ራሱን ከጠየቀ በኋላ እርሷን ለማሸነፍ የመጨረሻው ጥሩ ዘዴ ትእዛዝዋን መቀበል እንደሆነ አመነ። ከወደዱት ሰው ተለይቶ መኖር ምን ያህል አሰጨናቂ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ ለአጭር ጊዜ ከእርስዋ መሰወር ነው ሲል አሰደ። ጨርሻ እንደሻውን ልተዋት የሚል አሳብ ሲመጣበት ግን ራሱን ገሰጸ።

ለአንድና ለሁለት ቀን ጸያን ከነበረችበት ቤት አልደረሰም። እንዴት እንዳስቻለው ግን ማንም ሊያውቅ አይችልም። እነዚያ ሁለት ቀኖች ለጸያን ከሙቱ ዓመታት የረዘሙ ነበሩ። «ከአጠገቤ ጥሩ ባልሽኝ መሠረት ከፍሉራንስ መሄዴ ነው» ሲል ሚስታወሻ ጻፈላት። ታዲያ ሂጻ ትሰናበተው? አስቸጋሪ ጥያቄ።

ለምስኪንዋ ጸያን ማስታወሻው መርዶ ነበር። ያ ቆንጆና ከልብ ያፈቀረችው ሰው በራስዋ ጥያቄ ከእርስዋ ተለይቶ በሀዘንና በፍንጥት መካከል ጥለአት መሄዱ ነው። ጥለአት ከሄደ ቀኑ አልር ሳምንት ሲተካ፣ ወሩ አልቆ አዲስ ዓመት ሲገባ ይህች ሴት እንዴት ነው የምትሆነው! ለአንድ ቀን እንኳን እንደዚያ የጨነቃት ወደፊት ጊዜው እንዴት ነው የሚያልፍላት!

«ጥቅሬ፣ የእኔ ጥቅር» እያለች ታነሳው ጀመር። እንደ ልማዱ ፊትዋ

እንሰማ ሙስለ። ግን «የእኔ ፍቅር» ስማለት ምን መብት አላት? የሌላ ሰው ሚስት ናት። ትክክለኛውን አትጣጫ መርጣለች። ከሰውዬው መለየት አለባት። ይህን ለመወሰን እርስዋ ያሳለፈችው ጭንቀት ምን እንደ ነበር የደረሰበት ብቻ ሊገነዘውና ሊናገር ይችላል እንጂ ማንም ሰው ትክክለኛውን ስሜት አያያም።

ሉርድ ከርስቱን ጥሏት ቀይዶ ሲመጣ ገና ፈቱን ስታይ ቁርጥ እድረጎ ወስናው የነበረው አሳብ ሁሉ በቀላሉ ተለዋወጠ። ልክ ሰብርቱ በሐይ የተጋለጠ ትቢ በቀላሉ ቀልጦ ትርጹንና መልኩን እንደሚለውጥ ሁሉ ከልብ ያፈቀረች ሴትም አሳብና ልብ እንዲሁ በቀላሉ መልኩን ይቀያይራል። በናያገም ላይ የሆነው ይኸው ነው። እስከዚያን ጊዜ ከልብ ያፈቀረችው ሰው እርሱ ብቻ ስለሆነ እንዴት አድርጋ ነው ከእርሱ የምትለየው?

ብዙ ሴቶች ከተለያዩ ወንዶች ፍቅር እየያዛቸው አንዱ ሲሄድ ሌላውን በመጠባበል ሐያጁን ይረሳሉ። ይህች ሴት ግን ከዚህ ወንድ በስተቀር ሌላ ወንድ አልወደደችም። ከፊትዋ የቆመውን ሰው በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ አብልጣ የምትወድደው ነው። ቀና ብላ ስታየው ፈቱ ከጭንቀት ግጥ ውስጥ እንደ ተዘፈቀና ዓይኖቹ ደግሞ ምን ማለትዋ ነው በማለት እንደሚገስጽዋት ተገነዘበች።

«ሂለን ልለይሽ? የኔ ፍቅር ጨክንሽ፣ አንጀትሽ ቆርጦ ታባርሪኛለሽ?» ሲል ጠየቃት።

የሉርድ ከርስቱን ዓይኖች እምባ አዝለዋል። እምቢ ያለችበትን ትክክለኛ ምክንያት ቢያውቅ ኖሮ አሁን ያደረገችውን ይደግፋል ወይም የሆነው ይሁን በማለት ከእርሱ ጋር መሆንዋን ይመርጣል።

«ግማሽ አካሌን፣ ሕይወቴን፣ ነፍሴን፣ ደስታዬን፣ ከእንቺው ጋር ትቻቸው ልሂድ? እንለያይ?» ሲል በጠየቃት ጊዜ ጸያን ዓይን ዓይኑን እያየች እጆችዋን ዘርግታ መላ ሰውነትዋን ከደረቱ ላይ አሳረፈች። «መሄድ አለብህ» አለች እየተንሰቀሰቀች።

«መሄድ አለብህ፤ ግን...ብቻ...ጨክኜ...ልሰድህ...አልፈቅድም። ከእንተ ልለይ አልችልም። የእኔ ፍቅር፣ የእኔ መለሳ» በማለት የተምታታ ንግግር ተናገረች። ይህን እንደ ተናገረች ከብብቱ ሥር አስገብቶ እቅፍ አደረጋት። በኩላ እንደ ተጣበቀ እንጨት ላልተወሰነ ጊዜ እዚያው ተጣበቀው ቀሩ። በመጨረሻ ግን «እኔ እንደሆነ በምንም መንገድ ከአንቺ አልለይም። ያፈቀደሽን ልትናገሪ ትችያለሽ። እኔ ግን ከአንቺ ተለይቼ አልኖርም። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ሂድልኝ ብለሽ ብትጮሂ ዋጋ የለውም» አለ

ሎርድ ከርስተን።

ጳያን ቃል አልተነፈሰችም። እንዳቀረቀረች ስትቀር ፈትን ተ
አድርጎ አያት። ከዚያም ደጋግሞ ሳማት፣ እርስዋም እርሱን ከመሳቡ
ከመላስ አልቦዘነችም።

«በምን ምክንያት ከአንቺ እንድርቅ እንደ ፈለግሽ ገብቶኛል። የኢ
ሀብት በሁለታችን መካከል ላለውና ሊኖር ለሚችለው ግንኙነት እንቅፋት
የሚሆን መስሎሽ ነው፣ አይደል? ስሚ ፍቅሬ፣ ስለንቺ ሰል ያለኝን ሀብት
በሙሉ አባክኜ ራሴን ድሃ አደርጋለሁ። አንቺን ካገኘሁ እንኪን ደን
የፈለገውን ብሆን ደንታ አይኖረኝም» አያለ ስሜቱን ሲገልጽላት መለ
ሳትሰጥ ከብብቱ ሥር ተሸብራ እርሱን መማጠንዋ አልገባህ አለው።

የፈለጋትን ብትል ስውቤው እንደማይለቃት ሰለገለጸላት ከዚያ
ወዲያ ይቅርብን ብሎ መለፍለፉ ጥጋ እንደማይኖረውና ለምን ገባሁበት
ብሎ መጸጸት ደግሞ ጥቅም እንደማያስጥ ተገነዘበች። እውነትን በፍቅር
ላለመለወጥ ቆርጣ ነበር። ምንም ነገር ቢሆን ከሙሳኤዱ ፈተት አልለየ
የሚል እምነት ነበራት። ግን አልሆነም፣ ስሜትዋ ከዳት። ከተወሸቀችበት
ወጥታ ዓይን ዓይኑን ስታይ ለመለያየት ሁለቱም አለመቻላቸውን ከፈቱ
አነበበች። እንባዋ እንደ ጎርፍ ከጉንጮችዋ ላይ ፈሰሰ።

ከልብ የወደደ ሁልጊዜም እንደማለና እንደማረ የሚኖር መሆኑን
አልገባውም። እርሱ የመሰለው በሁለቱ መካከል ያለው የደረጃ ልዩነት
ስላነሳባት የራስዋ ሁኔታ እንዳስለቀሳት ነው። ይህም በበለጠ እንዲወድዳት
ገፋፋው። ፊትዋን ደጋግሞ ሳመው፣ ሳሰውም ለማለት ይቻላል።

«ሄለን» አለ፣ «በሕይወቴ ሙሉ እንደ ዛሬ ተደስቼ አላውቅም።
ታዲያ ደስታዬን በልትሶ ባትለውጪብኝ በይበልጥ ደስ ይለኛል። ምን
ያስለቅስሻል? ተወት አድርጊው እንጂ!»

ጳያን ደስታውን በጎዘን ልትለውጥበት አልፈለገችም። የእርስዋም
ፍቅር ከእርሱ የበረታ ስለነበር ለፍቅርዋ ስትል ምንም ነገር ቢሆን መስዋእት
እንድታደርገው ስሚትዋ ገፋፋት። «እኔም ደስ ብሎኛል፣ ደስታዬ ከአንተ
ደስታ ያነሰ አይደለም» ስትል በጆሮው አንሾካሾከች።

«እንዲህ ከሆነስ የጋብቻችንን ቀን ባናዘገየው መልካም ነው። ከጣትሽ
ላይ ቀለበት ካላየሁ ኅሊናዬ ለመሆን ትፈልጋለች፣ በማለት ራሴን
ለማጽናናትና መንፈሴን ለማረጋጋት ያዳግተኛል። መቼ ነው ከጣትሽ ላይ
የጋብቻ ቀለበት የማጠልቀው የእኔ ፍቅር?»

«አሁን አትጠይቀኝ» ስትል መለሰችለት። «ነገሩን በማሙጣትና

t.me/OLDBOOKSPDF

በሚሥራድ ከበላሁት በኋላ መልሱን አሰጥሃለሁ። አሁን ግን ልነግርህ አላችልም» «የእኔ ጥቅር አንቺ ያልሽው ሁሉ ይስማማኛል» አላት።

የሉርድ ከርስተንና የዳያን ጨዋታ ደርቶ ላለ እመቤት ከራይተን ሁለቱ ከነበሩበት ክፍል ይገባሉ። ዘመዳቸው ዳያንን አትፎ ዳያን ደግሞ እንሶስላ መስላ ሲያዩ እጅግ ተገረሙ። ሉርድ ከርስተን ሁኔታውን ለማስረዳት ሊሞክር «ፊሊፕ ምንም ዓይነት ገለጻ አያስፈልገውም፣ ሁናቴው ራሱ ይመለከራል» አሉት።

«እንኳን ደስ አለህ አንደምትዪኝ አልጠራጠርም። በዓለም ላይ ያሉትን ሴቶች ሁሉ የምታስንት ሴት አገኘሁ» ሲል የደስታ ስሜቱን ያበስራል። እመቤት ከራይተን ዳያንን አትጥ በማድረግ ጉንጭዋን ላሙ።

«በዓለም ላይ ከሚገኙት ሴቶች መካከል ሰዘመድሽ የምትሆን ሚስት ምረጪ ብባል አንቺን እመርጥ ነበር» አሉ እመቤት ከራይተን ለዳያን የነበራቸውን አድናቆት በመግለጽ።

ሁለቱ ሴቶች ጨዋታ ሲጀምሩ ሉርድ ከርስተን ጥሎአቸው ወጣ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ዳያን ብቻዋን ወደ መንገዝ ወረደች። ወደዚያ የሄደችው የደረሰባትን ለማሰላሰል ነበር። የአለፈው ታሪክዋን ስታስታውስ ዘገነናት። የሆነው ይሁን እንጂ እውነቱን ማውጣት አንደሷባት አመነች። እውነት ተደብቶ እንደማይቀር ታውታለች። ምንም እንኳን ባትደስትበትም የቡሩኖ ሊቨርን ሚስት ናት። ይህን ሰው ያገባችው በተክሊልና በታላት የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ስለነበር ጋብቻው ሕጋዊ ነው። የተፈጸመው ጋብቻ ሕጋዊ በመሆኑም ከሁለቱ አንደኛቸው ካልሞቱ በስተቀር ጋብቻው አይፈርስም። የመንዙን ወራጅ ውሃ እየተመለከተች እውነታው ያ እንደሆነ በግልጽ ታያት። ሆኖም «ጋብቻ ማለት ምንድ ነው?» ስትል ራስዋን ጠየቀች።

«ጋብቻ የነፍሶች መጣመር ነው። ተመሳሳይና ተስማሚ የሆኑ ነፍሶች ከተጣመሩ ፍቅራቸው እየጸና ስለሚሄድ እስከ ዕለተ-ሞታቸው ምንም ነገር አይለያያቸውም። ግን ተስማሚ ያልሆኑ ነፍሶች ከተጣመሩና እርስ በእርስ ለመዋሐድ የማይችሉ ከሆኑ እውነተኛ ጋብቻ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ዳያንና ቡሩኖ በምንም መንገድ ስለማይመሳሰሉ ነፍሶቻቸው ተጣምረው አንድ አካል አይሆኑም» ስትል ራስዋን አጽናናች። እንዲያውም ከነአካቴው ሉርድ ከርስተን በብዙ ነገር ስለሚመስላት ነፍስዋ ከእርሱ ነፍስ ጋር በቀላሉ ሊጣመር ይችላል የሚል እምነት አደረባት።

ቡሩኖ መስጥን ቢሆንና ከርስተን ገበሬ ቢሆን ከማግባት ወደ ኋላ እንድማትል ገመተች። ሥልጣን፣ ሀብት፣ ወይም የተለየ ጥ

ትም አሳብዋን ሊለውጡ እንደማይችሉ ተገነዘበች። ግማሽ አካሉን የሚችለው ቡፋኖ ሳይሆን ፊሊፕ በመሆኑ የፊሊፕ እንጂ የዚኖ መሆን እንደሌለባት ደመደመች። ምንም እንኳን ነገሩ ከአሥራ ሁለት ቢመስልም አርስዋ ሰላመኔችበት በዚህ ዓይነት ራስዋን አጽናናች።

«በዓለም ላይ እንደ እኔ ለሰውቃይ የተፈጠረች ሴት የለችም፡ ፈጣሪ ከተለየ ይግሞ ስቃዩ ዘላለማዊ ይሆናል። መከራዩን አስመጪ የጌታ እንድኖር ሰው ሲጋብዘኝ ለምን አልተበለጡም! በምንም መንገድ ከጌታ ቤት እንደገና ስለማልመለስ ዳግም ዓይኑን አላይም። ይገባት እንኳን አላነጋገረውም። ቱና ብዩ እንኳን አልመለከተውም። በሆነ ይህን በማድረጌ ጎሊናዩ ሰላም ይነሳኝ ይሆን? አያለች ዳያን ከረረች ተሟገተች። በሙግቱ የረታች ለመሰላት የወሰደችው እርምጃ ከሌላ መስሉ አልታያትም። ሆኖም ሙሉ ለሙሉ ትክክለኛ እርምጃ አለመሆኑን በመገንዘብዋ በመጠኑም ቢሆን የጎሊና መቀላ ነበረባት።

አንዱን ጥሎ ከሌላው ጋር መኖብለል በደል እንደሆነ ታውቃለች የወሰደችው እርምጃ ስሕተት ነው ወይስ ትክክል ከሚል ፈተና ጋር ስለወደቀች እንደ ልማድዋ የምትይዘውን በማጣት እንደ ውሃ ላይ አረፋ ከመዋዠቅ አልፋ ዋለለች። ነገር ግን እውነት እውነት ነው እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም። ለመሆኑ ከእንደዚህ ያለ ፈተና ውስጥ የወደቀች ተመላላይ ሴት በዓለም ላይ ትኖር ይሆን?

«እርግጠኛ ነኝ፡ የጎሊና ጸጸት አይኖርብኝም» አለች ዳያን ሰራሰየ «እንደ ሌሎች ሴቶች ደልቶኝ የምኖር ሴት አይደለሁም። የወደድኩትን ሰው ባገባ፡ ልጂ ባይሞት፡ ሌላው ተርቶ ደስ የሚያሰኝ የተሰፋ ሙላንሞይል ባለው ላይ በደል አልፈጽምም ነበር» በማለት መፍትሔውን የምትዘረጋው ይመስል እጆችዋን ዘርግታ «ፊሊፕን ባገባም የጎሊና መቀላ ሰለሚያድብኝ ተደስቼ አልኖርም ይሆናል፡ ይህን አውቀዋለሁ። ሆኖም ከፊሊፕ ለመለየት ደግሞ አልችልም» ስትል ደመደመች።

የምሠራው ሥራ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? በማውጣትና በማውረድ የተሠቃየችውን ያህል ማንም ሰው እንደዚያ ታማሉና ተሰቃይቶ አያውቅም። ከእንደዚያ ያለ አስጨናቂ ፈተና ውስጥ የገባ ሰው ሊኖር አይችል ይሆናል። ለነገሩማ ይህን ለመወሰን የሚያስችል በቂ ትምህርት አልነበራትም። ምክርና ድጋፍ በምትፈልግበት ጊዜ ከእናትዋ ምክር እንዳትጠይቅ እናት የላትም። ባጭሩ ዳያን ፈተናውን የምትቋቋምበት ትምህርት ወይም ምክር የሚሰጣት ሰው አልነበራትም። ስለዚህ ተጀምሮ እስኪጨረስ የሚበጃትን የምትመስነው ብቻዋን ሲሆን

ሁሉም፤ ዳኞም ራስጥ ነበረች።

ዳያን ከመንዙ ዳር ቁማ ከጎሊናዋ ጋር ስትሟገት ልጃገረዶች የአበባ ጉንጉን ከመንዙ ላይ በመጣል ሠጠንቆላቸው ታጠላት። በጋንጅስ ወንዝ አካባቢ የሚኖሩ ልጃገረዶችን አስበች። ልጃገረዶቹ ስለፍትረኛቸው ለመወሰን ሲፈልጉ የአበባ ጉንጉን ከመንዝ ውሃ ውስጥ ይጥላሉ።

«እኔም እንደነርሱ አደርጋለሁ፤ ከጎሊናዬ ጋር መሟገቱ ሰለቸኝ። ከእንግዲህ ወዲያ አድለ ያመጣልኝን አቀበላለሁ» አለች እርሰ በራስጥ ስትጋገር። በአካባቢው ከነበሩ ዛፎች አበቦችን ቀጠፈች። ከቀጠፈቻቸው አበባዎች ጀልባ-መሳይ ነገር ሠርታ ከመንዙ ውሃ ላይ ለቀቀችው።

«የእኔ አድል በዚሁ ይጠናል» አለች። «አሁን በማየው ትርኢት የወደፊት አድሉን አመራለሁ። በጀልባ መልክ ሠርቼ የለቀቅኩት አበባ ሳይፈርስ ለዓይን እስኪሰወር ድረስ ከሄደ ሳላወላውል ሎርድ ከርስቱን የሰጠኝን ደስታ አቀበላለሁ። ስለዚህ የፊልፕ ባለቤት እሆናለሁ ማለት ነው። ግን ማሰበል መጥቶ ወይም የሠራሁት ጀልባ ከድንጋይና ከግንድ ጋር ተጋጭቶ አበባው ከፈረሰ ወይም መንሳፈፍ ተስኖት ከሰጠመ ፊሊፕን አላገባውም።

'አበቦች ሂዱ፣ የወደፊት አድሌን ወስኑ' በማለት የሠራችውን ጀልባ ከወንዙ ውሃ ላይ ለቀቀችው። ጀልባውን ከመስደድዋ በፊት አገላብጣ ሳመችው። ጀልባው ተንሳፍፎ ሲሄድ ዳያን ከዳር ቁሞ ብላ ጠበቀችው። እንግዳ የሆነ ትርኢት ነበር።

ጊዜው ለዓይን ያዝ ወደ ማድረጉ ነበር። ወራጁ ውሃ የተንጠለጠሉ ቅርንጫፎችን አልፎ አልፎ እየነካ ያጫውታቸዋል። ከተረተሩ አካባቢ የነበሩ አበቦች ጥሩ መዓዛ ያለው ሽታ ስላመጡ የነበረው አየር እንደ መልካም ሽቶ ይጣፍጣል። ዳያን አቆልቁላ ወራጁን ውሃ ተመለከተችው። ድንገት ኃይለኛ ነፋስ ከወደ ሰሜን አቅጣጫ ስለመጣ ልብዋ ከሁለት ተሰነጠቀ። ከአበባ ጉንጉን የተሠራው ጀልባ ከዓይንዋ የተሰወረ መሰላት፣ ግን ጀልባው ቀጥ ብሎ ሳይፈርስ ሄዶ ሄዶ በጣም ስለራቀ ከዓይንዋ ተሰወረ።

«ይህን ሰው ማግባት አለብኝ» አለች ዳያን። «ይህን ጋብቻም የምፈጽመው በፍቅር ታውሬ ስለሆነ የማደርገውን አለማወቄን አውቃለሁ» አለች። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ይህን ሰው ላግባው፣ አላግባው የሚል ጥርጣሬ ከጎሊናዋ ውስጥ አልተመላለሰም።

ምዕራፍ ሃያ አንድ

ከእርሱ ወዲያ ሕይወት

«ሙሉ በሙሉ እንኳን አልረካሁም ሂለን» አሰ ሎርድ ከርስተን ከተጫጨችና ጥቂት ቀናት አብረው ካሳለፉ በኋላ። «ፊትሽ ወግ ግሉ እንዳይ አፈልጋለሁ። የእኔ ሕይወት፣ ዓይኖችሽ ውስጥ አሁንም ሚንቶት ይታያል» ብሎ ሲነግራት «ሚንቀት አልክ ፈሊፕ!» አለች ሬጋ ብላ።

«አምን ሚንቀት፣ የሕመም ይሁን የጸጸት ወይም የወደፊት ኑሮ ጥራቻ ለመለየት ያዳግተኛል። ምንድነው ነገሩ ሂለን?» አሰቲ ልለምንሽና እውነቱን ንገሪኝ።»

ቀና ብላ እያየችው «አሁንም አለ?» ስትል እየሳቀች ጠየቀችው።

«የለም፣ አባርረሽዋል። ግን ምንድነው የሚያስፈራሽ ሂለን?» ሲለ ድምፁን ዝቅ አድርጎ በተረጋጋ መንፈስ በድጋሚ ሲጠይቃት «ብዙ ነገሮች አሉ ፌሊፕ። ወደ አክስዴል ከወሰድከኝ በኋላ ጥሩ የቤት አመቤት ሆኜ ባታገኝኝ ምን ታደርገኛለህ? አንተ እኮ የምታገባው ከአንተ እጅግ በጣም ዝቅ ያለችዋን ሴት ነው።»

«ነው እንዴ?» ሲል ሎርድ ከርስተን በቀልድ መልክ ከጠየቀ በኋላ «ይገርምሻል፣ ታዲያ እኔ እኮ ምንም ቅር አላለኝም። በእኔ እምነት ደግሞ እንግሊዝ አገር ከሚገኙት ሴቶች ሁሉ የበላይ የሆነችዋን ሴት ነው የማገባው። ማንኛውም እኔ ነኝ ባይ ዘበናይ እንዲያገባሽ ቢጠይቅሽና እንቺም እሺ ብትዪው ክብር እንደሚሰማው አትጠራጠሪ። እና የዚህ የበታችነት ስሜት አያስጨንቅሽ» በማለት ሲመክራት «በቂ ምክንያት ነው» ስትል መለሰችለት።

ከዚያ በኋላ ከጎሲናዋ ጋር መሟገቱን ተወችው። የጥቅሩ ጽናት፣ የአነጋገሩ ስልት፣ የማባበልና ሰው የማቅረብ ችሎታው አንጀትዋን በላው። ያሰፈው ጋብቻዋ ትዝታ አልረሳም ቢሳት እርስዋ ተወችው።

ስለአዲሱ ጋብቻ በየጋዜጣው የሚወጡ ጽሑፎችን አነበበች። ሎርድ ከርስተን ቁንጅዋ ወይዘሪት ቱርፒን ለማግባት በዝግጅት ላይ ስለመሆኑ ብዙ ተጻፈ። ቢሆንም ጋዜጠኞን ስታነብ ዳያን ሳት ትበል እንጂ ፈገግታዋ ከአንገት በላይ ነበር። ከነዚያ ከተዋበ ከንፈሮችዋና ገጽታ የሚመር ፈገግታ ማየቱ የሚያሰቃይ ነበር። ደግነቱ ጋዜጠኞ ያወጥዋቸው ፎቶዎች የተደበቀ ሚንቀት እንዳለው ማንም አልጠረጠረም።

ሁሉንና ሄስተርም በጋዜጣ የወጣትን ጽሑርት በደንብ ባጋጣሚ ሰናን ርቆ አላዩም፤ ልብ ብለው ያላዩትም በማም ስለተለመጥም ደን ይችላል። ይግኑ፡ ጋዜጠኞን የገዙት ሌላ ነገር ለማንበብና አውቀት ሥጣት እንጂ ስለሌርድ ከርስተን ጋብጅ ለማጠት ነበተው ስላልነበረ ሰውን የሚያመሳውን ጽሑፍ ያልፉታል። ጋላቱ ሰው ማንን እንደሚያገ አሙቱም።

ዳያን ያልተንዘዘ ሠርግ ነበር የፈለግችው። ግን ማን ቢሰማ! ሌርድ ከልክንና አመቢት ክራያተን በአሳብዋ አልተስማሙም። «ሠርጋችን እንጂ በምትዪው ሳያኑት ቢሆን» አለ ሌርድ ከርስተን፡ «ሰምች በሚሰቱ አኖር ነው ያለቸው። እንዲህማ ሆኖ ግን በሚስቱ የምኩራራ እንጂ የማር አያደለሁም።»

«ለምን የደከመ ሠርግ እንዲሆን ፈለግሽ ሄለን?» ሲሉ አመቢት ከራያተን ከጠየቱ በኋላ «ፊሊፕ እንደሆነ በዚህ ፈጠርሰ አደስማግም» አለቸት። ነገር ግን የዳያንን ምኞት ሰመጠበቅ ሲባል ሠርጉ እጅግም ያልተንዘና የሌርድ ከርስተም ... ደረጃ እጅግ ዝቅ በማያደርግ መልኩ እንዲዘጋጅ ተመሰነ።

«እሾሽ ሄለን» አሉ አመቢት ክራያተን፡ «ሠርጋችሁ ከማንቸውም ተራ ሠርግ መለየት አለበት። ቅልትና ... ዘበረ ሰው ልታገቢ ስለሆነ የዚህ ሰው ሠርግ ደግሞ ከስሮ ጋር ...ሚሄድ መሆን ስለሚኖርበት ይህን መተበል አለብሽ።»

አመቢት ክራያተን በዝግጅቱ ለመሳተፍ ቅልቅ ጉጉት አደረባቸው። ዳያን ከመቼውም ይበልጥ አምራና ደምቃ እንድትታይም ፈለጉ። አቅምች በየዓይነቱ ተግዝተውና ከሻንጣ ውስዋ ከተከተቱ በኋላ ከአንድ ክፍል ውስዋ ተደረደሩ። ዳያንም ተጠርታ እንድታያቸው ተደረገ።

ያንን ሁሉ ያማሩና የተከበሩ ነገሮች ስታይ ዳያን መናገር አቅቱአት እናሞን ያዘች። ከዚያም አመቢት ክራያተንን እየተመለከተች «እውነትም ይህ ሁሉ ለእኔ ነው?» ስትል ጠየቀቻቸው።

«ይመስለሻል» ነበር መልሱ። «ከአንቺም ወዲያ ለዚህ ነበር የሚበቃ የለም ሄለን» በማለት ቢገልጹላት ዳያን ወደ አመቢተቱ ጠጋ አለች። ስትፈራ ስትቸር ቱና ብላ ተመለከተቻቸው። እጅችሞን ከትከሻቸው ላይ አሳረፈች። እንደገና ቱና ብላ ተመለከተቻቸው።

«ፍርሃት፡ ፍርሃት አለኝ፤ እንዲህ ያለውን ቅምጥል የምለምድ አይመስለኝም። ይህ ሁሉ ሀብትና ነብር ለእኔ የሚገባ አይደለም። እኔ

እንደሆንክ የአንድ ድሃ ሠካሲ ልጅ ነኝ።»

ትሕትናዋ የእመቤት ከራይተንን ሰሚት ከፋኝ ነገ... አግላብጠው ሳምዋት። «አውቃለሁ የእኔ ልጅ» አሉ፣ ...ን ... ቆንጆ ከዘረዳ ነሽ። ደግሞም እንግሊዝ አገር ውስጥ እሱ ከሚባ... ሰዎች መካከል የአንደኛው ሰው ሚስት ለትሆኚ ነው።»

«ይሀን እኔም አውቃለሁ» አለች ዳያን ሬጋ ብላ። «ግን እኔ ላለች ምስኪን እጅግ የበዛ ነው የመሰለኝ» ስትል እመቤት ... ነት ብለው ሳቁ። «ሂለን፣ በራስሽና በተሰጠሽ ከብር አለመ... ትህትናሽን ነው የሚያሳየው። አንቺም ብትሆኚ እኮ ለመቤ... የለውም፣ ይሀን አንቺም አትከሺም።»

«ይሀን ለመካድ አልፈትድም» አለች ዳያን። «ሆኖም ነ... ከብዶኛል» ስትሳቅ «ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው» አሉ እመቤ... ሂለን፣ ወደ ሦስት ጉልቻ ማምራትሽ ስለሆነ ይሀን ያክል ልለገስሽ ... ጊዜ ቢሆን ራስሽን ዝት አድርገሽ አትገምቺ። ይህች ዓለም እንደሆነ ... ራሳቸውን እንደ ግመቱት አድርጎ እንደምትተባቸው አስታውሺ...

ዳያን ላታስበው በርከት ላሉ የነበሩ አታውንትና ልብሶች ... ሆነች። ለሎርድ ከርስተን አልበታ ብሎት አሁንም በወርትና በ... እንድታጊጥ በመፈለጉ ጉትጉው፣ ሐብሉ፣ አምባሩ፣ ምኑ ቅጡ አ... ጊጥ ሳይተር ከገበያ እየወጣ ገዛ። ዳያን ለሁለተኛ ጊዜ ስለሙሽራ ... የምታስላስልበት ጊዜ ደረሰ። የሙሽራው ልብስ ግዙፍነት አስፈራት ... ለመጀመሪያ ሠርግዋ የተረበሳትን የሙሽራ ልብስ እንዴት እንዳደነ... ትዝ ሲሳት አንቀጠቀጣት። ያሁኑ ግን ከመጀመሪያው ፈጽሶ የተ... እጅግ የሳቱ ነበር። ተራ የሙሽራ ልብስ አልነበራም።

የሠርግዋ ቀን ዋዜማም እንዲሁ ደረሰ። ሁሉም ነገር እርስዋ እ... ፈቀደችው ተዘጋጀ። ሥነ ሥርዓቱ እጅግም እንዳይንዛዛ ሆኖ ነበር የ... ደው። ከዚያ የነበሩ የአገሩ ታላላት ሰዎችና መሳፍንት ተጠሩ። ሎር... ፒተርስ የሎርድ ከርስተን አንደኛ ሚዜ እንዲሆኑ ተመረጡ። የጣይ... አልጋ መራሽ የነበር እንግዳ ሆነው ተጋበዙ። የኮሞዶል እሙት ቤተ... የሙሽራይቱ ሚዜዎች ሆኑ። የተጠሩ እንግዶች ሁሉ በጥንቃቄ የተ... ረጡ ሲሆኑ ለዳያን ይህ ሁሉ ሕላም እንኚ እውን አልነበራም። በሚ... ለው ቀን ዳያን ባል ስለምታገባ ስጠታው ጎረፈ። በእሉቱ መደር የለሰ ... ቱርስ ተዘጋጀ።

«በትሂድ ይሻላል» አስነሉት ድረስ ሎርድ ከርስተን ከሙሽራይቱ ቤት ነበር ያመሸው። የወደፊት ሚስቱን አልጠግብ አያለ እጅዋን ከመጨበጥና

ነገሮን ከመሳም ባለማቋረጡ ሰው ሁሉ ጉድ አለ።

«መለላዬ! ነገ ውድ ባለቤቴ ትሆኛለሽ» አለ በሹክሹክታ ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ። «እንዴት ነው የሚነጋልኝ?» ሲል ጠየቃት። ሆኖም ሳጠየቀው ቀሪ መልስ አልነበራትም።

«እመቤት ከራይተን ደጎና እደሪ ብለው ከዳያን ከፍል ወጡ። ዳያን ከዚያ ሁሉ ስጦታ፣ ከዚያ ሁሉ የከበረ እቃ፣ ከዚያ ሁሉ ልብስ ጋርና ከአላብ ሚንቀት፣ ከተስፋና ከደስታ እንዲሁም ብዙ ሴቶችን ካሳበደው ከፍትር ወላፈን ጋር ብቻዋን ቀረች።

ያን ለት ባየችው አስፈሪ ሕልም ከጥንት ገጠር ቤትዋ ተመልሳ ልጅዋ ለመሞት ከሚያጣጥርበት ክፍል በመግባት የበሩን ፊት ሚጋማ መስሉና ሃስተር የተንኮል ፈገግታ ስታሳያት ተመለከተች። ልጁ ተኝቶበት ከነበረበት አልጋ አጠገብ ቆመች። የሕይወትዋ ተስፋ የሞት ጥላ እንዳረፈበት ተገነዘበች። ከዚያም ለመሞት የተቃረበት የልጅዋ ዓይኖች ተገልጠው ፊትዋን አተኩረው ሲመለከቱ አየች። እነዚያን ትናንሽ እጆቹን ዘርግቶ «እማዬ ጥለሽኝ አትሂጂ» ሲላት ሰማች።

ሕልሙ አስደንጋጪት በመሆኑ ከእንቅልፍዋ ባነነች። ዓይኖችዋን ስትገልጥ እነዚያ የሚያምሩ ጊጣጊጦች፤ የሙሽራው ልብስና ሌሎችም ላይ በባለመስታወት መስኮት ዘልቆ የገባው የፀሐይ ብርሃን አርፎባ ችውና ከፊት ለፊት ተደርድረው ተመለከተች። ያ ሁሉ እቃና ሀብት በሚተጥ ለሙ ቀን ሉርድ ከርስተንን እንደምታግባ አስታወሰዋት።

አየሯሽች ከአልጋዋ ዘልላ ወረደች። ልጅዋ ከአንባትዋ ላይ ተጠምጥሞ ድምፁ ከጆሮዋ ውስጥ ሲፈስ በአሳብ ታየች። ልጁ ግን ሞቷል። ከብዙ ዓመታት በፊት በሞት ተለይቷታል። እርሱ ባይሞት ኖሮ ከዚያ ቤት አትሄድም ነበር።

«ወይ አድሌ! ልጄ ባይሞት እኮ እስከዚህ አላብድም ነበር» ስትል ተብረከረከች።

«እማዬ» ነበር ያለው የዚያ ሕፃን ድምፅ! «እማዬ»..... በእናትነትዋ ምን አደረገችለት? በሚተጥለው ዓለም ሲገናኙ ምን ይላታል? የሉርድ ከርስተን ባለቤት ሆና ሳለ «እማዬ» ብሎ ይጠራታል? ሚንቅላትዋ ውስጥ የሚመላለስ አሳብ ነበር። የምትይዘውንና የምትጨብጠውን በማጣት በኃይል እየተነፈሰች እንደገና ከትራሱ ላይ ተደፋች። እንቅልፍ አሸለባት። አዙንም በሕልምዋ ልጅዋ ለመሞት ሲያጣጥር እንደገና አየችው።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ሁለተኛ ጋብቻ

ከፍሎረንስ ከተማ ወጣ ብሎ የሚገኝ ውብ የሆነ ግንብ ቲዮን የቅዱስ አንጀሎ ቤተክርስቲያን ይባላል። የጸደን ሠርግ ሥርዓት የተፈጸመው ከዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው።

ከዚያ አስከፊ ሕልም በኋላ ነገሩ ከአዕምሮ ጀምሮ የከዘር ከርስቱን ተብሎ እስከ ተሰየመ ድረስ ሲሳ ረጅም ሕልም መሰ አልባሽ እርስዋን ለማስዋብ ሲቻኮሉ ተገረመች። ወደ ብላ ስታይ ሰገር ሰማዋና ለውበትዋ ወደር የሌላት ሴት ም ውስጥ በእድናቆት ተመለከተች። ሳትወድ በግድ ሰለመጀመሪያ ማዋ ቀን ማሰላሰል ጀመረች። አንዘያ ሁለት ደጋግ ሴቶች ሳይ ምንም እንኳን የዚያን ጊዜው የመሸራ ልብስ ከእሁኑ ጋር ሰ ዝቅተኛ ቢሆንም እንዴት አንዳንተችው ታወሳት።

ያሁኑ ደስታዋ አንዳያደፈርስ ከቀድሞ ሕመምዋና ጸጸት ጭ ላትጠጣ ይሆን? ያለፈውስ ስቅያዋ ላይረሳ ነው? ሆነም ቀሪ ደግት ቀን ግማሽ አካሉዋን የምታገኝበትና የመጨረሻው የደስ ስለሆነ እውነተኛ የሠርግዋ ቀን የመጀመሪያው ሳይሆን የእሁኑ ነው ደጋ ይቃሳል። ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ መሞሸርዋን ልቦናዋ ስለሚያውቅ የ ወሳሳ ከማለቅየት አልፎ አስተከዛት።

«ዳያን በሠርግዋ ቀን መተከዝዋ ለምን ይሆን?» በማለት ሉርድ ከር ተጨነቀ። ከቤተክርስቲያኑ ውስጥ ቁሰ ለሁለተኛ ጊዜ ሊያሸም ሲጠጉ ሰውነትዋ ሁሉ በፍርሃት ተንቀጠቀጠ። አሁንም ለሁለተኛ ጊ «ባሌን አፈቅራለሁ፡ አከብረዋለሁ፡ እታዘዘዋለሁ፡ እስከ አለተ-ሞቴ ከር አልለያም» እያለች የመሐላ ቃል ልትፈጽም መሆኑን አስበች። እነ ቃሳት አጅግ አስፈሪ ቢሆኑም ለሁለተኛ ጊዜ ትምላለች። መጀመ ቀድም ብላ ያፈረሰችው በመሆኑ ብዙ አሳስባት። ሉርድ ከርስተን ፍ እንደ ተከፋች በማየቱ ለማረሳሳት «ያእኔ ፍቅር! የእኔ አመቤት፡ እኛ የተመደድሽ ባለቤቱ!» እያለ አቆላመጣት።

አምን፡ ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ባለቤቱ ሆነች። ከቤተክርስቲያኑ ሲወጣ ሕዝቡ በሮዝብሬሳ፡ ሴቱ በአልልታ ተቀበላቸው። የሁሩን ቀለበት ባለሉተችበት ጣትዋ ሲሳ በአልማዝ ያጌጠ ቀለበት ገበች። ሉርድ ከርስቱን ቀለበትዋን እያየ እጅዋን እንደ ለመደው ሳመው።

ሥራ መሳለፊያችን ነው። የደስታ ስሜት ከፈትሽ ላይ ይፈንጥቅ
ፈርሳችን ቀን እኮ ነው። ምነው ፈትሽን ትሳጥረዋለሽ፣ አጠገብ
ለ ለመ ለራድ ከርስቱን ጠየቃት።

ደ ጊዜ ከልብዋ ውስጥ ያኑድ የነበረውን የጭንቀት ወላፈን ለማጥ
ረህ ሥና ለመታየት ታግለች። ሉርድ ከርስቱንን አያመሰግኑት
ንደረው ከጅሮ በማይደርስ ዝቅተኛ ድምፅ መልስ ሰጠችው። ምን
ሥር ግን አደታጠትም። በልብዋ ውስጥ ግን ጎንሲናዩ እንደማያጠቅሰኝ
ደኛ ነኝ አያለች አሰበች።

ሥሪቱ እንደ ተራጸመ ቂሱ ጠጋ ብለው «እንዳንቺ ያለች ውንጀ፣
ደንና ግርማ ሞገስ የተጎናጸፈች መሸራ አስክ ዛራ አይቼ አላውቅም»
ለት ለፍቅር ብዬ በደል ብፈጽምም ጎሊናዩ አያወቅብኝም» በማለት
ሠዘች። መሸሮቹ ከሠረገላቸው ውስጥ እንደ ገቡም በፈረንጅኛ ባህል
ሥመደ ነውና ሉርድ ከርስቱን የዳያንን እጅ አየደጋገመ ሳመው። ወደ
ን ነት እድርጎም ግንባርዋን ሲስም አርስዋ አምርራ አለተሰች።
ጅ ብዬ በደል ብፈጽምም ጎሊናዩ አይወቅብኝም በማለት አስሳሰለች።
ሰ በግልተስዋ ሉርድ ከርስቱን አልተገረመም፤ ሲያሩ ግልተስ ወግ
ና ስለዚህ ለጥቂት ጊዜ ታልቅስ በማለት ገም አላት። ከዚያም ብዙ
ነባትና በርጎራኔ ዓይን ካያት በኋላ ፈትዋን የሸፈነውን የመሸራ ለብስ
ዘር ትንሹችዋን ሲስም እንባዋ ፈጨው ፈጨው አለው።

ደእኔ ሄለን፣ ሙድ ባለቢቱ፣ ከልብ ትወጂኝ የለ?» አለ። «ለምን
ታለቅሺኛለሽ? ከአሁን ጀምሮ እኮ የግሉ ነሽ። እኔም የአንቺ ብቻ ነኝ።»

እውነትም የግሉ ናት? የቡሩኖ ኮስታራ ፈት ከፈትዋ ድቅን አለ።
ከርቲ ከርስቱን ላይ ጥምጥም አለች። ስሜትዋን ተመለከተ እንጂ
ጠነያቱን ለማወት ግን አልቻለም።

«ሄለን!» አለ ረጋ ብሎ። «አሁን እኮ የእኔ ብቻ ነሽ። ከአሁን ወዲያ
ስንኖርና በደስታ ከመኖር በስተቀር የሚይስጨንቅሽ ነገር የለም። በልትሰሽ
ከመልሽ እኔን ፈርታ ነው ብዬ አስባለሁ።»

ዳያን ፈትዋን እንደዚያ ከሚያምናትና ከሚተማመንባት ሰው ለብ
ድዝ ለመደበቅ ሞከረች። «ለእንድ ደቂቃ እንኳን ልረሳው ብችል»
እች ለራስዋ። ግን ለሰኮንድ እንኳን በሩሩን ለመርሳት አልቻለችም።

ነገር ግን ዳያን እዲሱ ባልዋን እንደዚያ ማስጨነትና ማሳዘን ተገቢ
እንዲደለን በማመንዋና ለፍቅሩ ስትልም ብዙ ተስታዮች። ለዚሁ ፍቅርም
ሲ ይበልጥ ስሜትዋን በማመቅና በመቆጣጠር ራስዋን መሥዋእት

ማድረግ አንጸለባት ተግነዘበች። ስለዚህ ራስዋንና ሰሚትን ነጻ
የተቻላትን ሁሉ አደረገች። የሚያሳድጓትን አሳብሞ ለማመስገ

ቀና ብላ አዲሱ ባልዋን በመደገግም ሳመችው። በዚህ ጊ
ይሉኝታ ያሳት ሴት መሆንዋ ተረጋገጠ። ቀርስ ከተዘጋጀላ
ስለደረሰ የምግቡና የመጠጡ ዓይነት፣ የሳራራሬው ብዛት፣ የ
ድምቀትና ውበት፣ የተደረገው ንግግር፣ የምሥራቹ ጋጋታና ሌላ
ሁሉ ነገሩ ከለፊ በኋላ ጸያን እንደ ሕልም አየችው። ከዚያ ሥራ
ሰዓት ስለደረሰ እመቤት ከራይተን በአንባ፣ ሌሎች በሩጫትና በጭ
ሸኙዋቸው።

«አብረን በቆየንበት ጊዜ እውነተኛ ወዳጅና ረዳት ሁነ
የጥርሽው» አልዋት እመት ከራይተን። «አንቺን በማግኔ ለራሴ
ያዘንኩት። ስለአንቺ ኑር ግን ብዙም አልፈጁንትም። የሱርድ ከር
ሚስት እስከሆንሽ ድረስ ተደስተሽ አንደምትኖሪ አልጠራጠርም።

ባልና ሚስት የጓጉላ ጊዜአቸውን በደስታ ለማሳለፍ ብቻቸ
ከመሄዳቸው በፊት ሰምች ጸያንን ከበቡ። ሰሚትን የሚነካና መነ
የሚያድስ ታላ ተናግሩ፣ የምሥራቹም ተሰጠ። ከዚያም ከፈታቸው አ
ቸው የተዘረጋውን አዲስ የደስታ ሕይወት ለመቅመስ ባልና ሚስት ከ
የሩቁን አሻግረው ለማየት ሞከሩ። ሆኖም በደስታና በፍትር ተሸንመ
መደፊት ሊሆን የሚችለውን በግልጽ ሳያዩ ሄዱ፣ ተራመዱ፣ ነዚ
ጉዞአቸውን ተጠሉ።

በእለቱ በተጥታ ወደ ሱርድ ከርስተን ቤት አልሄዱም። እዚያ
ጣልያን አገር ውስጥ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ተደናቂ የሆኑ ሥፍራዎች
እየጎበኙ ጥቂት ጊዜ አሳለፉ። ጸያን ያለፈው ኑሮዋን ትዝታ ሙሉ በሙ
ከዛንትሳትዋ ነቅላ ለማስወጣት አለመቻልዋ ነው እንጂ ደስታዋ የእና
እጥፍ ነበር።

በኑሮዋ ይህን አገኛለሁ ብላ ባሳለመችበት ጊዜ የገጠማት እደ
በየደቂቃው ደስታን በገፍ የሚያስታቅፍ ሲሆን ዓለምን ከጫማዋ ሥ
ያደረገች ቆንጆ፣ ወጣትና ሀብታም በመሆንዋ ከዚህ መዲያ የሚያስቀ
ምን ነገር አለ?

ጸያን ሙግሳ አክብሮትና አድናቆት በየሄደችበት ተከተሳት። ስለዚ
ያ ያሳድጓትና ያስጨንቃት የነበረው የጓሊና ጭንቀት ቀስ በቀስ ቢለታ
የሚገርም አይሆንም።

ያ ለመርሳት የምትታገለው የጨለማ ዘመን ኑሮዋ ባይኖር አዲ

ምዕራፍ ሃያ ሦስት

እንግዳ የሆነ ማስታወቂያ

ጸያን ከዚያ ከታላቅ ሰው ቤት ስትገባ የሚለበትባትን ቀሚ ጸር ተሰናዳት ግሪ የሚገባት መሰላት ግን ከገዘዜ በኋላ ሁሉንም ነ ለመደችው ባልዋ እርስዋን ለማስደሰት ብሎ ሰጣዉነት ስታየው እረፍት በበኩልዋ እርሱን ለማስደሰት ጣረች እመቤት ከርስቱን ቤ ብዙ ሳያሠን በሚያዩት በማንኛውም ሰው ፊት ሁሉ መወደዱን አየ ሴቶች አደነቅዋት፣ ወንዶች ለሚስቱ ባይሆ ለመዲስት ተመኙ ባልና ሚስት ስማኙ ግንኙ በየከተሩ ግብዣ ተጠሩ በዚህ ቤት በእንግዳ ተሞላ የእንግዳ መብዛት ሱሪያ ከርስቱንን አሰደሰተዉ ጸያን ደግሞ በግብዣው ብቻ ሳያሠን በዚያ አካባቢ ባለው ነገ ተደሰተች የቤቱ ማማር፣ የግቢው ስፋትና ንጽሬና የአበቦች ያማሩት በጠቅላላው ከዚያ ሥፍራ የሚታየው የተፈጥሮ ዉበት የአስፈሠን አሳሳ ኑሮዋን ጨርሶ አስረሳት

አንድ ቀን «እንደ አክስዬል ያሉ የተዋጣ ሥፍራ ሠላስ ሳያ ያሉ አይመስለኝም ነበር» አለችው ባልና «የመኖሪያው አጠ ነተ በመሠኑ በጣም ደስ አለኝ

«ከአላት ጋር ከእንድ ሥፍራ ብር በመኖር ቤት ንብረት አላረ ሪችሁም?» ብሎ ሱርድ ከርስቱን ሰጠይቅት አሳፈራንም ስት መለሰችለት «ከሠታ በታ ስንከራተት ኑር ናረንም ያማራና ለሥስ ሥራ አመቺ የሆነ ሥፍራ ባገኝን ቁጥር ዉ ገን ሆኖ ለዋሪት ንር እንቆይና ከዚያም ወደ ሌላ ሥፍራ እንሂድ ነበ

«እንግዲህማ ኑሮአችሁ ዘወትር የእንግዳ ሳይሆን አልቀረም ይህ ከሆነ ደግሞ የለመዱትና ብዙ የናፍቀት ቤት ትርጉም ምን እንደሆን አታውቂም ማለት ነው» ብሎ ከተናገረ በኋላ እንደ ልማዱ ሳማት

ከመሳሳም መልስ «በፍጹም» ስትል መለሰችለት ርቃ ገርመው ግን ዘድንጉት የቡና ሲበርንን ቤትና ላርችዴልን አስተ ያም በሆን ቤትዋ ነበርና ችዝ ሲላት ፈትዋ ተለዋወጠ ባልዋ ሊናገረዉ አፉዋው አታውት «ምነው ጸያን ፈትሽ ተለዋወጠሳ?» ሲለ ፈራ

«እኔ እንጃ ብላ እንደ መጣላት ብትመልስም ቃሷ «ልንገረህ አልችልም አለችው ሆኖም እራሷን ላለማስከፋት ፈር ላይወጡት

ፈተው ይለምጠዋል ::» አሳት የመገረም ምልክት አሳየባት። «ወሰላዪ ንጉሥ ስእኔና ለዜቱ ያለሽ ፍትር ጽናት ይሆን እንዲህ የሚያደርግሽ? ለሷ ሲጠይቅ... ከእንቱና ከሄረቱ ሳይ ተጠምጥማ ፈትሞን በሄረቱ ሠሸለን «ከል» እንደምወድህ ታውቃ የለ ፈሊጥ እንዳንድ ጊዜ ብቻዬን ቅጥ ብዬ እንኒ ሳስብበ ፈቱ ይለየወጣል። ምንም ለማድረግ አልችልም። በግለት ለታሰረዩው ሞከረች።

ከረምቱ እንደ ምንም አለፈ። ጸደይ ሲመጣ አዘዘዬል በጣም ደስ እንደሚል አሰበች። እውነትም ወራቱ እንደ ገፀ ተፈጥሮ ውብትዋን አብራ ይዛ ገባች። የአበባው፣ የወርቁ ዝማሬ፣ የልምላሜው፣ የአየሩ መንዝ፣ ምኑ ቅው ሁሉም ነገር ልብን የሚመሰጥ ሆነ።

«እሁን ከረምቱ ስላለፈ ወደ ለንደን ሄደን ከንግሥት ፈት በመቅረብ እጅ እንነሳለን» ሲሳት ጸደን አንደ ልማድዋ ደነገጠች።

«ወይ ፈሊጥ! ትተልዳለህ መስለኝ፣ ወደሰ ከልብህ ነው?» ብላ ሰትጠ ይቀው ባልዋ ከት ብለ ሳቀባት።

«በእንቲ ደረጃ ያለች ሴት ከዜቱ መንግሥት ሂዳ እጅ መንሳትዋ እንግዳ ነገር አያደለም። ንግሥትን መግናት ደግሞ የሚያስደስት አንጂ የሚያስደንግጥ አይመስለኝም።»

ብዙም ሳይቆዩ ጸደንና ባልዋ ወደ ለንደን ሄዱ። አዚያም ጸደን ከብዙ ታላላት ሰዎች ጋር ተዋወቀች። ለንደን በቆየችበት ጊዜም «እንግሊዝ አገር ከሚገኙት ቆንጆጅት ሁሉ ጸደን ትበልጣለች» የሚል ወሬ በከተማው ውስዋ ነፈስ። ባልና ሚስቱን የተዋወቁ ሁሉ መልስ ስለሚጠራችው በየቦኑ የሚሳርፈው የግብዣ ጥሪ ወረቀት ከጸደን ጠረጴዛ ላይ ተቆለለ። በዚህም የትሯውን ጥሪ ትቦን ወዲትሯው እንሂድ የሚል ጥያቱ አስጨነቃቸው። በአንድ ቀን ከመጠት፣ ብዛት ካሳችው የጥሪ ወረቀቶች መካከል፣ የሱሪድ ከርስቦን የመንፈስ ወዳጅ ከሆነችው ከእመቤት ሊልያን ሄይ ለመጣው ጥሪ ቅድሚያ በመስጠት ወደዚያ እንዲሂዱ ሱሪድ ከርስቦን አሳብ አቀረበ።

«ስለእመቤት ሊልያን ሳወራ የሰማሽ ይመስለኛል» ሲሳት «አዎን» አለች ጸደን። «እኔ ሁልጊዜም እንደ ዘመዴ ነው የማያት» አለ ሱሪድ ከርስቦን። «የምትወደድ ንጹሕ ሴት ናት። በደምብ እንድታውቂያትና እንድትቀራረቡ አፈልጋለሁ።»

«ሴትዮዋ የምታቀርበኝ ይመስልሃል?» ስትል ጠየቀችው የመጠራጠር ስሜት አየታየባት።

«ግንም ስው ቢሆን ካላቀረብሽው በትክክል ሊያውትሽ የሚችል

ፈታቸው ይለዋወጣል?» አሳት የመገረም ምልክት አየታየበት። «መሰላዪ ምናልባት ለእኔና ለቤቱ ያለሽ ፍቅር ጽናት ይሆን እንዲህ የሚያደርግሽ?» ብሎ ሲጠይቃትም ከእንቅፋትና ከሂሩቱ ላይ ተጠምጥማ ፈትዋን በሂሩቱ በመሸፈን «ከልብ እንደምወድህ ታውቃ የሰ ፈሊጥ! አንዳንድ ጊዜ ብዙን ቁም ብዬ እንኪን ባስብህ ፈቱ ይለዋወጣል። ምንም ለማድረግ አልችልም። በማለት ልታስረዳው ሞከረች።

ከረምቱ እንደ ምንም አለፈ። ጸደይ ሲመጣ እዝዘይል በማም ደስ እንደሚል አስዘች። እውነትም ወራቱ እንደ ገዘ ተፈጥሮ ውብትዋን አብራ ይዛ ገባች። የአበባው፣ የወርቅ ዝግሬ፣ የልምላሜው፣ የአየሩ መኳኳ ምኑ ቅጡ ሁሉም ነገር ልብን የሚመስጥ ሆነ።

«አሁን ከረምቱ ስላለፈ ወደ ለንደን ሄደን ከንግሥት ፈት በመቅረብ እጅ እንነሳለን» ሲላት ጸደን እንደ ልማድዋ ደነገጠች።

«ወይ ፈሊጥ! ተተልዝለህ መስለኝ፣ ወይስ ከልብህ ነው?» ብላ ስትጠ ይቀው ባልዋ ከት ብሎ ሳቀባት።

«በእንቺ ደረጃ ያለች ሴት ከዚቱ መንግሥት ሂዳ እጅ መንሳትዋ እንግዳ ነገር አይደለም። ንግሥትን መግናት ደግሞ የሚያስደስት እንጂ የሚያስደንግጥ አይመስለኝም።»

ብዙም ሳይቆዩ ጸደንና ባልዋ ወደ ለንደን ሄዱ። እዚያም ጸደን ከብዙ ታላላት ሰዎች ጋር ተዋወቀች። ለንደን በጽዮትበት ጊዜም «እንግሊዝ አገር ከሚገኙት ቆንጆዎች ሁሉ ጸደን ትበልጣለች» የሚል ወሬ በከተማው ውስጥ ነፈስ። ባልና ሚስቱን የተዋወቀ ሁሉ መልስ ሰለሚጠራቸው በየቀኑ የሚሳርፈው የግብዣ ጥሪ ወረቀት ከጸደን ጠረጴዛ ላይ ተቆለለ። በዚህም የቅኝውን ጥሪ ችሎን ወደጎኛው እንሂድ የሚል ጥያቄ አስጨንቅቸው። በአንድ ቀን ከመጠት፣ ብዛት ካሳችው የጥሪ ወረቀቶች መከከል፣ የሱርድ ከርስቱን የመንፈስ ወጻጅ ከሆነችው ከእመቤት ሲልያን ሂደ ለመጣው ጥሪ ቅድሚያ በመስጠት ወደዚያ እንዲሂዱ ሱርድ ከርስቱን አሳብ አቀረበ።

«ስለእመቤት ሲልያን ሳመራ የሰማሽ ይመስለኛል» ሲላት «አምን» አለች ጸደን። «እኔ ሁልጊዜም እንደ በመጂ ነው የማያት» አለ ሱርድ ከርስቱን። «የምትወጂድ ንጹሕ ሴት ናት። በደግነ እንድታመሂያት ና እንድትቀራረቡ አፈልጋለሁ።»

«ሲትዮዋ የምታቀርበኝ ይመስልሃል?» ስትል ጠየቀችው የመጠራጠር ስሜት እየታየባት።

«ማንም ሰው ቢሆን ካሳቀረብሽው በትክክል ሊያውትሽ የሚችል

አይመስለኝም» አለ ሎርድ ከርስተን እየሳቀ። «እኔና እመቤት ሲሉን ለረጅም ጊዜ ወዳጆች ሁነን ኖረናል። እና አሁን ሚስቱን እንድታገ ቅለኝ አፈልጋለሁ።»

ጸያን «ምን ማለቱ ነው?» ስትል ዓይን ዓይኑን አየችው። «ሊልያንስ እስከዚህ ቆንጆ ሴት ናት?» ብላ ስትጠይቀው አሁንም ሳቅ አለ።

«ከአንቺ በስተቀር ስለሴቶች ውበት ያስላስልኩበት ጊዜ ስለሌለ ልነግርሽ አልችልም። ብቻ ደግና ትመስለኛለች። አንቺን ግን አትስተካከልም። ጸጉርዋ እንጸንቺ ወርቃማ አይደለም፡ ዓይንዋም ጥቁር ነው።»

ጊዜው ገና ስለነበር እግረ-መንገዳቸውን ከእመቤት ዶርማን ዳገስ ቤት ጎራ አሉ። ከመውጣታቸው በፊት ጸያን ተሚስ ስታማርጥ ጥቂት ጊዜ ወሰደች። ነጭ ልብስ ከለበሰች በኋላ ባልዋ በስጦታ መልክ የሰጣትን የአልማዝ ጌጥ አደረገችበት። ከእመቤት ዶርማን ቤት ስትገባ ሰው እንደ ተለመደው ተግላምጠና አተኩሮ ተመለከታት።

«አዲስዋ ሙሽራ እመቤት ከርስተን፡ ቆንጆዋ እመቤት» ሲል ሰዉ እገረመረመ። እርስዋ ግን ስሜት አልሰጣትም። በየሄደችበት ቆንጆ መባሉን ለምጸዋለች። ያንን ያማረና የደመቀ ቤት በዓይንዋ ታኖኝው። ሊልያን ሄይ የተባለው ስም የተለየ ስሜት ስለሰጣት ያእመቤቲቱን ስም እየደጋገመች ጠራች። ለምን ስለዚያች ሴት እንደ ተጨነቀች ግን ሊገባት አልቻለም። ስሙ ራሱ ተጠንቀቂ በማለት ማስጠንቀቂያ የሚሰጣት መሰላት። ግን ለምን ይሆን የዚህ ዓይነት ስሜት ያደረባት?

ፈገግ ብላ ባልዋን ስታየው ከዓይኑ ውስጥ የደስታ ጭንጣቂ እየታየ ከፊትዋ ቆሞአል። እንዳጋጣሚ ሆኖ እመቤት ሊልያንም ከዚያው ስለነበረች «እመቤት ሊልያን ሄይም እዚሁ አለች» አላት። «ከአንቺ ጋር ለመተዋወቅ በመጓጓትዋ በጣም ደስ አለኝ። እንደ ዛሬ የተደሰትኩበት ቀን ቢቆጠር ጥቂት ነው። አንቺ ደግሞ እንደዚህ አምሮብሽ አያውቅም። 'እመቤት ሊልያን በቀላሉ የማይደሰት ፍጡር' እያለች ታሾፍብኝ ነበር። በዘንቡ እንዳልነበረ ዛሬ ትገነዘባለች።

ጸያን ነይ እስቲ ተከተዪኝ፤ ወደዚያ እንሂድ» ሲላት ብድግ ብላ ተከተለችው። የባልዋን እጅ ያዘች። ከዚያ የነበሩ ሰዎች ዓይን ተከተላቸው። «እርሱ ቆንጆ፣ እርሷም ቆንጆ! እንዴት ደስ ይላሉ» አልዋቸው። የደከማቸው ሰዎች ከሚያርፉበትና እጅ ለእጅ ተያይዘው ከሚጨፍሩበትና ዙር ካለ ሥፍራ ከሚገኝ ከፍል ደረሱ። ከፍሉን ከፍተው ሲገቡ ጸያን በእንዲት፤ ከቁመትዋ ዘለግ ባለች ግን እስከዚህም የምትደነቅ ቆንጆ ባትሆንም ደስ

የሚል መልክ ባሳች ሲት ትማረክለች። ከሲትዮዋ ፈት ሳይ በአንድ ጊዜ የደስታና የኀዘን ምልክት አየች። እመቤት ሊልያን ገና ወጣት በመሆንዋ ከሎርድ ከርስተን በእድሜ ታንሳለች። ከፈትዋ ሳይ የጭንቀት ስሜት በግለጽ ይታያል።

ብዙ ሰዎች እመቤት ሊልያንን ያፈቅራሉ። ጉርድርድ ብላ ደስ የምትል ሲት ናት። ደምግባትዋ የወንዶች ዓይን የሚከተለው ዓይነት ሲሆን ለሰው አዛኝ በመሆንዋ ሰው ሁሉ ያቀርባታል። ከተደሳችም ሆነ ከአዛኝ ጋር የመግባባት ኃይል አሳት። የተከፉ ሰዎች ስታይ እርስዋም የተከፉች ሳትሆን አትቀርም የሚል ስሜት ስለምታሳድር ሰዎች በቀላሉ ይቀርብዋታል። አለባበስዋ ዘመትር ያሸበረቀ ነው።

እመቤት ሊልያን በአለባበስዋ የተደነቀች ሲት ሰትሆን የልብስ ፋሽን ትጠብቃለች። ያን አለትም በአልማዝ አጊጣ በና ዓይነት ቀለም ያለው ቆንጆ ቀሚስ ነበር የለበሰች። ዳያን ቤቱን ሰትታኝ ከእመቤት ሊልያን ይበልጥ ማራኪና ደስ የምትል ሲት ከዚያ አለመኖርዋን ተገነዘበች። ሎርድ ከርስተን ወደ እመቤቲቱ መሰዳት። ያለወትርው ባልዋ በጣም መቅበጥበጥ ጡን ዳያን ታዘበች። ሁለቱን ሲቶች በማስተዋወት አጨባበጣቸው።

«እንደ ሁለት እንግዶች አላስተዋውቃችሁም። ሁለታችሁንም ማለቴ ውድ ባለቤቴ ሄለንና ጓደኛዬ ሊልያን ከዙሉም ይበልጥ እወድጻችኋለሁ። እመቤት ከርስተንና እመቤት ሄይ የእኔ መደሰት በማድ ስለሚያተራርባችሁ ጓደኞሞች እንድትሆኑ አልጠይቃችሁም።»

ከሊልያን ዓይን ውስጥ እንባ አቅርፎ እያለ የሚያማምሩ ከንፈሮችዋ ፈገግ ሲሉ ስሳየች ዳያን ትገረማለች። «እርግጠኛ ነኝ፣ ጥሩ ጓደኞሞች እንሆናለን» አለች እመቤት ሊልያን ሄይ። «በደምብ እስክንተዋወቅ ብቻ ችንን ልትተወን ትችላለህ?»

ሎርድ ከርስተን ከአጠገባቸው ዞር ሲል እመቤት ሊልያን የዳያንን እጅ ጨብጣ ይዛ መልክዋን አተኩራ አስተዋለች። «አንቺ ነሽ የጓደኛዬ የፊሊፕ ሚስት? በጣም ቆንጆ ስለሆንሽ ጓደኛዬ ከባድ ሎተሪ ነው የወጣለት። ይህ ዓይነት እድል እንደሚገጥመው አምን ነበር።

ሄለን ብዩ ልጥራሽ?» በማለት ስትጠይቃት «አምን» አለች ዳያን በመጠኑም ቢሆን ውስጥ ውስጡን በቅናት እየነደደች። ፍቅር ከለ ትናት በመጠኑም ቢሆን ውስጥ ውስጡን በቅናት እየነደደች። ፍቅር ከለ ትናት የግድ ነው። «በመጀመሪያ ስሜ ብትጠሪኝ በጣም ደስ ይለኛል።» ልስልስ ያለውና ዝግ ብሎ የሚወጣው የእመቤት ሊልያን ድምፅ ዳያንን ይማርክ ጀመር።

«እንግዲያውስ ሄለን» በማለት እመቤቲቱ ጨዋታውን ቀጠሉ። «መጀመሪ እንድትሆኚ ልጠይቅሽ። አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት ከአንቺ በላይ ሳይሆን እውነተኛና የልብ መጀመሪ እንድትሆኚ ነው የምፈልገው ግን ይህ ሊሆን የሚችለው አንቺም ያፈተርሽኝ እንደሆነ ብቻ ነው፤ ምን ትያለሽ?»

ፈገግ «በጣም ደስ ይለኛል» የሚል ነበር የዲያን መልስ። «ብዙ ሰዎችን አውቃለሁ፥ ጓደኛ ግን የለኝም። ባለቤቴ ስለሚወድሽ እኔም እንደ ሚፈትርሽ አርግጠኛ ነኝ።»

እመቤት ሊሊያን ሳቅ አሰች። «ፈሊፕ እንደሚወድደኝ እንዴት አወቅሽ?» ስትል በጠየቀቻት ጊዜ የእመቤቲቱ ፊት ሰምን በድንገት እንስሳ እንደ መሰለ ዲያንን ግራ አጋባት።

«እኔን በመውደዱ ደስ ይለኛል፥ አጠራጥሮኝም። ፈሊፕ እንደሆነ ሳይሞት ፈላ ዓይነት ሰው ባለመሆኑ ስሜቱ ዋጋ ያጎርጋል። ምንም እንኳን ትንሽ በስድሚ ቢበልጠኝም ለረጅም ጊዜ ጓደኞቹ ሁሉን ኖረናል። ልጅት ሆነን አፈር አብረን እየፈጨን፥ ከዚያም ነድግን በኋላ ጥሩ ዓይኖቹ ሁሉን እስከ ዛሬ ኑረናል። እንዲያውም ከዓይኑት አልፈን እንደ እጅና ወንድም ሆነናል።»

የቃልዋ አመራረድና አሰባበር ለስለስ ብሎ አድምጠኝ፣ አድምጠኝ የሚል ዓይነት ስለነበር ዲያን ሳይታወቃት ጉንጮዋን ሳመቻት። የትናት ስሜትም ከነሊናዋ ሙስጥ አየጠፋ ሄደ። ለ-ርድ ከርስተንን ማድነትዋ እንግዳ ነገር አልነበረም። ሁለቱ ሴቶች ብዙ ተጠያየቁ። ስለባልዋ የልጅነት ዘመን መስማቱ ዲያንን አስደሰታት።

«ባለቤቱ ከልጅነቱ ጀምሮ ነው መለስኝ ነበዝ የነበረው» አለች ዲያን።

«እምን በጣም ኩሩና ነበዝ ሰው ነው» አለች እመቤት ሊሊያን። «ለ-ርድ ከርስተን ነኝማንም ሰው ይበልጥ በራሱ የሚተማመን ኩሩ ሰው ነው' እያልኩ ዘወትር የማልመው ነው። ለቀጣፊና ለአታላይ ምሕረት የሌለው ፍጡርም ይመስለኛል።»

እመቤት ከራይተን ለለ-ርድ ከርስተን የተናገሩትን በማስታወስ የሁለቱ ሴቶች አሳብ አንድ እንደሆነ ዲያን ተገነዘበች። ከጊዜ በኋላ ዲያን እመቤት ሊሊያንን በጣም እየወደደቻት ስለሂደች በተለያዩ ተናት አብረው ቁጭ ብለው ብዙ ተጫወቱ። የእመቤት ሊሊያን ቤተሰቦች በሕይወት ስለሌሉ ባለብዙ ሀብት ትሁን አንጂ ልክ እንደ ዲያን ብቸኛ

ሴት ናት። ስለዚህ ሊልያን ከጓደኞቿ ሚስት ጋር የመጥፎ ግለትዋ የሚያንት አያሆንም። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ዳያን ስለእጣቢት ሊልያን ብዙ ታስብና ትጨነት ጀመር።

መልከዋ ደንና ነው፡ ሀብት ደግሞ የተትረፈረፈት ናት። ታዲያ እንዴት ነው ባል ያላገባችውን ብዙ ሰዎች ስለሚያደንቋት ያከራከራት። ብዙዎቹም ለጋብቻ ጠይቀዋታል። ግን እርሱዋ እንደሆነ እገሌንም አገሌንም እምቢ አልኳቸው እያለች ታመራለች። ስለዚህ ነገሩ አልገባ ሰላት ዳያን አንድ ቀን ባለዋን ደፍሬ ጠየቅችው። ሱርድ ከረሰቦን ሳቀ።

«ለምን እንደማታገባ ልነግርሽ አልችልም። መልከም እድል ሳያጉመጣት ግን ቀርቶ አያደለም» ሲል መለሰላት።

የዳያንና የእጣቢት ሄደ መደጅነት እየጠነከረ ሲሄድ አንድ ቀን ዳያን ደፍራ «ለምንድነው ባል ያላገባሽው?» ስትል ጠየቀቻት። እጣቢት ሊልያን ሄደ መልስ ሳትሰጣት ለአንድ ደቂቃ ያህል ዝም አለች። ፈትዋ ተለዋወጠ፡ የቅነዘ ስሜትም ወረራት።

«ሄለን» አለች፡ «እነግርሻለሁ። ብዙ ሰዎች ይህን ጥያቄ ከዚህ በፊት ጠይቀውኛል። ግን መልስ አልሰጠኋቸውም። እርግጥ ነው ባል አላገባሁም፡ ወደፊትም አላገባም። ምክንያቱም.....» ጥቂት ዝም አለች። «ምክንያቱም አንድ ለእኔ ፍቅር ስሜት የሌለውን ሰው ስለመደድሁ ነው» ብላ ስትናገር የእጣቢቲቱ አንጋገር አንጀት የሚበላ ዓይነት ስለነበር የዳያን ዓይን በእንባ ተሞላ። «ፍቅር ማለት ምን እንደሆነ ከማወቁ በፊት ልቤንና ፍቅሬን ላፈቀርኩት ሰው ሰጠሁ። ያኔ ግና ትንሽ ልጅ ነበርኩ። ታዲያ አሁን ያንን ፍቅር ለመርሳትና ሌላ ለመጀመር አልቻልኩም። ብቻ ምስጢሬን እንደምትጠብቂ አምናለሁ። የምትመጭ ሴት ለመሆንሽ ፈትሽ ያመለክራል። ያ ክፉ ፍቅር ከልቤ ውስጥ ተተክሎ እንደ ከባድ ድንጋይ ያስቃየኛል። ስለዚህ ስለሚያሰቃየኝ ፍቅር ስናገር ላመጀመሪያ ጊዜ ነው» ስትላት «ሊልያን ልታምኚኝ ትቺያለሽ» አለች ዳያን የሴትዮዋን ጉንጭ እየላመች።

«ታማኝ እንደሆንሽማ አውቃለሁ። ዓይኖችሽ በእንባ የተሞሉት በእኔው በእድለቢስዋ ሴት የተነሳ ስለሆነ ተዪው ይቅር፡ ባናወራው ይሻላል። እኔ እንደሆነ አልከፋኝም። አንደገር ላመፈጠር የሚቻል ቢሆንና ሌላ ወንድ ከልቡ ቢያፈቅረኝ ያን ያፈተረኝን ሰው ትቼ ያንተው ልቤ ውስጥ የተተከበረውን ሰው በነበረ መውደዴን አልተውም ነበር። ዘመኑ እንደሆነ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ስለተዋሐደኝ ሰምጀዋለሁ።»

« ግን ሊልያን፡ ይህ እመድደዋለሁ የምትዪው ሰው ከእርሱ ፍቅር እንደያዘሽ ያውቃል?»

«የለም፣ በጭራም አያውቅም፤ ማወቅ ቀርቶ ጥርጣሬ እንኳን አልገባውም። እርሱም በበኩሉ ከሊላ ሴት ፍቅር ይዞታል። በዚያች ሴት ፍቅር መያዙን ሁሉ ለእኔ ገልጾልኛል። የመጀመሪያ ልጅ ብጠና በፍቅር ቋንቋ ሲገልጽልኝ ልቤ በመታገዝ ከዙሉት የተሰነጠቀ መሰለኝ። ግን እንደ ምንም ብዬ ቻልኩት። ሆኖም ስለፍቅሩ ሲገልጽልኝ ልቤ የደም እንባ አያዘንብ የሚያዋራኝን በጥሞና አጸመጥሁ። የሆዴን በሆዴ ሰላመትሁም ምስጢራን ማንም አላወቀብኝም።»

«ታዲያ ነገሩ ተሰፋ ያለው ይመስልሻል? አንድ ቀን አንቺ እንደ ምትወጂው እርሱም አፍቅሮሽ አባቤ ይሚሳል የሚል እምነት አለሽ?»

«የለም፣ ነገሩ እንቺ እንደምትዪው ተሰፋ ያለው አይደለም። የወደደ ኩት ሰው እንደሆነ ሊላ ሴት አፍቅሯል ፡ ስለዚህ ከልቡ ውስጥ ለእኔ ፍቅር ማረፊያ የሚሆን ትርፍ ቦታ የለውም። ብቻ ዳያን አትጨነቂበት፣ እኔ እንደሆነ ለምጀዋለሁ።»

«ግን የምንኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ ሳለ እሰከ አድሜ ልክ ተከፍቶ መኖር ለማንሳት የማይቻል ከባድ ሸክም መሰሉ አይታይሽም?»

«ቢሆንም የተሳሳተ መንገድ ይዞ ከመራመድ ለዘላለም መከራት ይሻላል» አለች አመቤት ሊልያን። «ከዚህም በላይ ከእኔ መቶ ጊዜ ይበልጥ የሚሰቃዩ ሰዎች አሉ። እስቲ አሁን አንዲት ሳትወድ በግዴታ ትዳር የያዘችን ሴት ውሰጂ ወይም ፍቅር ይዞአት ባል አግብታ በእጁ ካደረጋት በኋላ ፍቅረኛዋ እሸነ የሆነባትን ሴት ተመልከቺ እስቲ። እኔና ዘዘኤ እንደሆነ ብቻችንን አብረን እንኖራለን፣ በማምም እንከራም።»

ከዚያን ጊዜ ወዲህ ዳያን ፡ መቤት ሊልያንን በይበልጥ ወደደቻት። ግን በዚያች ሰዓትም ሆነ ወደፊት ለመቤት ሊልያንን በፍቅር የጣለው ባለኖ ሱርድ ከርስቶን መሆኑን ጨርሳ አላወቀችም። ሊላው ቀርቶ ጥርጣሬ እንኳን አልገባትም። ይሽው ነው የሕይወት አውነታ! እኛ የምንወድዳቸው ሰዎች እነርሱ አይወድዱንም። እኛ የማንወድዳቸው ደግሞ እነርሱ ይወድዱናል። ለመዳጅነት እንኳን ቢሆን እኛ የማንፈልጋቸው እነርሱ ይፈልጉናል፤ እኛ የምንፈልጋቸው እነርሱ አይፈልጉንም።

በ.ያመ·ቅመሃ!

ለ·ርድ ከርስተን ያቺን ቍንጅ በሚስትነት ከዘ·ቱ ከሰገባ ሰባት ዓመታ·ት አለፉ። ጋብቻቸው የሰመረ ስለነበር ጊዜው እያለፈ ሲሄድ ከቤታ·ቸው ውስጥ በደበልጥ ሰላም ሰፈነ። የለ·ርድ ከርስተን ነብርና ዝናም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየላ·ቀ ሄደ። በአገሩ ውስጥ እጅግ በጣም የታ·ወቁ ሰዎች እንኪን ባልዋን ሲያደንቁላት ዳያን እጅግ ትደሰታለች። ለ·ርድ ከርስተን ከአንዲም ዘለቱ የፓርቲ መሪ ሆኖ ተመረጠ። የተመረጠውም አንዳንድ አገር ውስጥ እንደሚደረገው በሀብቱ ወይም በቀላፊነቱ ሳይሆን በብልሀቱና በጉብዝናው ነበር። ስሙ በአገሩ ውስጥ እጅግ እየታወቀና እየገነነ ሲሄድ በሀገሩቱ የፖለቲካ ሥራ ከፍተኛ ሥፍራ ያዘ። በሥራው ለሕዝብ ጥቅም እንጂ ለራሱ ጥቅም እጅግም አያጨነቅም። ስለዚህ ለለ·ርድ ከርስተን ሐቲ ኛነት ጋዜጦች በሰፈው አተ·ቱ። ከት·ት·ላችውን በማጠንከር ሊላው ቀርቶ አልፎ አልፎ ምሳውን የት እንደበላ እንኪን በጋዜጣ ያጠኑ ጀመር።

ባለቢቱ ይህን ሁሉ ከብር ትካፈላለች። በሀገሩ የእርስዋን ዓይነት ከብር የነበራቸው ሴቶች ጥቂቶች ሲሆኑ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሕይወትዋ እንደዚያ በመለወጡ ትገረማለች። የባልዋ አውነተኛ ወዳጅና አማካሪ፤ ሲከፋውም አጽናኝ ሆነች። ባልዋ ቅር ሳይለውና ሳያኩር በየጊዜው ምክር ከእርስዋ ይጠይቃል። አዋቂ በመሆንዋ እጅግ ይከራከራል። ዓመታት ሲያልፉ ዳያን በይበልጥ እያማረች ስለሄደች ገጣሚዎች ለግጥማቸው፤ ሠዓሊዎች ለሚሠርዋቸው ሥዕሎች ሞዴል አደረግዋት።

ከእነዚህ መንፈስ ቅዱስ ከቀረባቸው ሰዎች ቤት ገብቶ መጋበዝ እንደ ትልቅ ክብር ተቆጠረ። በተለይም ዳያንን ማነጋገር እንደ ትልቅ ፀጋ ይታሰበ ጀመር። እመቤት ከርስተን በእውቀትዋ፣ በውበትዋ፣ በትሕ ትናዋና በለጋስነትዋ የታወቀች ሴት ሆነች። ለዓይነ-ስውሮች፣ መስማት ለተሳናቸው፣ ለሙት ልጅነትና ለመሳሰሉት ሁሉ እንደ ሆስፒታልና ትምህርት ቤት ያሉ ተቋሞች ሲቋቋሙ የመሠረት ድንጋይ ከሚያኖሩት መካከል አርስዋ አንደኛዋ ሆነች። የበጎ አድራጎት ሥራ ከተባለ ደግሞ ዳያን ራስዋን አስተደመች። ተመሳሳይ ሥራ ሲታሰብም ዳያን እንድትገኝ ጥሪ በብዛት ይተርብላታል። ይኸኔ ሳት እያለች «እውነትም የጥንትዋ ዳያን ማለት እኔ ነኝ» እያለች ራስዋን ትጠይቃለች።

ታዲያ አሁን እንደዚያ ተከብራና ተፈርታ የምትኖረዋ ሴት ከሰው

ቤት ጠፍተ መሄድዋን፡ እሷን አደራጋ የምትጠላው ሰው ግዴ ስማንያዋን ያላወረደች ቤት መሆንዋን እንዲሁም የመጨረሻ ልጅ እንቁ የነገሩን ሕግና ባህል የጣሰች ቤት መሆንዋን ረስቷ ይሆን?

የለም አልረሳችም፤ ዘመና አየጣልዋት ሲሄዱ የተመኙዋቸው ሥነ ምግባሮች እየጠፉ ያሄድ እንጂ ፈጽሮ ከኅሊናዋ ውስጥ አልጠፉም አውንም ቢሆን የዋንቱ ጭንቀትዋ በአዲስ ኑሮዋ ተደስታ እንዳትኖር የሕይወት አቀሳ የሚቸልበት ጊዜ ነበር። እንዲያውም ከአካቢው በፍጹ ብቻ ሳይሆን በሕልምዋም ሄስተሪያ [illegible] ቁመው ያታያዋታል። ደግሞ ዓመታት አያለፉ ሲሄዱ ይህ ግዙ ትግሉም ቢሆን እሷን ያመነምነል።

ምንም እንኪን ዳሆን በሰው ሞኑ ብዙ ብትመኮርም ለሰው ርኅሩ ነበረች። ማንም ሰው ቢሆን በበንቱ ሃንርዋን እርዳታ አያጠይችም ነበረ ኑትና ለሰፈ ችርታ እንደ ምላለ. የምን [illegible] ሰሰው ሙሉ ሙዳ መዋጪ እርዳታ ማድረግ የሚያስለጅት ሲት ነበረች። ግን ደግኑትዋና ለፎ የምትሙለው ሙሉ ከተድሞው በሄልዋ ጋር የተመሳጠነ ስለማሄመስነ ብቻዋን ስትሆን ብዙ ጊዜ ምርር ብላ ታለትሳለች። ይህንንም ቢሆን ከቲ በኋላ ብትተመሙም፡ ከኅሊናዋ ውስጥ ግን ፈጽሮ ሊጠፉ አለቻለም ጨርሶ ሊያጠፉው የሚችለው አውነቱን ማመጣጥ ብቻ ነበር። ለባልዋ አውነቱን ነግራ ወደ ጥንት ባልዋ ወደ በሩፍ ሲሸሽን ብትመለስ የጎሲና ጠላሳ እንደማይኖርባት ታውታለች። ግን አውነቱን አሙጥታ ወደ በሩና ከምትመለስ ብዙ ሸህ ጊዜ መሞትን ትመርጣለች።

ዳሆን የራስዋ ሁኔቱና ከልብዋ ውስጥ የተቀበረው ስሚት ርኅሩኅ ስላደረጋት በደል ሠርቶ ለሚሸሽና እሷን ለተጨነረ ሰው ከመጠን በላይ ትራራለች። አንድ ቀን ባልዋ ሊረሳው የማይችል ትርኢት ያታመለዋል ባልና ሚስት ቲያትር ቤት ሂደው አሳዛኝ የሆነ ቲያትር ያያሉ። የቲያትሩ ፍሬ ነገር አንዲት ሲት ባልዋን ጥላ ስትሄድ የሚያሳይ ሲሆን ይህች ሴት ከባልዋ ከተለየች ከብዙ ጊዜ በኋላ ሊላ ባል አግብታ ስትኖር የመጀመሪያ ጥቅረኛዋ በድንገት ሲያገኛት በድንጋጤና በኅዘን ብዛት ትሞታለች።

ይህ ቲያትር የዳሆንን ስሚት ከመጠን በላይ ነካው። በደልዋ በመስታወት እንደሚታይ ነገር ቱልው ብሎ አደባይ የመጣ መስላት። በዚህም የተነሳ በአንድ ጊዜ ደምዋ ልጡጥጡጥ አለ። ባልዋ «አመመሽ እንዴ?» ሲል ጠየቃት። «የለም፡ ደኅና ነኝ» ስትል መለሰችለት።

ቲያትሩ አሰዚያልት ፊትዋን አየደበቀች እንደ [illegible] ቻለች።

ቲያትሩ አልቆ መጋረጃው ሲዘጋ ዳያን ቱሉ እንዳለች የባልዋን እጅ ያዘ «ፈሊፕ ይነሙኛል፡ ራሴንም በድያለ አሞኛል። በተጥታ ወደ ቤት ሮጠን» አለችው።

ቲያትሩ ጥሩ ሆኖ ሳለ ዳያን ለምን እንደመማት ባልዋ ስላላወቀ ግራ ተጋ። ከአጠገብዋ እንደ ተቀመጠ ወደ እርስዋ ዞር ቢል ከዘንዱ ላይ ወደቀች።

«ቲያትሩ አስፈራሽ እንዴ ሄለን?» ብሎ ሲጠይቃት «ኧረ የለም፡ አላስፈራኝም። ታሪኩ ግን በጣም ያሳዝናል» በማለት ስትመልስለት አልተጠራጠራትም።

«እምን አላዛኝ ነው፡ አንቺ ግን በጣም አጋነንሽው» አላት።

በቲያትሩ ውስጥ የታዮችው ሴት ጭንቀትና በደል የዳያን በደል ትዝዝል ግልባጭ መሆኑን ቢያውቅማ.....

«ተዝታዛው አየር የራስ ምታትሽን ያሽልልሻል። ወጣ ብለን እንንሸራሸር» በማለት «መፍትሔውን ሲነግራት ተደያዘው ወጥተው በመ ረገላ ትንሽ እንደ ተጓዙ አንዲት ሴት ከደረጃ ላይ ወድቃ አዩ። ሴትዮዋ ብዙ የተሠቃየች ለመሆንዋ ፊትዋ ይመሰክራል። በዚያ ሲያልፉ «ሴት ዮዋ ምን ሆና ይሆን?» በማለት ዳያን በሀዘን ዓይን አደታት አለፈቻት። እንዳጣሚ ሆኖ በዚያው መንገድ ሲመለስ ሲትዮዋ ከመደቸበት ተነስታ ለመራመድ ስትሞክር ደረሰ። ሲትዮዋ ሁለት ጊዜ ያህል እንደ ተራመደች መሄድ አትቷት ከደረጃው ላይ ወደቀች። ሎርድ ከርስተን ሲትዮዋን ልብ አላለም ነበር። ዳያን ሠረገላውን በድንገት አስቁማ ወደ ሲትዮዋ ሮጠች። ሎርድ ከርስተን ፈጥኖ ሚስቱን ተከተለ ሄደ። ዳያን የዚያችን ጣዕራሞት የያዛትን ሴት ፊት ቀና አድርጋ አያየች ከንድዋን አንተራሰቻት።

«ምን ማድረግሽ ነው?» ሲል ባልዋ ተቆጣ።

«መይኔ ፈሊፕ፡ ይህቺ ምስኪን መሞትዋ ነው!» አለች ዳያን።

«ሳይሆን አይቀርም። ታዲያ ለምን ትነኪያታለሽ? አዛዘሽን ተዮት» ሲል በንይለ-ቃል ገሰጻት።

«ለምን ትነኪያታለሽ! ምን አለበት፡ መሞትዋ እኮ ነው!» ስትለው «ባይሆን ልጅት ይርድዋት፡ ቢፈልጉ ምግብና ገንዘብ ወይም የፈለገችውን ይሰጥዋት። አንቺ ግን በእድሽ አትንኪያት» አላት።

«ለምን?» ብላ በድንገተ ስትጠይቀው ተገርሞ «ለምን? ምክንያቱም እኔን ይቀራኛልና ከድንጋዩ ላይ መልሰሽ አሳርፊያት» አላት።

«ከሚተዘጥዝ ጠጠርና ድንጋይ ሳይ አንደት ልጣላት?» ባሰኝ። «እኔን ለማናደድ ነው የምትፈልገው!» ሲል ከዚያ በፊት ባሳየው አኳኋን ፈርቧት። «ሄለን! የባለቤቴ እጅ የዚህችን ጎበጣላ ሴት ፡ መሸከም ስለሌለበት መኸከቱ ይቅርብሽ ነው የምለው።»

ዲያን ቀስ ብላ ከባዋን አውልቃ ሴትዮዋን አንተራሰቻት። ባልዋ በቁጣ ሳይሆን ለስለስ ባለ አንደበት «ያትርታሽን ዲያን ለተከሩት ሴት የፊለማሽውን አድርጊላት። ብትፈልጊ ታክሲ አስመጪ ወደ ሆስፒታል ላኪያት። ግን ስውነትሽ የሴትዮዋን ሰውነት ሲነካ ግን ይከብደኛል» ሲላት አሁንም ዲያን መልስ አልሰጠችም። ግን እንከን ቀና አድርጋ ሰማይ ሰማይ እያየች «ቢያውቅማ.... ሁናቴዬ ታሪክ እንዴ ቢያውቅማ!» በማለት ዲያን አሰላሰለች።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

የክፉ ቀን ጥሪ

ሎርድ ከርስተን በኑሮው ተደስቶና ዝናው ገንኖ ሳለ የጎደለው አንድ ነገር ነበር። ይኸውም ሚስት ካገባ ሰባት ዓመት ቢሆነውም ልጅ ባለመውለዱ ወራሽ አላገኘም። ጉዳዩ ብዙ ቢያሰጨርረውም ባለቤቱን ለማጽናናት ሲል «ብዙ የምንሠራው ሥራ ስላለብን ልጅ ብንወልድ ኖሮ ልጅ ለማሳደግና ለማስተማር ጊዜ አይኖረንም ነበር» በማለት ለዲያን ነገሩን እያቃለለ ይነግራል።

ከዲያን ጎሊና ውስጥ ግን ምን እንደ ነበር ማንም አያውቅባትም። የባሷ የጋለ ፍቅር፣ የማይመለስ የፍቅር ልጅ ትዝታ፣ ሲላ ልጅ የማግኘት ፍላጎትና የማይጠገብ የልጅ ፍቅር ሁሉ ከጎለናዋ ውስጥ የሚቀጣጠሉ ብርቱ ስሜቶች ስለነበሩ ብቻዋን ስትሆን ስትሰት ብላ ታለቅሳለች።

በሲላ በኩል ግን ልጅ ባለመውለድዋ ትደሰታለች። ምክንያቱም ከእጥረት፣ ከጎዘንና ከመጥፎ ታሪክ በስተቀር ለልጅዋ የምትነግረው ነገር ስላልነበራት ነው። በተጨማሪም ልጅ ብታገኝ የሥራትው በደል ቅጣት በእርስዋ ላይ ሳይሆን በልጅትዋ ላይ የሚደርስ መሰላት።

የመጀመሪያ ባለ ያግኘኸል የሚል ፍራቻ ከጊዜ ብዛት ተወግዶላታል። በአሁኑ ጊዜ የሚያሠቃያት በሠራትው በደል የተነሳ ፈጣሪ ለ ይሠርስበት

ስለሚችለው ትጣት ሲሆን ከአዲሱ ባልዋ ልጅ ያልወለደችውም በዚህ ስቢያ ነው ብላ ገምታለች።

አንድ ቀን ሎርድ ከርስተን ከባለቤቱ መልበሻና መኪኒያ ክፍል ውስጥ ይገባል። ሊሊያንና ዳያን ቁጭ ብለው ስለአንድ የግብግ ጥሪ መረቱት ያወጋሉ። ዳያን ፈገግታ በተሞላበት ዓይን ቀና ብላ አየችው። ባልዋ ከባለቤቱ ልብስ መልበሻ ክፍል በመግባቱ ትደነቃለች።

«ፊሊፕ፣ ከቤተ መንግሥት የመጣውን የግብግ ጥሪ ናና አይ» አለችው። «ጊዜ አግኝተህ የምንሄድ ያመስለሃል?» ብላ ስትጠይቀው «የጥሪውን መረቶች ከእጅዋ ተቀብለው ተመለከተው።

«መሄድ አለብን፣ እንዲህ ያለው ጥሪ ግብግ ብቻ ሳይሆን ትእዛዝም ጭምር ነው» አላት።

ሎርድ ከርስተን ሥራ ስለሚበዛበት በጊዜ ከቤቱ መጥቶ አያውቅም። ያን አለት በጊዜ በመምጣቱ ዳያን ተገርማ ቆሰ እንዴት እንደመጣ ትጠይቀዋለች።

«ዛሬ ጠዋት የሦስት ሰዓት አረፍት ለማድረግ ወስኛለሁ። ሙሴ ጸቫር የተባለ የታወቀ ሠዓሊ የሠራቸውን ሥዕሎች እንዳይለት ስለጋበዘኝ ወደዚያ ብንሄድ ደስ ይልሻል ብዬ ገመትኩ» አለ ሎርድ ከርስተን።

« በጣም ደስ ይለኛል» አለች ዳያን። «ሊሊያን አብረሽን ትሂጂ የለም?» በማለት ስታጠየቃት «እንዴታ!» አለ ባልዋ፣ «የሙሴ ጸቫርን ሥዕሎች በቡድን ሆኖ ማየት የሚደገፍ ነው።»

ሰማዩ ጥርት ብሎ የፀሐይ ብርሃን ወጣ በማለቱ ከቤት ውስጥ ተቀመጠ የሚያሰኝ አልነበረም። የወፎች ዝማሬ ከየባቱ ላይ ይሰማል። የዚያን አለት ጠዋት አየር ጸጥ በማለቱ በምድር ላይ ሰላም የሰፈነ ይመስል ነበር። ዳያን ልብስዋን ለመልበስና ለመኪኒል ስትቅበል ደስ ያላትን ዘፈን ታንጎራጉራለች። በዚያች ባማረች ቀን ከፊሊፕ ጋር ወጣ ማለቱ መነፈስዋን አነቃቃው። እውነት አልመሰላትም። ዝግጅትዋን ስትጨርስ ራስዋን በመስታወት ተመለከተች።

ሠረገላው ከበራፍ ቆሞአል። ሦስቱም ተያይዘው ወጡ። በዚያ ደማቅ ቀን በሠረገላ መሄዱ በጣም የሚያስጓጓ ነበር። ከሠዓሊው የሥዕል አስቱዲዮ ደረሱ። ቤቱ ትልቅ ብሎ የተሠራ አነስተኛና በሥነ ጥ በብ የታነጸ ቤት ነበር። የሥዕል አስቱዲዮው መላ ምድር ቤቱን ሲይዝ የመጀመሪያው ክፍል የእንግዳ መቀበያ ነው። ሁለተኛው ክፍል በጣም

ሰፊ ሲሆን ከዚህ ክፍል ውስጥ ሠዓሊው የሥራቸው ሥዕሎች ተሰቅለዋል። አርቲስቱ ሥዕሎቹን የሚስለው ከሦስተኛው ክፍል ውስጥ ነበር። ከዚህ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ብሩሾች፣ ቀለሞች፣ በጅምር ያሉ ሥዕሎች ይገኛሉ። በብዛት ይታያሉ። ከቤቱ ቀለም ጋር የሚሄድ መጥራም የወይን ጠጅ ቀለም ያለው መጋረጃ በመሰቀሉ ክፍሉ ያምራል። በባለ ቅስት በር የተከለለው ቀጥሎ የሚገኘው አነስ ያለው አራተኛው ክፍል የሠዓሊው ተግሪያን የሚለማመዱበት ክፍል ነው።

ሠዓሊው ጎብኝዎቹን በትሕትናና በአክብሮት ይቀበላል። ሎርድ ከርስተን የሙሴ ጳጳርን አሰቱዲዮ በመሳብኘቱ እንደዚያ ተደስቶ የማያውቅ መሆኑን ይናገራል። ደግሞም እንደ ጳያን ያለ ሙንጅ ፈት አይቶ ስለማያውቅ በውበትዋ እጅግ ይደነቃል። ሠዓሊው እንግዶቹን ወደ ሁለቱ ሻውና ሠዓሊው የሳሳቸው ሥዕሎች ወደሚገኙበት ክፍል ይዞአቸው ገቡ። ሥራውን በማድነት እየተዘዋወሩ ሥዕሎቹን ተመለከቱ።

«እያንጻንዱ ሥዕል ተወጻጻሪ የሌለው ሲሆን የሰውን ፈት በማላመር ተወጻጻሪ አይገኝልህም። እነዚህን የመሰለ ፈት ያላቸው ሥዕሎች አይቼ አላውቅም። መልካም ፈቃድህ ቢሆን የባለቤቱን ምስል እንደነዚህ ሥዕሎች አሳምረህ ብትስልልኝ እጅግ ደስ ይለኛ ነበር» ሲል ሎርድ ከርስተን ሠዓሊውን ጠየቀው። በሎርድ ከርስተን መጠየቅ ትልቅ ክብር ስለሆነ ሠዓሊው ትእዛዙን በደስታ ይቀበላል። በዚህን ጊዜ ሠዓሊው ለብዙ ሰው ንግግር ለማድረግ እንደሚዘጋጅ ተናገሪ ይትበጠበጣል።

«ሂለን በዚህ ትር እንደማትስኝ አምናለሁ። ምስልዋ በታወቀ ሠዓሊ እንዲቀረጽ ለረጅም ጊዜ የተመኘሁት ቢሆንም አርስዋ ግን ከማንኛውም ሠዓሊ ፈት ቀጭ ብዬ ምስሌን አሳስነሳም ስላለች ዘመትር እንደጨቶ ጨትኪት ነው» አለ ሎርድ ከርስተን።

ሙሴ ጳቫር አዙንም ቢሆን ጳያን አምቢ ልትል ትችላለች በማለት ተስፋ የመቁረጥ ምልክት ታየበት። ሠዓሊው እነዚያን የጳያንን ሙንጅ ዓይኖች አየየ ምስልዋን ቢያነሳ እጅግ ደስ ይለዋል። አመቤት ሊልያን ወደ ጳያን ዞር ብላ «እሙነትም ምስልሽ በእጅ እንዲነሳ አትፈልጊም?» ስትል ጳያንን ጠየቀቻት።

«አዎን፣ አልፈልግም» አለች አመቤት ከርስተን። «ፈሊጥ ብዙ ጊዜ ጠይቆኝ ነበር።»

«ለምንድነው የጠላሽው?» ብላ አመቤት ሊልያን ስትጠይቃት የጳያን ፈት እንደልማዱ ቀላ።

«እውነቱን ብነግርሽ ትስቂብኛለሽ» አለች ዳያን። «አንድ ልገልጸው የማልችለው አሳብ ጎሊናዬ ውስጥ በመላሪጹ መጥፎ ነገር ይደርስብኛል ብዬ በመፍራት ነው። ብስለት የለለው የልጅ አሳብ እንደሆነ አውቃለሁ። ሆኖም ምንም ማድረግ አልችልም።»

እመቤት ሊልያን ትክክር ብላ ዳያንን ተመለከተቻት። «እንግዳ ነገር ነው» አለች። መዲያው ሎርድ ከርስተን ወደ ሚሰቱ ጠጋ ብሉ «ሂለን፡ የማትፈትሺውን ነገር አድርግ ብዬ ለማስገደድ እንኳን አልፈልግም ነበር። አሁን ግን ተታውሞሽን ትተሽ የምወዳትን ሴት ፈት በእኛ ሥዕል ተሥሉ እንዳይ ብትፈትሺ በጣም ደስ ይለኛል» አላት።

ዳያን የጭንቀት ስሜት እየተሰማት የባልዋን ዓይን ቀና ብላ አየች። ከልብዋ ውስጥ የተቀበረው ብርቱ ተታውሞ ተብላላ። ሆኖም ባልዋን እምቢ ለማለት አዳጋች ሆነባት።

«ለመጪው ትውልድ ተራ ግንዘብ ይሆናል ብዬ ስለገመትኩ ነው» አለ ባልዋ ፈገግታ በተሞላበት ዓይን እያያት። «በሕይወቱ ዘመን መጠቀሰ የሚገባው ሥራ ለመሥራቱ የአገሩ የታሪክ ማኅደር ሊያወሳ ይችላል። የቤተሰቤ የታሪክ ማኅደር ደግሞ ስለአንድ ነገር ማውሳት ይኖርበታል።»

«ምንድነው እሱ?» ባለችው ጊዜ «በመላ እንግሊዝ አገር ውስጥ በውበትዋ የተደነቀች ሚስት ማግባቴን» ሲል መለሰላት።

«እናስ አሁን» አለች እመቤት ሊልያን፡ «ከዚህ በኋላ እምቢ ለማለት ትችያለሽ?» አሁንም የጥርጣሬና የማመንታት ስሜት ከዳያን ፈት ላይ ታየ።

«ፍራቻሽ ምን እንደሆነ ገልጸሽ ብትነግሪኝ ደስ ይለኝ ነበር። ለእኔ መቼም እንግዳ ነገር ነው የሆነብኝ። ብዙ ሴቶች ምስላቸው በእጅ ሥዕል እንዲነሳላቸው በጣም መጓጓታቸውን ነው የማውቀው» አለ ሎርድ ከርስተን።

«ልነግርህ አልችልም ፊሊፕ፡ ልናገረውና ልገልጸው የማልችለው ነገር ነው። እንዲያውም ምክንያቱ ምን እንደሆነ በትክክል ራሴም አላውቀውም። ብቻ ጉዳት የሚያስከትልብኝ እየመሰለኝ ከዚህ ነገር አንድርት አንድ ነገር ሰለሚገፋፋኝ ነው» አለችው።

«ይህ መቼም እስከዚህም የሚረባ አሳብ አይመስለኝም» አለች እመቤት ሂይ ፈገግ እያለች። እመቤት ሂይ ይህን አንዳለች ሙሴ ጳቨር ባልታ በጠባቡ ይትርታ አየጠየቀ አሳብ ለመስጠት ወደ ፊት ቀረብ ይላል።

ሁሉም እና ለእና ግሥመው ሲመሥዩ ዳያን ብቻ በጨዋታው አትሳተፍ ስምቹ በእጠቃላይ ስለሥነጥበብ ብዙ ተነጋገሩ። ዳያን ስእል የመሥ አሳብ አስጨንቆአት ከአነርሱ ተሰይታ ወደ ሴሎች ክፍሎች በመሄ ከመዲሀ መዲያ ትሳለች።

ከመጋረጃውም በስተጀርባ ጥሩ ጥሩ ሥዕሎች እንዳሉ በመገ ወደዚያ ሄደች። መጋረጃውን ገልጣ የሚጠብቃትን አሳዛኝ ታሪክ ሳ ጡን ወደ ውስጥ ገባች። ወደ ግድግዳው ስትመለከት የተፈጥሮን ውበ የሚያሳይና በመኸሉ የሴት ምስል የተቀረጸበት ግሩም ሥዕል አየች።

ዳያን በሥዕሉ ስለተመሰጠች ከዚያ ክፍል ውስጥ ሰው መኖሩን አልተገነዘበችም። አንድ ወጣት የሠራውን ሥዕል ያመለክት ፕሮ ፌትን ቦር ብታደርግ ወጣቱን አየችው። ልጅ ሥዕሉን ማየቱን አውቀው ዳያን አተኩሮ ተመለከታት። በድንገት የሁለቱ ዓይን ግጥምጥም አለ። ዳያ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ አልቻለችም እንጂ ሰውነትዋ በፍርሃት ተርበተበተ። የልብዋ ትርታ ከፍ አለ። ፊትዋ ቱሳ፡ በማምም ደነገጠች።

ምን አሰደነግጣት? የምታየው ሰው በውበት ማረኩአታል? ምስጢሩ አልታወቀም እንጂ የአስተሳሰብ ችሎታዋ ተታውሷል። ልጁ ሳያ ለምን ያህል ጊዜ እንዳፈጠጠችበት አታውትም። ይህን ሰው የት ነው ያየቱት እያለች ራስዋን ጠየቀች። «በሕልሚ ነው ወይስ በውኔ! ሕልም ነው ወይስ ቅዠት! የዚህን ዓይነት ፍጡር በሥዕል ላይ ነው ያየሁት ወይስ የማየ ነገር ሁሉ ሕልም ነው?» በማለት ብዙ አሰበች።

ሰላንጠራራት ከእንቅልፍዋ የነቃች መሰላት። ምን እንደሆነ ለማወ ያልቻለችውን አሳብ አውልቃ ለመጣል ሞከረች። ሆኖም ዓይንዋን ከልጁ ዓይን ለማንሳት ተሳናት። ልጁም ግራ ገባው። እንደዚያ ስታፈጥበት ምን አስቦ ይሆን? ዳያን በተከሳተፈ እንደነበት አናገረችው።

«ያትርታ በሥዕሉ ተመስጪ ከነፍሱ ውስጥ ሰው መኖሩን አልተገ ነዘብኩም ነበር» አለች ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ። ልጁ ቀና ብሎ አያት። እንደገና ዓይን ለዓይን ተጋጠሙ። ነገሩ አርስዋን ግራ አጋባት። እንጂ ልጁ ላይ ይህ ነው የሚባል ብዙ ለውጥ ወይም አዲስ ነገር አልታየበትም። ራስዋን በኃይል ተቆጣጥራ ወደ ልጁ ጠጋ አለች። ዳያን በድጋሚ ያትርታ ከጠየቀች በኋላ ከልጁ ጋር ጨዋታ ጀመረች።

«የማን ናት ባለጊ ብለህ ሳትታዘበኝ አልቀረህም። ከዚህ በፊት በአርግጥ ያየሁህ ስለመሰለኝ ነው» አለችው። እንደገና ዓይን ለዓይን ተጋጠሙ። ዳያን የሥታየው ወጣት ልጅነቱን ጨርሶ ከትልቅ ሰው ደረጃ የገባ ሲሆን መልኩ

ደ፡ ያማረ ነው። ግርማ ሞገስ ማንነቱም ይማርካል። የምታውቀው መልክ
ሥሩ አልተጠራጠረችም። ዓይናቸውና ከንፈሮቹ የእርስዋን ያመሰሳሉ።
ት እንዳየሁህ ከማስላስል በሰተቀር ሌላ አላብ ከጎሲናዬ ውስጥ
ደህ አልቻለም» ስትለው ሳንበስ ብሎ እጅ ነሳት።

«እኔ ግን ምንም ትዝ አይለኝም። «ለዚህ በፊት ባይምት ኖሮ አልረሳ
ያትም ነበር።» በዚህ ጊዜ ከመትጽበት ፊትዋ ለምን እንደ ተለዋወጠና
ናደት ፍርሃት እንዳላት ግራ ገባው። ዳያን ከበስተ-ጀርባዋ የነበረውን
ጠበር አጥብቃ ያዘች። አለበለዚያ ልትወድቅ ሆነ። ያ ድምፅ የማን ድምፅ
ም? የልጅ ድምፅ ከደም ስርዋ ውስጥ ነው የገባው። እንግዳ የሆነ፣ ግን
ሚጣፍጥ ትዝታ ነው የተሰተሰሰባት። ትዝታው ለዘላለም እንደማይጠፋና
ዘእንትልፍ ጊዜ በሕልም እንደሚሰማ ሙዚቃ ነበር።

«ያየኸውን ሰው ሁሉ የማስታወስ ችሎታ አለህ?» ብላ ስትጠይቀው
«ይመስለኛል» ሲል ከመለሰላት በኋላ «ስለእርስዎም ያለኝ ትዝታ ግን እጅግ
በጣም የመነመነ ስለሆነ ምናልባት እኔን የመሰለ ሰው አይተው ይሆናል
የሚል ግምት ነው ያለኝ» አላት።

የልጁ ድምፅ ሳትወድ በግድ ወደ ልጁ እንድትጠጋ ሳባት። ባልዋ
መጋረጃውን ገልጠ በመገረም እንደሚያያት አላስተዋለችም። ባልዋ
በትንሹ ገልጠ የያዘውን መጋረጃ ሰተተው። ዳያን ወደ ልጁ ጠጋ ብላ
የሚሠራውን ሥዕል አተኩራ ተመለከተች። ጥሩ ሥዕል ስለነበር በአድ
ናቆት አየችው።

«እንዴ! ግሩም ድንቅ ሠዓሊ ነህና!» አለችው።

«አምን ኖኝ ልበል ወይስ አንድ ቀን እንደምሆን አልጠራጠርም ብል
ይሻላል መሰለኝ» ሲል ሳይታወቀው የልቡን ጥላጎት ተናገረ።

«የለም፣ አሁንም ነህ» ካለች በኋላ «እነዚህ ሥዕሎችህ ሁሉ አንተው ነህ
የሳልካቸው?» ስትል ጠየቀችው።

«አምን፣ ሁሉም የእኔ ናቸው» ሲል መለሰላት።

«በዚህ ከተጠልክ ሙሴ ጳጳርን ሳታስንት አትቀርም።»

«ይህ ሁሉ በሕይወቴ ዘመን ብቻ ያፈራሁት አይደለም። ከልጅነቴ
ጀምሮ ሕልሚና አላቤ ስለሥዕል ነበር። ግና የኅሊምን ውበት በትክክል
ያየሁ አይመስለኝም። ያለንበት ዓለም በጥሩ ሥዕል የተሞላ ውብ ዓለም
እንደሆነ ጥርጥር የለውም።»

«እንግዲያውማ ሠዓሊ ሁነህ ነዋ የተወለድከው!» አለችው።